አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# “የአገልጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብ ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙ የተመረጡ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ”

በ

አበበች ሀብተማርያም

አማካሪ

መሀመድ አሊ (ዶ.ር)

ጥር፣2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

**"የአገልጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብ ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙ የተመረጡ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ"**

**በ**

**አበበች ሀብተማርያም**

2016 ዓ.ም

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| **አማካሪ ስም** | **ፊርማ** |
| ______________________ | ______________________ |
| **ፈታኝ ስም** | **ፊርማ** |
| ______________________ | ______________________ |
| ______________________ | ______________________ |

## ማረጋገጫ

“የአገልጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብ ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙ የተመረጡ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ” በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ይህ ጥናት የራሴና አዲስ (oroginal) እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው አካዳሚያዊ ዲሲፕሊን መሰረት የተበጀ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

የጥናቱ አቅራቢ ሥም፡- አበበች ሀብተማርያም ጂዳ

ፊርማ፡-______________________________

የጥናቱ ማሟያ መርሐ ግብር፡- የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር

ቦታ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ

የቀረበበት ጊዜ፡- መጋቢት 2016 ዓ.ም

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና------------------------------------------------------------------------------- I

ማውጫ------------------------------------------------------------------------------- II


## ምዕራፍ አንድ


**መግቢያ**-----------------------------------------------------------------------------------------1

1.1. የጥናቱ ዳራ------------------------------------------------------------------------------------1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት------------------------------------------------------------------3

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች-------------------------------------------------------------------------4

1.3.1. የጥናቱ አቢይ ዓላማ----------------------------------------------------------4

1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች-------------------------------------------------4

1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች------------------------------------------------------------4

1.5. የጥናቱ ዘዴ----------------------------------------------------------------------------------5

1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ----------------------------------------------------------------------------6

1.7. የጥናቱ ወሰን----------------------------------------------------------------------------------6


## ምዕራፍ ሁለት


2. ክለሳ ድርሳናት

2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ /Theoretical background/---------------------------------------7

2.1.1. አገልጋይነት ምንድነው?-------------------------------------------------------7

2.1.2. አገልጋይ ሰዎችን ወደ ቤተሰቦቻችን ለምን እንቀላቅላለን?-----------------12

2.1.3. ለአገልጋይነት የሚዳርጉ ምክንያቶች ምንድናቸው?------------------------14

2.1.3.1. የተሻለ ህይወት ፍለጋ-----------------------------------------------14

2.1.3.2. አለመማር------------------------------------------------------------16

2.1.3.3. ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና-----------------------------------------18

2.1.3.4. የትውልድ ቦታን መልቀቅ /መሰደድ/--------------------------------22

2.2. ፅንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፎች /Conceptual background/---------------------------------24

2.2.1. የገጸባህሪ አቀራረብ----------------------------------------------------25

2.2.2. የገጸባህሪ አይነት-----------------------------------------------------26

2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት -------------------------------------------------------------26

## ምዕራፍ ሶስት

## 3. የአገልጋይ ገጸባህሪያት ትንታኔ ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙ የተመረጡ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ

3.1. "አገልጋይ ገጸባህሪያትን" ወደ እዚህ ሙያ የመራቸው ምክንያት -------------------33

3.1.1. የተሻለ ህይወት ፍለጋ አገልጋይነት የተቀጠሩ ገፀባህርያት--------------------33

3.1.1.1. ቢስ ራሔል-----------------------------------------------------33

3.1.1.2. የደራሲዋ ፋይል-------------------------------------------------38

3.1.2. ባለመማራቸው አገልጋይነት የተቀጠሩ ገፀባህርያት-----------------------------41

3.2.1. ቢስ ራሔል-----------------------------------------------------------41

3.2.2. የደራሲዋ ፋይል------------------------------------------------------42

3.2.3. የገቦ ፍሬ-------------------------------------------------------------44

3.3. በቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና አገልጋይነት የተቀጠሩ ገፀባህርያት ----------46

3.3.1. ቢስ ራሔል ----------------------------------------------------------46

3.3.2. የደራሲዋ ፋይል---------------------------------------------------50

3.3.3. የገቦ ፍሬ--------------------------------------------------------58

3.4. የትውልድ ቦታቸውን ለቀው አገልጋይነት የተቀጠሩ ገፀባህርያት------------66

3.2. የአገልጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብና ዓይነት በተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ-----------68

3.2.1. የአገልጋይ ገጸባህሪያት ዓይነት----------------------------------------------68

3.2.1.1. ቢስ ራሔል ------------------------------------------------------68

3.2.1.2. የደራሲዋ ፋይል---------------------------------------------------68

3.2.1.3. የገቦ ፍሬ--------------------------------------------------------69

3.2.2. የአገልጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብ--------------------------------------------70

3.2.2.1. ቢስ ራሔል ------------------------------------------------------70

3.2.2.2. የደራሲዋ ፋይል---------------------------------------------------71

3.2.2.3. የገቦ ፍሬ--------------------------------------------------------72

ማጠቃለያ--------------------------------------------------------------------------------74

ዋቢ ጽሑፎች------------------------------------------------------------------------------78

አባሪ-----------------------------------------------------------------------------------81

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

የጥናቱ ርዕስ “የአገልጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብ ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙ የተመረጡ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ” የሚል ሲሆን ጥናቱን በአራት ምዕራፎች ከፋፍዬ አቀርባለሁ፡፡ ምዕራፍ አንድ መግቢያን መነሻ በማድረግ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ እና የጥናቱ ወሰን የሚባሉትን ስለ ጥናቱ ዕቅድ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉትን ጉዳዮች የሚይዝ ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የተካተቱ ሲሆን በምዕራፍ ሦስት የተመረጡት ሥራዎች ትንታኔ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም በምዕራፍ አራት ጥናቱ የደረሰባቸው ግኝቶችን አቅርቤ ማጠቃለያና ዋቢ ሥራዎችን በተጨማሪም አባሪ በማካተት አጠቃልላለሁ፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በትምህርት ቆይታችን እንደምናውቀው ረጅም ልቦለድ ከስነጽሑፍ ዘውጎች አንዱ ነው፡፡ ልቦለዱ ተነባቢ እንዲሆን ደግሞ አላባውያን ወሳኝ ናቸው፡፡ ከልቦለድ አላባውያን መካካል ገጸባህሪ ዋነኛው ነው፡፡ ገጸባህሪያት በልቦለድ የሚነገረን ታሪክ እንዲከናወን የሚያደርጉ ሲሆን በተቀመጠላቸው ሳይንሳዊ መስፈርት ልክ ከሌሎች አላባውያን ጋር ሆነው እንደ ደራሲያኑ ፍላጎት የሚቀርቡ ናቸው፡፡ “...ከሌሎች የልቦለድ አላባውያን ጋር በመቀናጀት ደራሲው ስለ ህይወት ያለውን አመለካከት የሚገልጽባቸው ዋነኛ መሳሪያዎች ናቸው፡፡” (ዘሪሁን፣2012፣60)

በልቦለድ ዓለም ከሚቀርቡ በርካታ ገጸባህሪያት መካካልም አገልጋይ ገጸባህሪያት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አገልጋይ ገጸባህሪያት ስነጽሁፍ አንድ የጥናት መስክ ተደርጎ መወሰድ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በሚቀርቡ ሥራዎች ውስጥ ከሌሎች ገጸባህሪያት አጠገብ ሲገለፁ ኖረዋል፡፡ በአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ እነዚህን ገጸባህሪያት ማግኘት ከባድ አይደለም፡፡ የሀገራችን የመጀመሪያው የፈጠራ ታሪክ በሆነው የአፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ “ጦቢያ” ውስጥ እራሷ ጦቢያ፣ በፍቅር እስከ መቃብር ብዙዎች ሀብትሽ ይመር፣ ባለእንዲሩ ገብሬ፣ ወለቴ፣ አመቴ፣ አፈረ ጠላቱ፣ ልኩራ በሁሉ ወዘተ.፣ በየልምዣት ደመቀች፣ በሀዲስ ቶሎሳ፣

በየወዲያነሽ የወዲያነሽ፣ በጉንጉን ምንዳዬ ወዘተ. አገልጋይ ገጸባህርያት እየቀረቡልን ስናነብ ኖረናል፡፡

ይህ ጥናት ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የተካተቱ አገልጋይ ገጸባህርያት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ "ቢስ ራሔል"፣ "የደራሲዋ ፋይል" እና "የገቦ ፍሬ" ጥናቱ የተደረገባቸው ረጅም ልቦለዶች ናቸው፡፡ በልቦለዶቹ ውስጥ አገልጋይ ገጸባህሪያት አጠቃላይ አቀራረባቸው ምን እንደሚመስል እና ገጸባህሪያቱ ከየትኛው የገጸባህሪ ዓይነት እንደሚመደቡ ይመረምራል፡፡ በዋናነትም እነዚህ ገጸባህሪያት ለሰው ቤት አገልጋይነት የተዳረጉበትን ምክንያት ከታሪኮቹ በመረዳት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ከአገልጋይ ገጸባህሪያት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነጥቦች ጠቅለል አድርጎ ያስቀምጣል፡፡

በጥናት ሥራው በተከለሉት ሁለት አሰርት ዓመታት በተለያየ ዘውግ ሥራዎቻቸውን ለህትመት ያበቁ ሴት ደራሲያን አሉ፡፡ መረጃዎች እንደሚያስረዱት በተጠቀሱት 20 ዓመታት ውስጥ በሴት ደራሲያን እንቅስቃሴ ውስጥ ከቀደሙት ዓመታት በተሻለ ከፍተኛ መነቃቃት የታየበት በመሆኑ (ዘሪሁን፣ በክፍል ውስጥ ማብራሪያ) በጥናቴ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሠሩ ልቦለዶችን ለመምረጥ ተመችቶኛል ብዬ አስባለሁ፡፡ በነዚህ ዓመታት ውስጥ የታተሙ የሴት ደራሲያን ሥራዎችን መረጃ ለማሰባሰብ ባደረኩት ጥረት ያገኘኋቸውን ብቻ ዝርዝራቸውን በአባሪነት አቅርቤያለሁ፡፡ ምናልባትም በ20 ዓመታት ውስጥ የታተሙት የሴት ደራሲያን ሥራዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ 39 የረጅም ልቦለዶችን፣ 10 አጫጭር ልቦለዶችን እና የወግ ስብስቦችን፣ 28 የግጥም መድበሎችን እና አጫጭር ትረካዎች እንዲሁም 12 ሳይንሳዊ ፅሁፎች፣ እውነተኛ ታሪኮች፣ የህይወት ታሪኮችና ግለ ታሪኮች በአጠቃላይ 89 መፃህፍትን ለአንባቢ አቅርበዋል፡፡ እኔም ከነዚህ ሥራዎች ውስጥ ሶስቱን ረጅም ልቦለድ መፃህፍት ለይቼ የመረጥኩት ከርዕሰ ጉዳዬ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውን ገጸባህርያት ስላገኘሁባቸው ነው፡፡

ለጥናቱ የተመረጡ ልቦለዶች ደራሲያን ነባርና አዲሶች ሲሆኑ ከአንድ በላይ መጻህፍትን ያሳተሙ ናቸው፡፡ ከተተኳሪዎቹ መጻህፍት መካከል የ"ቢስ ራሔል" ደራሲ የሆነችው ፀሐይ መልአኩ በ1982 ዓ.ም "ቋሳ" የተባለውን የመጀመሪያ መጽሐፏን አቅርባለች፡፡ በመቀጠልም "አንጉዝ" በ1984 ዓ.ም፣ "ቢስ ራሔል" በ1996 ዓ.ም፣ "እመ ምኔት"፣ "የስሜት ትኩሳት" ቁጥር አንድና ሁለትን በ2002 ዓ.ም ለተደራሲ ካቀረበች በኋላ "የንስሐ ሸንጎ"ን በ2004 ዓ.ም አሳትማለች፡፡

የዝና ወርቁ በ1979 ዓ.ም "የተሸጠው ሰይጣን" የሚለውን የአጫጭር ልቦለዶች መድበል ከጀማል ሱሌያማን ጋር በመሆን ማቅረብ ከጀመረች በኋላ ይህ መጽሀፍ እስኪታተም ድረስ አምስት መጻህፍትን በግሏና ከሌሎች ደራሲያን ጋር በመሆን አስነብባለች፡፡ "ያልተመቻት ችግኝ" እና "ክንፋማ ህልሞች" አጫጭር ልቦለዶች እንዲሁም "ዛሬን ከተጉበት ነገን ያነጉበት" የእውነተኛ ታሪኮች ስብስብ፣ "የአፍንጮ በር ወፎች" እና "ይቅርታ" የተሰኙ የህፃናት መጻህፍትን አሳትማለች፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተተው "የደራሲዋ ፋይል" የሚለው ረጅም ልቦለድ በ2002 ዓ.ም ለአንባቢ ያቀረበችው ነው፡፡

በ2003 ዓ.ም የታተመወው "የገቦ ፍሬ" ለትንታኔ ከተመረጡት ልቦለዶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ደራሲ እነዬ ሺበሺ ከዚህ መጽሀፍ በፊት ከሌሎች ደራሲያን ጋር በመሆን በተለያዩ ሁለት መጽሀፍት ውስጥ ሥራዎቿን አቅርባለች፡፡ በተጨማሪም "ያልጠራ ደም" እና "ስውር ግዛት" የተባሉ ሥራዎችን ለአንባቢ አበርክታለች፡፡

በእኔ ዳሰሳ በሴት ደራሲያን ሥራዎች ዙሪያ የተሠሩት ጥናቶች ውስን ናቸው፡፡ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ በደራሲ ፀሐይ መላኩ "ቋሳ" እና "አንጉዝ" እንዲሁም በሙሉወርቅ አስራት "ንቡት" መጻህፍት አተራረክ ዘዴ ላይ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ በኤምኤ ዲግሪ ደረጃም በሴት ገጣሚያን የግጥም መጻህፍት ውስጥ "እንስታዊ የስነጽሁፍ ሂስ" በሚል ርዕስ የቀረበ አንድ ጥናት እናገኛለን (ዘሪሁን፣2013፣137-141)፡፡

የአገልጋይ ገጸባህርያት ጉዳይን ቀዳሚ ትኩረቱ ያደረገ ጥናት አንድ ብቻ ነው ያገኘሁት፡፡ ስማቸው ዓለሙ በ1976 ዓ.ም "የአገልጋይ ገጸባህርያት ጥናት ከ1966 እስከ 1975 ዓ.ም በወጡ የአማርኛ ልቦለድ መጻህፍት ውስጥ" በሚል ርዕስ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያውን አቅርቧል፡፡ ከዚህ ሌላ በአገልጋይ ገጸባህርያት ላይ የተደረገ ጥናት አላጋጠመኝም፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሱኝ ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው ለርዕሰ ጉዳዩ ያለኝ ፍላጎት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በርዕሱ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች (ከአንድ በስተቀር) ባለመኖራቸው ይህንን ክፍተት የመሙላት አስፈላጊነት ነው፡፡

ለርዕሰ ጉዳዩ ያለኝን ፍላጎት የተጠነሰሰው በአንድ ወቅት በታደምኩበት የሴት ደራሲያን የስነጽሁፍ ምሽት ላይ አብዛኞቹ ደራሲያት ሥራዎቻቸውን ከህይወት ልምዳቸው ተነስተው እንዳቀረቡት በመግለፃቸው ነው፡፡ ምናልባት የጥናቴ ትኩረት የሆኑት ሥራዎችም ከዚህ

ልምድ ተቀምረዋል በሚል ግምት በዚህ ርእስ ላይ እንድሠራ ወሰንኩ፡፡ አገልጋይ ሆነው ወደ የቤቱ የሚመጡ ሰዎች በአብዛኛው ሴቶች ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በሴት ደራሲያን ሥራዎች ውስጥ ምን ያክል በቅርበት እንደተዳሰሱ መፈተሽ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ምርምር ለማድረግ የሚያነሳሳ ተጨማሪ ምክንያት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች ፡-

### 1.3.1. የጥናቱ አቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም በታተሙ የተመረጡ የሴት ደራሲያን ሥራዎች ውስጥ አገልጋይ ገጸባህርያት ወደዚህ ሙያ ያስገባቸውን ምክንያትና እንዴት እንደቀረቡ ማሳየት ነው፡፡

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

የሚከተሉት የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎች ናቸው፡፡

- አገልጋይነት ምን እንደሆነ ማስረዳት፤
- ባለታሪኮቹ አገልጋይ ገጸባህርያት ሆነው የሚቀርቡባቸው ምክንያቶችንና የሚደርስባቸውን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጫና ማብራራት፤
- በታሪኮቹ ውስጥ ከአገልጋይ ገጸባህሪያት ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን መግለፅ፤

### 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ይህ ጥናት ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም በታተሙ የሴት ደራሲያን ሥራዎች ውስጥ የሚገኙ አገልጋይ ገጸባህርያት አቀራረብ ምን ይመስላል? ለሚለው አቢይ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ሲሆን ዝርዝር ጥያቄዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አገልጋይነት ምን ማለት ነው?
- ባለታሪኮቹ አገልጋይ ገጸባህርያት ሆነው የቀረቡባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
- የሚደርስባቸው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጫና ምንድነው?

❖ በታሪኮቹ ውስጥ ከአገልጋይ ገጸባህሪያት ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

### 1.5. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በአብዛኛው በገላጭ የምርምር ዘዴ አማካኝነት ሊያነሳ የፈለጋቸውን ነጥቦች ያብራራል፡፡ በታላሚ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ መሰረታዊ ነጥቦችን ለይቶ በማውጣት ይዘታቸውን በጥልቀት መፈተሽ፣ በታሪኮቹ ውስጥ የሚገኙ ተተኳሪ ነጥቦች እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነትና የሀሳብ ትስስር እስከምን ድረስ እንደሆነ መገንዘብ እና አላቸው ተብሎ የሚታሰበውን ፍቺ ነጥሎ በማሳየት ፍካሬ መስጠት የጥናቱ ዋና ተግባር ነው፡፡ ለዚህም እንዲረዳኝ በዋናነት “በይነ-ቴክስታዊ” (Inter-textuality) የንባብ ዘዴን እከተላለሁ፡፡

የመስኩ ምሁራን በ“በይነ-ቴክስታዊ” (Inter-textuality) የንባብ ዘዴ የአንድ ጽሁፍ ትርጉም ከጸሐፊ ወደ አንባቢ በቀጥታ እንደማይተላለፍና ይልቁንም ከጸሐፊው ለአንባቢው በሚቀመጡ “ኮዶች” አማካይነት ተደራሲው በራሱ የሚሰጣቸው ፍቺዎች መሆናቸውን ያብራራሉ (Elaine,2011,148-151)። የዚህ ሀሳብ መሰረታዊ መልዕክት ደራሲው ባቀረባቸው ታሪኮች ዙሪያ አንባቢ መነሻ ምክንያቶችን በመያዝ አዋጭ ናቸው ያላቸውን የራሱን ትርጓሜዎች መስጠት ይችላል የሚል ነው፡፡ ተደራሲውን ትርጉም ለመስጠት የሚገፋፉት ምክንያቶች ሳይንሳዊ ዕውቀት፣ ዓለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ ተለምዶ፣ የደራሲው ግላዊ አቀራረብ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በነዚህ መነሻዎች አማካኝነትም በተመረጡት ልቦለድ ሥራዎች ውስጥ የጥናቱ ትኩረት የሆኑትን ነጥቦች በማውጣት ፍካሬ እየሰጠሁ እተነትናለሁ፡፡

ለዚህ ጥናት የተገለገልኩባቸው ልቦለድ መጻህፍት የመመረጣቸው ዋና ምክንያት በሴት ደራሲያን የተዘጋጁ መሆናቸውና በይዘታቸውም አገልጋይ ገጸባህርያትን በዋና ገጸባህሪነት በማካተታቸው ነው፡፡ በመሆኑም መጻህፍቱን ለመምረጥ ያገለገለኝ “ዓላማዊ ናሙና” (purposive sampling) ነው፡፡ የልቦለድ ሥራዎቹን ለመመርመር እንደ መሳሪያ የተገለገልኩባቸው ስለገጸባህሪ ምንነት የሚያስረዱና ሌሎች ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ ካልአይ የመረጃ ምንጮች በምዕራፍ ሁለት በሚሰፍረው ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ውስጥ ትንታኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በታለመለት ልክ ተጠናቆ ለንባብ ሲበቃ የሚያበረክታቸው አስተዋፆዎች ይኖሩታል፡፡

- ሴት ደራሲያን አገልጋይ ገጸባህሪያትን እንዴት እንደሚገልጹ ያሳውቃል፡፡
- በርዕሰ ጉዳዩ /በሴት ደራሲያን ስራዎችም ሆነ በአገልጋይ ገጸባህሪያት/ ዙሪያ ያሉ የጥናት ውስንነቶችን ክፍተት ለመሙላት ያግዛል፡፡
- ተጨማሪ ጥናት ለሚያደርጉ መነሻ ሀሳብ ይሰጣል የሚል እምነት አለኝ፡፡

## 1.7. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙ ሶስት የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ አገልጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብን መርምሮ ትንታኔ የሚሰጥ ነው፡፡ በመሆኑም ታሪኮቹንና ንድፈ ሀሳቡን ለማስታረቅ በተመረጡት ህትመቶች ዙሪያ በይነ-ቴክስታዊ ንባብ በማድረግ ፍካሬ ሰጥቶ በመተንተን ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡

በዚህ ዘመን ከታተሙት የሴት ደራሲያን ልቦለዶች ውስጥ ስለ "አገልጋይ" ገፀባህርያት በስፋት ያነሱት እነዚህ ደራሲያን ብቻ አይደሉም፡፡ በተለይም የፀጋ ዮሐንስ "ጂዳ ነኝ" እና የሰአዳ መሀመድ "እሾህማ ወርቅ" በዓረብ ሀገራት ያሉ ኢትዮጵያዊያን እህቶቻችን በሰው ቤት አገልጋይነት በሚደርስባቸው ችግር ላይ አተኩረው የቀረቡ ረጅም ልቦለዶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ልቦለድ ታሪኮች የተመሰረቱባቸው መቼቶች ማህበረሰባዊ ዳራ በውጭ አገር በመሆኑ በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ በተጨማሪም በዚህ ዘመን የታተሙ የወንድ ደራሲያን ረጅም ልቦለዶችን ይህ ጥናት አይመለከትም፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን በኔና በስማቸው ዓለሙ ጥናት የዓመታት ምርጫ ውስጥ የአስራ ዓምስት ዓመታት ልዩነት አለ፡፡ የሱ ከ1966 ዓ.ም እስከ 1975 ዓ.ም ሲሆን የኔ ደግሞ ከ1990 ዓ.ም ይጀምራል፡፡ በሁለቱ ጥናታዊ ሥራዎች ውስጥ ባሉት ዓመታት /ከ1976 ዓ.ም እስከ 1989 ዓ.ም/ በነበረኝ ፍተሻ በሴት ደራሲያን የተቀረጹ አገልጋይ ገጸባሪያት ለጥናት በሚያግዘኝ ልክ ስላላገኘሁ መነሻዬን 1990 ዓ.ም አድርጌያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናት

### 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ /Theoretical background/

በማህበረሰባችን አገልጋይና ተገልጋይ (የቤት ውስጥ ሠራተኛና አሠሪ) በሚል መጠሪያ አንዳቸው ከአንዳቸው ሳይነጣጠሉ አብረው ይኖራሉ፡፡ አብረው ቢኖሩም የየራሳቸው መለያ ድንበር፣ መለኪያ ሚዛንና ተለምዷዊ የሆነ ሰብዕና መገለጫ መንገድ ስላላቸው ያንን ድንበር ጠብቀው ሲኖሩ እናገኛቸዋለን፡፡ ልዩነታቸውን ለማሳየት የሚተገበረው በተፈጥሮ ሳይሆን በተለምዶ የተገነባ ሰው ሠራሽ መለኪያ ነው፡፡

ሌሎች በርካታ መነሻ ምክንያቶች ቢኖሩም በአብዛኛው በአገልጋዮች የኢኮኖሚ አቅም ዝቅተኝነት ምክንያት የሚፈጠረው ይህ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በተግባራዊው ህይወታችን ውስጥም ለዘመናት አብሮን የዘለቀ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ማስረጃ የራሳችንን የህይወት ልምድ ማንሳት እንችላለን፡፡ ልጆች ሆነን ወላጆቻችን ገንዘብ ለማግኘት ሰው ቤት ተቀጥረው፤ ወይንም የቤት ውስጥ ስራ እንዲያግዟቸው አገልጋዮችን ቀጥረው አይተናል፡፡ በራሳችን ቤት መስርተን ስናስተዳድርም ይህ ልምድ ቀጥሎ እየኖርነው እንገኛለን፡፡

በዚህ ርዕስ ስር ለማብራራት ያሰብኩት የአገልጋይነትን ምንነት፣ አገልጋይ ሰዎችን ወደ ቤተሰቦቻችን ለምን እንቀላቅላለን? እና ለአገልጋይነት የሚዳርጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የሚሉ ነጥቦችን ነው፡፡ በተለይም በሰው ቤት አገልጋይነት ሙያ የሚሰማሩ ሰዎች ምክንያቶቻቸው የተለያዩና በርካታ ቢሆኑም ጎልተው የሚታዩትን ነጥቦች እናነሳለን፡፡

#### 2.1.1. አገልጋይነት ምንድነው?

“አገልጋይ” የሚለውን ቃል ደስታ ተክለ ወልድ “ያገለገለ፣ የሚያገለግል፣ ቅን፣ ሎሌ፣ አሽከር፣ ምንደኛ፣ ባሪያ፣ ገረድ፣ አወዳሽ፣ ካህን፣ ዐዳይ፣ አሳላፊ” በማለት ይተነትኑታል፡፡ (ደስታ፣ 1970፣ 260) የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 ዓ.ም ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላትም “በጦርነት ላይ እየተማረከ ወይም በገንዘብ እየተገዛና እየተሸጠ ወይም ካለበት አካባቢ በግድ ታፍኖ እየተወሰደ ለማራኪው ወይም ለገዛው ወይም አስገድዶ ለወሰደው ሰው በነፃ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ሰው፤ አገልጋይ፣ ታዛዥ፣ ሎሌ፣ መብትና ነፃነት የሌለው በተገዥነት የሚኖር ህዝብ” (1993፣ 270) እያለ በስፋት ሲገልፀው እናነባለን፡፡

የCambridge Business English Dictionary በመረጃ መረብ ባስቀመጠው ትንታኔ መሰረት በዓለም ላይ ከሚገኙ የግለሰብ ቤት አገልጋዮች ውስጥ 73% ሴቶች መሆናቸውን ያስቀምጥና ሙያውን ከዚህ በታች በተገለፀው መልኩ ያብራራዋል፡፡

> "አንድ ሰው በክፍያ ተዋውሎ በሌሎች ሰዎች መኖሪያ ቤት ውስጥ የተለያዩ የቤት ውስጥ ስራዎችን ለማገዝ ሲገባ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ግለሰብ የሌላ ሰውን ቤት ማደራጀት እና ምግብ ማብሰል፣ ማጽዳት፣ ወዘተ…ይጠበቅበታል፡፡ ለቀጣሪዎቹ የዕለት ተዕለት የቤት ውስጥ ስራዎችን ያከናውናል፡፡ እዚህ ላይ ሊጠቀሱ የማይችሉ እንቅስቃሴዎችን በማከናወን ቀጣሪዎቹ የሚፈልጉትን አገልግሎት ያቀርባል።" (Cambridge English Corpus)

በነዚህ ትንታኔዎች መሠረትም ቀደም ባለው ጊዜ ለወንዱ አገልጋይ "ባሪያ" ለሴቷ ደግሞ "ገረድ" የሚል ስያሜ የነበራቸው አሁን ባለንበት ማህበረሰብ ተለምዶ "የቤት ውስጥ ሠራተኛ" ተብለው የሚጠሩ ግለሰቦች የቤት ውስጥ ስራን ሊያግዙ ከቀጣሪዎቻቸው ቤተሰቦች ጋር የሚቀላቀሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በአብዛኛው ከቤተሰቡ ጋር በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን አልፎ አልፎ በተመላላሽነት (ሌላ ቦታ እያደሩ) እየተገኙ አገልግሎታቸውን ያበረክታሉ፡፡

በሀገራችን ከተወሰኑ አሰርት ዓመታት በፊት አገልጋይ ሰዎች የራሳቸው የሆነ መገለጫ የተዘጋጀላቸው ነበሩ፡፡ ጌታና ሎሌ፤ አሳዳሪና ባሪያ፤ ወዘተ. በሚለው ቅንጅት ውስጥ የአገልጋዮቹ የሚሰጡት ግልጋሎት ሳይሆን የሚታየው የበታችነታቸው፣ ጥገኝነታቸው፣ በዘር ሀረግ፣ በአካላዊ ብቃት፣ በቋንቋ፣ በአጠቃላይ በውስጣዊም ሆነ በውጫዊ ሰብዕናቸው ከአሳዳሪዎቻቸው ያነሱ ሆነው እንዲታዩ የሚያደርግ ማህበረሰባዊ ተለምዶ ውስጥ ዘመናትን አሳልፈዋል፡፡

እነዚህ አገልጋይ ሰዎች በተለየ ሁኔታ ከመታየታቸውም በተጨማሪ የነሱ ብቻ በሚመስል ልክ መጠሪያ ሲሰጣቸው እናስተውላለን፡፡ ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው "የባሪያ ስሞች በአማራው ባህል" በሚለው ዕሁፋቸው "ባሪያ" የሚለው መጠሪያ ነፃነት በሚቀነቀንበት ማህበረሰብና ስርዓተ መንግስት ውስጥ ብንጠቀምበት አስደንጋጭ ይሆናልና አንባቢን ላለማስደንገጥ "አገልጋይ" በሚለው ለመተካት አስበው እንደ ነበር ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሙያ ግብራቸውንና የሚደርስባቸውን ጫና እየተመለከቱ መጠሪያቸውን መጻየፉ ብቻ ለውጥ

ስለማያመጣ በነበረበት ሁኔታ "ባሪያ" የሚለውን መጠሪያ ይዞ መቀጠሉ የበለጠ ገላጭነት አለው በማለት ቃሉን በፅሁፋቸው ውስጥ የተገለገሉበትን ምክንያት ያስቀምጣሉ፡፡

> "የጥናቱን አርእስት "የባሪያ ስሞች በአማራው ባህል" ብየዋለሁ፡፡ ዕውነት ነው፤ ገና በአርዕስቱ አንባቢን እንዳላስደነግጥ "ባሪያ" የሚለውን ስያሜ "አገልጋይ" በሚለው ልለውጥ እችል ነበር፡፡ ይህ ግን ፣ "የልጅ መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ" እንደሚባለው፣ ለመጥፎ ነገር (ባርነት) ጥሩ ስም ሰጥቶ የጉዳዩን እውነተኛ መልክ መሸፈን ስለመሰለኝና፣ በበኩሌ ደግሞ ነገሩን በጥሬው ላጠናው ስለፈለኩ፣ በአርዕስቱ ሆነ በፅሑፌ ውስጥ "አገልጋይ" የሚለውን ቃል ትቼ፣ የጉዳዩ ዕውነተኛ መጠሪያ በሆነው "ባሪያ" በሚለው ስም ብቻ ተጠቅሚያለሁ፡፡" (ሰይፉ ፣1964፣ 130)

ከዚሁ ጋር አያይዘውም የሰው ቤት ሰራተኞች "አገልጋይ" በሚለው ስያሜ ለመጠራት ብዙ እንደሚጠብቁና "ባሪያ" ለአገልጋይነት የሚታጨው በርካታ ዘመናትን በባርነት ለጌቶቹ እስካገለገለ ጊዜ ድረስ ብቻ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ "…ባሪያ "አገልጋይ" የመባልን ክብር የሚያገኘው "በባሪያ ፈንጋይ" ወይም "በማራኪ" እጅ ብዙ ጊዜ ተጉላልቶ፣ ብዙ ጊዜም ተሽጦ ተለውጦ፣ እመጨረሻ ጌታው እጅ ገብቶ፣ ከጌታው ቤተሰብ ጋር ከተዋሐደ በኋላ ስለሆነ ነው፡፡ ለዚያውም የጧት ማታ ምሱ 'አንተ ደንደሳም ባረያ!' ነው፡፡" (ሰይፉ ፣1964፣ 130) ከዚህ ሀሳብ በመነሳት በሀገራችን ለዘመናት በአገልጋይ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ይደርስ የነበረውን ተፅእኖ ለመረዳት አንቸገርም፡፡

ከተወሰኑ ዓመታት ወደዚህ በዜጎች ላይ ከስያሚያቸው ጀምሮ ይህንን አይነት ተፅእኖ መፍጠርና ለሠራተኛው የሚገባውን ሰብአዊ ክብር አለመጠበቅ፤ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ በህግ ተጠያቂ እንደሚያደርግ በግልፅ ቢቀመጥም (የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011) ተግባሩ ሙሉ በሙሉ ቀርቷል ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ እንደሌለ እንገነዘባለን፡፡ ብዙውን ጊዜ የስራ ስምምነቱ የሚከናወነው ያለምንም ህጋዊ መሰረት ወይም ከጽሁፍ ውለታ ውጭ በቃል ቢሆንም የሰነድ ስምምነት አለመኖር ግን የህጉን ተፈፃሚነት እንደማያስቀረው የኸው አዋጅ በአንቀጽ ስምንት ላይ ይጠቅሳል፡፡

ይህንን ሀሳብ ምህረት በርሄ በአዲስ አበባ ከተማ (በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ) በሰው ቤት ሰራተኞች ህይወት ዙሪያ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት መነሻ አድርጋ "The Struggle Begins at Home: Domestic Worker Rights in Ethiopia" በሚል ርዕስ በAfrican feminism የመረጃ መረብ ላይ JUNE 12, 2019 በለጠፈችው ፅሁፍ የበለጠ

ታብራራዋለች፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያለው የቤት ሰራተኞች አያያዛችን በፊውዳል ዘመን ከነበረው እምብዛም የተሻለ እንዳልሆነ ትተቻለች፡፡ ሰራተኞቻችን የህግ ከለላ የሌላቸው መደበኛ በሆነ ስምምነት ወደ ቀጣሪዎቻቸው የማይቀላቀሉ፣ 24 ሰዓታትን ለመስራት የሚገደዱ፣ በሚሰሩት የስራ ድርሻ ላይ ምንም ህጋዊ ስምምነት ስለሌለ ቤት ውስጥ የሚከናወንን ማንኛውንም ተግባር እንዲያከናውኑ መደረጋቸውን በፅሁፏ ታስረዳለች፡፡ አብዛኞቹ ወደ ትምህርት ቤት የማይሄዱና በቀጣይ ህይወታቸው ላይ ምንም አይነት አስተዋፅኦ በሌለው ልፋት ውስጥ የሚዳከሩ ስለመሆናቸውም ታነሳለች፡፡

> "...በኢትዮጵያ የቤት ሰራተኞች አያያዝ በአብዛኛው በንጉሣዊው አገዛዝ ዘመን ፊውዳል ቤተሰቦች ባሪያዎቻቸውን በማስፈራራት ለማስተዳደር የሚከተሉትን መንገድ የተከተለ ነው። በተለምዶ እነዚህ ሰራተኞች "ገረድ" ይባላሉ፤ ቀጣሪዎች ሰራተኞቻቸውን ለ24 ሰአታት እንደሚያሰሯቸው ያስባሉ፡፡ ምንም ቀናት እረፍት የሌላቸው እና ለግል ወይም ለቤተሰብ ጉዳይ እንኳን በወር ውስጥ ከአንድ ቀን በላይ ፈቃድ የማያገኙ ናቸው፡፡ ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመማርም ሆነ ለሙያ ክህሎት ማሻሻያ ስልጠናዎች እድል የላቸውም፡፡ በአብዛኛው አሰሪዎች ገና ለመቅጠር ሰራተኛ ሲያፈላልጉ መስፈርታቸው "የማትማር/የማይማር" የሚል ነው..." (MEHRET,2019)

ዓለም አቀፉ የሰራተኞች ፌዴሬሽን እያንዳንዱ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ውስጥ ሊሰራ እንደሚገባና አባል ሀገራትም ይህንኑ ሁኔታ ማረጋገጥ እንደሚጠበቅባቸው ይደነግጋል፡፡

> "ማንኛውም የቤት ሰራተኛ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የስራ አካባቢ የማግኘት መብት አለው። እያንዳንዱ አባል በሀገር ውስጥ ህጎች፣ መመሪያዎች እና ልምዶች መሠረት ውጤታማ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ለቤት ውስጥ ሥራ ልዩ ባህሪዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የቤት ውስጥ ሠራተኞችን የሥራ ደህንነት እና ጤንነትነን የማረጋጋጥ ግዴታ አለበት።" (ILO, 2024)

ሀገራችን የInternational Labour Organization (ILO) አባል ብትሆንም በቤት ውስጥ ሰራተኞች ዙሪያ ፌዴሬሽኑ የሚያወጣቸው መመሪያዎች ስለመተግበራቸው በአግባቡ ትከታተላለች ወይ ብሎ ለመጠየቅ ቢሞከር ክፍተት ማግኘት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ፌዴሬሽኑ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ህጎች

በአባል ሀገራት በሙሉ እንዲተገበሩ ከማዘዙም በላይ አባል ለመሆንም የመጀመሪያው መስፈርት የፌዴሬሽኑን ህግ መቀበል በመሆኑ ነው፡፡

በሀገራችን ማህበረሰባዊው ተለምዶ ለአሰሪና ሠራተኛ ድንበር አበጅቶ በጎ የሚባሉ መገለጫዎችን ለአሠሪው ቡድን ከዚህ በተቃራኒው የሆኑትን መለኪያዎች ደግሞ ለአገልጋዮች በመስጠት ሲፈርጃቸው እናያለን፡፡ በሀገራችን ለዘመናት ከኢኮኖሚያዊ አቅም ባሻገርም የቆዳ ቀለም፣ የፀጉር ሁኔታ፣ የመናገር ብቃት፣ አካላዊ ጉዳት ሲኖርም በዛ ላይ በመመስረት ወዘተ. የተሻልኩ ነኝ የሚለው የማህበረሰብ ክፍል ልዩ መገለጫ ያዘጋጅላቸው ነበር፡፡ አሳዛኙ ነገር ተሰያሚዎቹ በሌሎች የተጫነባቸውን ማንነት የመከላከል አቅማቸው ደካማ ከመሆኑ የተነሳ አምነው መቀበላቸውና ለተለያየ ጉዳት መዳረጋቸው ነው፡፡ በሌሎች ዓለማትም የምናገኘው ልምድ ከዚህ የተለየ እንዳልነበር መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

> "...ከበርካታ ሀገራት የቀደመ ታሪክ ለመረዳት እንደምንችለው የተለየ የቆዳ ቀለም ያላቸው የማህበረሰብ አካላት፣ በኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ ተብለው የሚፈረጁ ዜጎች፣ ሴቶች፣ በቋንቋቸውና በባህላዊ አኗኗር ልምዳቸው ከገዢ ወገን ያልሆኑ ቡድኖች በሚደርስባቸው ተፅእኖ ምክንያት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሚናቸው ለዘመናት ዝቅ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሲቀጥል አይተናል..." (jinH.,2017,2)

በአብዛኛው እራሳቸውን መከላከል የማይችሉት ተጎጂዎች ከቤተሰብና ከማህበረሰብ ተገልለው ለብቸኝነት ይዳረጋሉ፡፡ በቤተሰብና በማህበረሰብ ውሰጥ የተለዩ ተደርገው መቆጠራቸው ደግሞ ሁለንተናዊ የሆነ ጥልቅ ጉዳት ስለሚያስከትልባቸው ከላይ እንደተገለፀው ለብቸኝነት፣ ለአካላዊና ለስነልቦናዊ ህመም ይዳረጋሉ፡፡ መቋቋም ሲያቅታቸውም እራሳቸውን እስከ ማጥፋት ይደርሳሉ፡፡ ከዚህ የተሻለ እርምጃ ወሰዱ ከተባለ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ማይታወቁበት ማህበረሰብ እስከመቀላቀል የሚደርስ ውሳኔ ያሳልፋሉ፡፡ አካባቢያቸውን እየጣሉ ወደማያውቁት አካባቢና ማህበረሰብ ለመቀላቀል ሲገደዱም ያላቸው ኢኮኖሚያዊ፣ አካላዊና ስነልቦናዊ ዝግጅት የተሻለ ሙያ ላይ ሊያሰማራቸው የሚችል ባለመሆኑ በማያውቁት ስፍራ በህይወት ለመቀጠል የሰው ቤት አገልጋይነት ብቸኛ አማራጫቸው ይሆናል፡፡

## 2.1.2. አገልጋይ ሰዎችን ወደ ቤተሰቦቻችን ለምን እንቀላቅላለን?

የቤት ውስጥ ሠራተኞች የቤተሰብ አባላት ባለመመቸት፣ ባለመቻልና በተለያየ ምክንያት ሊያከናውኑ ያልቻሉትን የቤት ውስጥ ሥራ እንዲሠሩ ሲባል በደመወዝ የሚቀጠሩ ናቸው፡፡ አብዛኞቻችን የቤት ሰራተኞችን ወደ ቤተሰቦቻችን የምንቀላቅለው ለኑሯችን ወሳኝ የሆኑ ነገር ግን እራሳችን ልናከናውናቸው ያልቻልናቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑልን በማለት ነው፡፡ በመኖሪያ ቤታችን ውስጥ መከናወን የሚገባቸውና በራሳችን ልናከናውናቸው ያልቻልናቸውን ተግባራት ለሌሎች ሰዎች አሳልፈን የምንሰጠው ከአቅማችን በላይ በሆኑ ምክንያቶች ነው፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ደግሞ እንደዚሁ በህይታችን ታላላቅ የሚባሉ ተግባራት በመሆናቸው እነሱን በራሳችን ተወጥተን የቤት ውስጥ ተግባራትን ደግሞ ለሚያግዙን ሰዎች አሳልፈን እንሰጣለን፡፡ በመሆኑም የቤት ውስጥ ሠራተኞች ለሚቀላቀሏቸው ቤተሰቦች ኑሮ እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡

ይህንን ሀሳብ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት "በዘመናዊ የባርነት ዓይነቶች ላይ" ጥናት የሚያካሂዱት ባለሙያ ኡርሚላ ቡሆላ በተሻለ መንገድ ይገልፁታል።

> "በአለም ላይ ያሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው አባወራዎች በስደተኛ የቤት ሰራተኞች ላይ ጥገኛ ናቸው። ይህ ለህብረተሰቡ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ እውቅና እና ዋጋ ሊሰጠው የሚገባው ብቻ ሳይሆን፤ መንግስታት እና የግል የስራ ስምሪት ኩባንያዎች የሁሉንም ስደተኛ፣ የቤት ሰራተኞችን፣ በጣም ተጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ ሰብአዊ መብቶችን የሚጠብቁበት፣ የሚያከብሩበት እና የሚያሟሉበት ጊዜ ነው" (Bhoola, September 2018)

የቤተሰብ ኃላፊ የሆንን በርካታ ሰዎች ምናልባትም ገንዘብ በሚያስገኙልን ተግባራቶቻችን ተወጥረን፣ በስራ ላይ ባሉን አዳዲስ ፕሮጀክቶች ላይ ማተኮር ፈልገን፣ ያሉንን ሙያዊ ክህሎቶች ለሌሎች ለማካፈል ስንል ጊዜ አጥተን ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ተግባራቶች በቤታችንና በቤተሰባችን ላይ እንዳናተኩር ሊያደርጉን የሚችሉበት ሁኔታ ብዙ ነው፡፡ ስለዚህም ዘና ለማለትና ከቤተሰብ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ በቀኑ ውስጥ የምናገኛትን ጥቂት ተጨማሪ ሰዓት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የቤት ሰራተኛ መቅጠር ህይወታችንን ሚዛናዊ ለማድረግ የሚረዳ መፍትሄ ነው።

International Domestic Workers Federation's July 2018 በwebsite ላይ ባጋራው መረጃ አገልጋይ ሰዎች የምንቀጥርባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች በማለት ያስቀመጣቸው ነጥቦች አሉ፡፡ ከነዚህ መረጃዎች በመነሳትም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ቁርኝት ያላቸውን በመምረጥና በማደራጀት በጥናቴ ውስጥ አካትቻለሁ፡፡

- ረጅም ሰዓታትን ገንዘብ በሚያስገኙ ተግባራት ላይ ከቤታችን ውጭ ካሳለፍን ወደ ቤታችን ገብተን ዘና ለማለት መፈለጋችን ፍጹም ምክንያታዊ ነው፡፡ በሳምንቱ መጨረሻ በምናገኛቸው የእረፍት ቀናትም /ቅዳሜና እሁድን/ በቤት ውስጥ ስራዎች ረጅም ሰአታት መፍጀት አድካሚና አሰልቺ ይሆንብናል፡፡ ስለዚህም የቤት ሰራተኞቻችን ወደ ቆንጆ፣ ንጹህና የተሟላ ቤት እንድንመለስ እድል ይፈጥሩልናል ብለን ስለምናምን የቤት ሰራተኞችን እንቀጥራለን፡፡
- በኑሯችን ውስጥ የምንፈልጋቸው ጉዳዮች በአንድም በሌላም የኛን ትኩረት ይፈልጋሉ፡፡ ልጆች ወይም እንስሳት ወይም ብዙ እንግዶች እንደየፍላጎታችን የኑሯችን ማጣፈጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የቤተሰብ አባላት ደግሞ የሚገለገሉባቸው ሁኔታዎች ተጨማሪ ጊዜ፣ ጉልበትና ወጪ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በየዕለቱ ምግብ ማብሰል፣ ንፅህና መጠበቅና ደህንነታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ተግባራት እኛ ማድረግ ካልቻልን ከፍተኛ ጫና ይፈጠርብናል፡፡ ጥሩ የቤት ሰራተኛ ማግኘት ይህንን ጫና ከማቃለሉም በተጨማሪ በቤተሰቦቻችን እና በጓደኞቻችን ጠቃሚ ለውጦች ላይ ማተኮር እንድንችል ያግዘናል፡፡
- ብዙ ጊዜ አዲስ ወላጆች ወይም ቤተሰቦች አዲስ ሕፃን ሲመጣ ከፍተኛ ጫና ይሰማቸዋል። አራስ እናትም ትኩረቷ ወደ አዲሱ ህፃን ላይ ብቻ ከመሆኑም በተጨማሪ ድካም ይሰማታል፡፡ ስለዚህም ተጨማሪ እንክብካቤ ትፈልጋለች፡፡ በዚህ ሰዓት የሚቀጠሩ የቤት ሰራተኞች ኃላፊነታቸው በርካታ ነው፡፡ በህፃኑ ላይ፣ በአራሷ እናትና በቀሪው የቤተሰብ አባላት ላይ አተኩረው ተግባራቶቻቸውን ሲወጡ እናያለን፡፡ ይህም ለቀጣሪዎች የሚኖረው ድጋፍ ከፍተኛ ነው፡፡
- በሀገራችን አብዛኛውን ጊዜ በተለይም ወንዶች ለቤት ውስጥ ስራ ሩቅ ናቸው፡፡ ሙሉ በሙሉ ላያውቁ ይችላሉ፡፡ የሚያውቁ ከሆነም በአብዛኛው ስልቹዎች ናቸው፡፡ ከህፃንነት ጊዜያቸው ጀምሮ በቤተሰባቸው ውስጥ ሌሎች በሚያከናውኑት ተግባር አገልግሎት እያገኙ የኖሩ የቤት ውስጥ ስራዎችን የሚችሉበት አጋጣሚ ብዙ

አይደለም፡፡ አለመቻላቸው ደግሞ ተግባሩን እንዲፈሩትና እንዲጠሉት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ግድ ሲሆንባቸውና መክፍል ከቻሉ ተግባራቶቹን ለሰው ቤት ሰራተኞች አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡ በዚህም የሚወዷቸውን ነገሮች ለማድረግ ነጻ ይሆናሉ፡፡

- ብዙ ጊዜ ለስራ ወይም ለመዝናናት አዘውትረን የምንጓዝ ከሆነ ቤታችን ባዶ ይሆናል። ይህ የደህንነት ስጋት ነው፡፡ አብረውን የማይጓዙ የቤተሰብ አባላትም ሆኑ ንብረቶቻችን እንዲጠበቁልን የቤት ሰራተኛ እንቀጥራለን፡፡ ይህም የአእምሮ ሰላም ስለሚፈጥርልን ከቤታችን ያራቀን ጉዳይ ላይ እናተኩራለን፡፡

እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች በርካታ ምክንያቶች የቤት ሰራተኛ እንድንቀጥር የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በተለይም የቤት ሰራተኞቻችን ጥሩዎች ሆነው ሙሉ ዕምነታችንን ካገኙ የቤተሰባችን ደህንነት ማረጋገጫዎች ስለሚሆኑልን ትኩረታችን ከቤታችን ውጭ ባሉ ኃላፊነቶቻችን ላይ ይሆናል፡፡

## 2.1.3. ለአገልጋይነት የሚዳርጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለሰው ቤት አገልጋይነት የሚዳርጉ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ የተሻለ ህይወት ፍለጋ፣ ጥልቀት ያለው ቤተሰባዊ ድህነት፣ የተለያዩ ተፈጥሯዊ አደጋዎች (ድርቅ፣ ጎርፍ)፣ አለመማር፣ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫናዎች፣ ቤተሰብንና የትውልድ አካባቢን ለቆ መሰደድ፣ የሰው ቤትን ስራ የማይከለክል አካላዊ ጉዳት፣ የኑሮ ውድነት ወዘተ. ወጣቶችን ለሰው ቤት አገልጋይነት የሚዳርጉ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በእኔ ጥናት ትኩረት ያደረኩባቸው የተወሰኑትን ሲሆን እነሱም የተሻለ ህይወት ፍለጋ፣ አለመማር፣ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና፣ የትውልድ ቦታን መልቀቅ /መሰደድ/ የሚሉትን ነጥቦች ነው፡፡ እነዚህ ችግሮች በቤተሰብ ወይም በግለሰብ ደረጃ ሲከሰቱ ከነሱ ለመላቀቅ የተሻለ አማራጭ ማግኘት ያልቻሉ ሰዎች የሰው ቤት አገልጋይነት ብቸኛ አማራጫቸው ይሆናል፡፡

### 2.1.3.1. የተሻለ ህይወት ፍለጋ

ማለፊያ አሩዋ ፊላባ “Saratanya (House Servant) in Ethiopia and ‘Ya’yan Magajiya (Errand Children) in Nigeria” የሚለው ንፅፅራዊ ጥናታቸውን በ African Research Review መፅሄት ላይ በ Jan., 2008 ባቀረቡበት ጊዜ ብዙዎቹ የሰው ቤት ሰራተኞች የቤተሰቦቻቸው የኢኮኖሚ አቅም ዝቅተኝነት የሰው ቤት ሠራተኝነትን እንዳስመረጣቸው ይገልፃሉ፡፡

> "በዚህ የዳሰሳ ጥናት ወቅት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሁሉም የሰው ቤት ሰራተኞች ማለት ይቻላል በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳጊዎቻቸው መኖሪያ ውስጥ ያለው ጥልቅ ድህነት ይህንን ሙያ እንዲመርጡ እንዳደረጋቸው አስረድተዋል። በተለይም ደግሞ ታዳጊና ወጣት እንዲሁም ህፃናት ሴቶች በብዛት ወደ ከተማ በመሰደድ በአገልጋይነት ተቀጥረዋል፡፡" (Malefiya, 2008, 226)

ከላይ እንደተጠቀሰው በተግባራዊው ህይወታችንም ሆነ በልቦለዶቻችን ውስጥ የሰው ቤት አገልጋይ በመሆን የሚቀጠሩት በአብዛኛው ከገጠሩ የሀገራችን ክፍሎች ወደ ከተማ የሚፈልሱ ሴት ህፃናትና ወጣቶች ናቸው፡፡ የእነዚህ ወጣቶች መሰረታዊ ችግር የአርሶ አደሮቻችን ድህነት ነው፡፡ በአብዛኛው የገጠር ነዋሪ አርሶ አደር ውስጥ የቤተሰብ ምጣኔ እውቀት ካለመዝለቁም በላይ  በቂ ምርት ሊያመርት አለመቻሉ ቤተሰቦቹን በአግባቡ ለመያዝ የሚቸገርበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በቂ ቤተሰባዊ መጠለያ አለመኖር፣ የእርሻ መሬት ጥበት፣ የንፁህ ውሃ አለመኖር ወይንም ውስን ተደራሽነት፣ የምግብ ዋስትና ማጣት፣ የጤና እንክብካቤ አቅርቦት እጥረት ወዘተ. እያስመረራቸው የተሻለ ህይወት እንዲናፍቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ሴት ህፃናትና ወጣቶች የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ህይወት ለመለወጥ ወደ ከተማ እየተሰደዱ ለሰው ቤት አገልጋይነት እንደሚዳረጉ "Young, Female and Looking for Change: Migrant Girls' Narratives in Addis Ababa በሚል ርዕስ Marina de Regt and Felegebirhan Belesti በ March 2017 ባቀረቡት የጥናት ስራ ውስጥ በስፋት አብራርተውታል፡፡

> "ባለፉት አስር አመታት በኢትዮጵያ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች የራሳቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለማሻሻል ከትናንሽ መንደሮች እና ከገጠር ከተሞች ወደ አዲስ አበባ ገብተዋል።… ብዙ ልጃገረዶች ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት ካላቸው ፍላጎት በተጨማሪ እንደ ያለ እድሜ ጋብቻ እና የመንቀሳቀስ ነፃነት መገደብ ከመሳሰሉ ጨቋኝ የስርዓተ-ፆታ ስርዓቶች ለመሸሽ ይሰደዳሉ።…በአብዛኛው የሚሰደዱት ደግሞ ማረፊያቸው የሰው ቤት ሰራተኝነት…ነው፡፡" (Marina and Felegebirhan, 2017,1-2)

ከላይ በጥናት አቅራቢዎቹ እንደተገለፀው ብዙዎችን ህፃናትና ወጣት ሴቶች ለሰው ቤት አገልጋይነት ከሚዳርጓቸው ምክንያቶች ዋናው የኢኮኖሚ አቅም ዝቅተኛነት ነው፡፡ በቂ

ገቢ የሌላቸው ቤተሰቦች ውስጥ የተወለዱና ያደጉ ልጆች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት፣ ቤተሰቦቻቸውን በገቢ ለመደገፍና ቀጣይ ህይወታቸውን በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለመጣል በአጠቃላይ የተሻለ ህይወትን ፍለጋ ለሰው ቤት አገልጋይነት ይዳረጋሉ፡፡

## 2.1.3.2. አለመማር

በሰው ቤት ተቀጥረው የሚሰሩ በርካታ ግለሰቦች በአብዛኛው የተማሩ አይደሉም፡፡ መማር ያልቻሉት ስለፈለጉ ሳይሆን ከህፃንነት እድሜያቸው ጀምሮ ትምህርት ለማግኘት የሚያስችል አማራጭ ስላልተፈጠረላቸው ነው፡፡ ይህንን እውነታ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ስናየው ሁለንተናዊ ችግር በሚያስከትለው ሀገራዊ ድህነታችንና ለዘመናት በማህበረሰቡ ውስጥ ተስፋፍተው በኖሩት ጎጂ አስተሳሰቦች ምክንያት የተፈጠረ ነው፡፡

ትምህርት ሰዎች የተሻለ ኑሮ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን እውቀት እና ክህሎት ይሰጣል፡፡ አብዛኛው የሀገራችን ገጠር ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩ ህፃናትና ታዳጊዎች ግን ይህንን እድል ለማግኘት አልታደሉም፡፡ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ ልዩ ልዩ የመማሪያ ግብአቶችን የማግኘት እድላቸው በእጅጉ ጠባብ ነው፡፡ ትምህርት ቤት በቅርብ ርቀት ያገኙ አካባቢዎች ላይ የሚገኘው አርሶ አደር ማህበረሰብም ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ የሚያስችል ንቃተ ህሊና ስለሌለው ወንዶቹን የግብርና ስራ እንዲያግዙ ሴቶች ህፃናትን ደግሞ ትዳር ይዘው ቤተሰብ እንዲመሰርቱ ማድረግን ይመርጣል፡፡ እነዚህ ህፃናትና ታዳጊዎች ደግሞ ይህንን እድል ማግኘት ስላለልቻሉ የሚጎላቸው ጉዳይ ብዙ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ህንዳዊው የSavitribai Phule Pune University መምህር Dr. D. Y. Patil በድረ ገጽ ባጋሩት መረጃ የበለጠ ያብራሩታል፡፡

> "ትምህርት ግለሰቦች የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የባህል መብቶችን እንዲጠቀሙ ስለሚያስችል በእጅጉ አስፈላጊ ነው። በእያንዳንዱ ደረጃ መማር የሁሉም ሰው ህይወት አስፈላጊ ገጽታ ነው፡፡ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ መንገድ የምናገኘው ትምህርት በህይወት ዘመናችን ውስጥ የምንራመደውን እያንዳንዱን እርምጃ ልኬት የሚመጥንልን ነው፡፡ አሳቢ፣ ሩህሩህ እና በትብብር የምናምን፣ በህብረት ማደግን የምንናፍቅ ሆነን የምንቀረፀው በትምህርት ነው፡፡ ያለ ምንም ችግር ወደ ፊት ለመራመድና በህይወታችን ውስጥ ያለማቋረጥ የሚከሰቱ ለውጦችን ለመቋቋም መማር ጠቃሚ

> መሳሪያ ይሆናል። አሁን ካለው ዓለማቀፋዊ አስተሳሰብ /globalization/ ጋር እራስን አስማምቶ ለማቆየት መማር በጣም አስፈላጊ ነው። አዳዲስ ነገሮችን መማር ከእለት ተእለት ህይወታችን የማይነጠል ተግባር ከሆነ ቆይቷል፡፡ መማራችን ደግሞ እነዚህን አዳዲስ ነገሮች በተለያዩና ቀላል በሆኑ መንገዶች እንድንፈታ እድል ይፈጥርልናል፡፡…" (Patil, 2021)

በዚህ ጥቅል ሀሳብ ውስጥ በርካታ ነጥቦችን ማንሳት እንችላለን፡፡ በተለይ ከገጠር ወደ ከተማ በመሰደድ የሰው ቤት አገልጋይ የሚሆኑ ታዳጊዎች ብዙ የሚያጡት ነገር አለ፡፡ ባለመማራቸው ምክንያት የተሰማሩበትን ሙያ ከሚጀምሩባት እለት አንስቶ ጥቃቅን የሚመስሉ ነገር ግን ውጤታቸው የከፋ የቃል ስምምነቶችን በመፈፀም ከቀጣሪዎቻቸው ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ ሰብአዊ መብታቸው የሚከበረው እንኳን እነሱ አውቀው ስለጠየቁ ሳይሆን ቀጣሪዎቻቸው በጎ ሰዎች ከሆኑ ብቻ የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ባለመማራቸው ምክንያት ለእለት እንቅስቃሴያቸው እንጂ ለዘላቂ ህይወታቸው ዋስትና የሚሆናቸው አንዳችም መሰረታዊ ነገር ሲይዙ አይታይም፡፡

በቀጣሪዎቻቸው ቤት ውስጥም ሆነው መማር እየፈለጉ መማር ሲከለከሉ የሚቀረቀርላቸው አካልም ስለሌለ እንዲሁ እንደባከኑ ይቀራሉ፡፡ ይህንን ነጥብ ዮሀንስ መርሻ በለጠ የተባሉ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር በInternational Jornal of Sociology and Anthropology በJune 2014 ላይ ባሳተሙት የጥናት ፅሁፍ ውስጥ በጥልቀት ይገልፁታል፡፡

> "አሁን ያለው የኢትዮጵያ መንግስት ሴት የቤት ሰራተኞች ከሌሎቹ የሴቶች ቡድን በተለየ በሁሉም ጥቅማጥቅሞች እኩል እድል እንዲያገኙ አላደረገም። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሴቶች ጉዳይ ከሀገሪቱ ዋና አጀንዳዎች አንዱ ሆኗል፡፡ በተለይም የሴቶች የትምህርት ተደራሽነት እንደ መሰረታዊ መብት እውቅና የተሰጠው ሲሆን፣ የትምህርት ተደራሽነታቸውን ማሳደግ ከኢትዮጵያ የትምህርት ግቦች አንዱ ነው። እነዚህን ግቦች እውን ለማድረግ በስልጣን ላይ ያለው የኢትዮጵያ መንግስት የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ መጠን ለማሳደግና በዚህም በአጠቃላይ በዕድገት ሂደት ውስጥ የተለያዩ ስልቶችን ነድፏል። በዚህ ረገድ መንግሥት ትልቅ ስኬት ያስመዘገበ ቢሆንም ይህ ስኬት ሴት የቤት ሠራተኞችን ያካተተ አይደለም።" (ዮሀንስ፣ 2014፣ 193)

የትምህርት እጦት ከአንባገነን ቀጣሪዎቻቸው ህጋዊ መብታቸውን የመጠየቅ እድላቸውን ይገድብባቸዋል። ስለነሱ መብት ተጨንቆ በምን ሁኔታ ውስጥ እንደሚኖሩ የሚከታተል ተቋም ስለሌለ ሲበደሉ የመሰማት እድላቸው ጠባብ ነው፡፡ ከላይ የጠቀስናት ጥናት አቅራቢ ምህረት በርሂ መሰረታዊ በሚባሉ የቤት ሰራተኞች መብት ጥሰት ዙሪያ የህግ ከለላው ሰፊ ክፍተት ያለበት መሆኑን ገልፃ ተደጋጋሚ በደሎች ሲፈፀምባቸው እነሱ አውቀው ወደ ፍትህ አካላት እንደማይሄዱ ታስረዳለች፡፡ ጉዳያቸው ለፍርድ ሲቀርብም የሚያገኙት ፍትህም በቂ እንዳልሆነ ታብራራለች፡፡

> "…የቤት ሠራተኛ ክፍያ በጣም የተለያየ እና ምንም አይነት መደበኛ ወይም ግልጽ የሆነ ግምት የሌለው ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ከአሠሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት በማንኛውም የውል ወይም ህጋዊ ሰነድ የተረጋገጠ ስላልሆነ ነው፡፡ ይህ መደበኛ ያልሆነ አካሄድም ከሚመለከተው መንግስታዊ አካል ምንም አይነት ህጋዊ ቁጥጥር አይደረግበትም፡፡ ሌላው አሳዛኝ ጉዳይ ከቀድሞ ጀምሮ በነበረው የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ኃይል አለመመጣጠን ምክንያት አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ወደ ሰው ቤት ሠራተኝነት የሰማራሉ፡፡ ስለሆነም ዘርፈ ብዙ ለሆነና በፆታ ላይ ለተመሰረተ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው። ብዙዎቹ የቤት ሠራተኞች በአሠሪዎቻቸው ሊደፈሩ ወይም ሊደበደቡ ይችላሉ። ይህን መሰሉ የጥበቃ እጦት በኢትዮጵያ እስካሁን መፍትሄ ያልተገኘለት ትልቅ የህግ እና የሞራል ክፍተት ውጤት ነው።…" (Mehret,2019)

በአጠቃላይ ሰዎች በውዴታ ሳይሆን አማራጭ በማጣት ለሚሰማሩበት የሰው ቤት ሰራተኝነት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል አለመማር አንዱ መሆኑን አይተናል፡፡ እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ባለመማራቸው ምክንያት በርካታ ችግሮችን በህይወታቸው ውስጥ ያስተናግዳሉ፡፡

### 2.1.3.3. ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና

የእርስ በርስ ግንኙነትን አንድ ብለን የምንለማመድባቸውና ለግንኙነቶቻችን አወንታዊም ይሁን አሉታዊ ሚና ያላቸው ቤተሰብና ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ሰብዕናችንን ከመገንባት አንፃር የማይናቅ ድርሻ ያበረክታሉ፡፡ ቤተሰብ በሚለው መዋቅር ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙትም ሆነ ግዙፉን ኃላፊነት የሚወጡት ወላጆች ናቸው፡፡ ምናልባትም በስጋ ወላጆች

/biologyical/ ለማደግ ያልቻለ ህፃን አሳዳጊዎች ይህንን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ በዚህ ሂደት የሚፈጠሩ የወላጅና የልጅ ብሎም አብረው የሚኖሩ የሌሎች ቤተሰቦች ግንኙነቶች እለት በእለት እያደጉ ከአካላዊና ከውስጣዊ ሰብእናችን ጋር በመቆራኘት ለሚኖረን ሁለንተናዊ ማንነት ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ከቤተሰብ አለፍ ያለው ግንኙነት ገደብ እስካልተበጀለት (ክልከላ) ድረስ በአካባቢያችን የሚገኙና አብረውን የሚኖሩ ፍጡራንን የሚያካትት ነው፡፡

እነዚህ ፍጡራን በአንድም ሆነ በሌላ ለመኖር የሚያስፈልጉን ናቸው፡፡ ከመጀመሪያው ደረጃ ግንኙነት ቀጥሎ የሚመጡት እነዚህ ግንኙነቶች "ማህበረሰብ" በሚለው ማዕቀፍ ውስጥ የሚጠቃለሉ ግንኙነቶችን የሚይዝ ነው፡፡ ይህ ግንኙነት ደግሞ በየትኛውም የዓለም ጥግ በሰዎች የህይት ዘመን በሙሉ የማይሸሹት አብሮነት ነው፡፡ Jilmarie Murephy የተባሉት አሜሪካዊቷ ተመራማሪ Attachment, Place, and Otherness in Nineteenth-Century American Literature/ በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ይህንን ሀሳብ በስፋት ገልፀውታል፡፡

> "...ሰዎች ፈልገውም ይሁን ሳይፈልጉ ኑሯቸው በሌሎች ፍጡራን የታጠረ ነው፡፡ በጓደኞች፣ በጎረቤቶች፣ በፍቅር አጋሮች፣ በተማሪዎች እና በአስተማሪዎች፣ በሰዎች እና እንስሳት፣ በስራ ባልደረቦች፣ በግለሰቦች፣ ስለተፈጥሮና ፈጣሪ ባላቸው ጽንሰ-ሀሳብ ወዘተ. ስፍር ቁጥር በሌላቸው ሌሎች ግንኙነቶች በአጠቃላይ ሙሉ ህይወታቸውን ከሌሎች ጋር ይጋሩታል።..." (Murephy,2018, 3)

በቤተሰባዊው ብሎም በማህበረሰባዊው ትስስር ውስጥ እየዳበሩ የሚሄዱት አወንታዊ እና አሉታዊ ግንኙነቶች የሰው ልጅ በህይወት ዑደቱ ውስጥ ከሌሎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ላይ ተጽእኖ የማሳደር አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው ፕሮፌሰር Murephy ገና ስንወለድ ጀምሮ በቤተሰብና በማህበረሰብ እየታሸ ያደገው ግንኙነት በቀሪው ዘመናችን አብሮን የሚጓዝና ሰብዕናችንን ከመገንባት አንፃር ትልቅ ድርሻ እንዳለው ያስረዳሉ፡፡

> "...የመጀመሪያ ደረጃ ግንኙነት በተለምዶ በጨቅላ ሕፃናት እና በወላጆች (ወይም በአሳዳጊዎች) መካከል ጥልቀት ያለው ትስስር የሚፈጥር ነው፡፡ እነዚህ ግንኙነቶች በአንድ ሰው የህይወት ዘመን በሙሉ ለሚፈጠሩት የእርስ በርስ ግንኙነቶች መሠረት ሆነው ያገለግላሉ። በወላጆችና በህፃናት መካከል የሚዳብሩ አወንታዊ እና አሉታዊ ግንኙነቶች በህፃኑ የህይወት ዑደቱ ውስጥ ሙሉ በሙሉ

አሻራቸውን በማተም ለስኬቱና ለውድቀቱ መነሻ ይሆናሉ፡፡…"
(Murephy,2018, 3)

በዚህ ግንኙነት ውስጥ ህፃናት ሙሉ እምነታቸውን የሚጥሉበት፣ በአግባቡ ያልተረዱት ዓለም የሚፈጥርባቸውን የእንግድነትና የፍርሀት ስሜት የሚሸሸጉበት ጥግ አድርገው የሚቆጥሩት የቤተሰባቸውን ከለላ ነው፡፡ ከቤተሰባቸው እያንዳንዱ አባል ጋር ያላቸው ቁርኝት ወይም የሚፈጥሩት ትስስር በሚኖረው ውጤት ልክ አካላዊና ስነልቦናዊ ሰብእናቸው እየተገነባ ይሄዳል፡፡ በትክክለኛው ሁኔታ ለመሄድ የቻለ የወላጅና የህፃናት ግንኙነት የተቃና ሰብእና ባለቤት እንዲሆኑ እድል ሲፈጥር የተዛባ ግንኙነት ደግሞ ህፃናቱን ለተጣመመ ማንነት ይዳርጋቸዋል፡፡

በዚህ የእድሜ ክልል አንዳንዴ በሰዎች ላይ የሚከሰቱ ተፈጥሯዊም ሆኑ ሰው ሠራሽ አጋጣሚዎች በሰብዕና ግንባታ ሂደት ውስጥ ተጨማሪ ምክንያት ሆነው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ አጋጣሚዎች በሰዎች ላይ ጥለውት የሚያልፉት አካላዊ ጉዳት ካለና ለዚህ ጉዳት ቤተሰብና ማህበረሰብ የሚሰጡት ምላሽ የልጆች ስነልቦናዊ እድገት ቅርፅ እንዲይዝ ያደርጋል፡፡

ይህንን ነጥብ ከማህበረሰባችን ተለምዶ አንፃር ስናየው በርካታ አሳዛኝ ሁኔታዎችን ማግኘት ይቻላል፡፡ ምናልባትም የህፃናቱ ጉዳቶች የአእምሮ እድገት ውስንነት፣ የማየት ችግር፣ የመስማትና የመናገር ችግር፣ የእግርና የእጅ ጉዳት ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ክስተቶች የተለየ ተአምር እንደሆኑ አድርጎ በማሰብ አጋጣሚውን ቤተሰቡ ላይ እንደመጣ የፈጣሪ ቁጣ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ችግሩ የደረሰባቸውን ህፃናት ወደ ህክምና ወይንም ለዘላቂ ህይወታቸው መፍትሄ ሊሆን ወደሚችል አማራጭ ከመውሰድ ይልቅ በህፃናቱ የማፈርና የመሸማቀቅ ዝንባሌ በቤተሰብ ይስተዋላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ተጎጂዎቹን ከቤት ውስጥ እንዳይወጡ የማድረግ፣ ከሰው የማሸሸ፣ ከቤተሰባዊም ሆነ ከማህበራዊ እንቅስቃሴዎች የማግለል ድርጊቶች ይፈጸሙባቸዋል፡፡ ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ስለሚደረግ በእድሜያቸው ልክ ሊያገኙ የሚገባቸውን እውቀት እንዳያገኙ ይሆናሉ፡፡ ምንም ነገር ማሳካት እንደማይችሉ እንዲሰማቸው የማድረግ ወዘተ. በደሎች በቤተሰቦቻቸው ይፈፀሙባቸዋል፡፡

ምናልባትም እነዚህ ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው ወጣ ብለው በአካባቢያቸው የመንቀሳቀስ እድል ከገጠማቸው አብዛኛውን ጊዜ የሚያጋጥማቸው ከቤተሰባቸው የባሰ እንጂ የተሻለ የሚባል ሁኔታ አይደለም፡፡ ባለባቸው አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት የተነሳ ከእኩዮቻቸው እኩል

የመንቀሳቀስ፣ /ተሯሩጦ የመጫወት፣ ት/ቤት የመሄድ፣ በእድሜያቸው ልክ ሥራን ያለማከናወን/ ችግር ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የአካባቢ ኗሪዎች ይህን ችግራቸውን ተረድቶ ወደ መደበኛ ሁኔታ እንዲመጡ ከመርዳት ይልቅ ከላይ በቤተሰብ ከሚደረገው ተጽእኖ በባሰ ሁኔታ ህፃናቱ ላይ ጫና የመፍጠር ዝንባሌ ይስተዋላል፡፡

"Perceptions and experiences of stigma among parents of children with developmental disorders in Ethiopia" በሚል ርእስ እነ ቤተልሄም ተኮላ Social Sience and Medicine በተባለ መጽሔት ላይ በአዲስ አበባና በቡታጅራ ከተሞች ላይ የችግሩ ተጠቂ ወላጆችን በማነጋገር በ2020 ባወጡት የጥናት ጽሑፍ ላይ ይህ ማህበረሰባዊ ተፅእኖ ህፃናቱን ብቻ ሳይሆን ወላጆችንም በርካታ ችግር ውስጥ እየከተተ ስለመሆኑ በስፋት አቅርበዋል፡፡

> "…በርካታ አካላዊ ጉዳት ያለባቸው ህፃናት ጉዳታቸው ውስን ሆኖ ባላቸው ትክክለኛ ሁኔታ እንዳይጠቀሙ አንዳንድ ወላጆችና ማህበረሰቡ እንቅፋት ይሆኑባቸዋል፡፡ በልጆቻቻቸው ጉዳት የሚያፍሩ ወላጆች ወደ ማህበረሰቡ እንዳይቀላቀሉ ሲያደርጓቸው፤ ደፍረው የወጡትን ወላጆች ደግሞ ትክክለኛ ያልሆነው ማህበረሰባዊ ምላሽ በልጆቻቸው ላይ ቤት እንዲቆልፉ ያስገድዳቸዋል፡፡ … ህፃናቱ ትክክለኛ የሚባሉ ድርጊቶችን ሲፈፅሙ ከማበረታታት ይልቅ የማሸማቀቅ ሁኔታ በጥናታችን በስፋት ታይቷል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ጉዳት ላለባቸው ህፃናት ትምህርትን ጨምሮ ሌሎች ድጋፎችን የሚሰጥ ተቋም የለም በሚባል ደረጃ ስለሆነ ያለው ህፃናቱ በእውቀትና በክህሎት እንዲደገፉ ሆነው አያድጉም…ይህ ሁኔታም ህፃናቱንና ወላጆቻቸውን ለዘርፈ ብዙ ችግር እንደሚዳርጋቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡" (እነ ቤተልሄም፣ 2020)

ተጎጂ ህፃናት በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ ውስጥ ካገኟቸው ሰዎች እኩል ነን ብለው ስለማያስቡ በራሳቸው መፈጸም የሚችሏቸውን ጥቃቅን ነገሮች ሁሉ ለማከናወን የሌሎችን ይሁንታ ይጠብቃሉ፡፡ በትምህርትና በክህሎት የዳበረ አስተዳደግ ስለማይኖራቸው በስነልቦናም ሆነ በሁለንተናዊ ዕውቀት ተወዳዳሪ ሆነው ይህን ዓለም አይጋፈጡም፡፡ በትውልድ አካባቢያቸውም ሆነ ከዛ አለፍ ብለው ለሚያገኙት የማህበረሰብ ክፍል የሚኖራቸው ምላሽ ፍርሀት፣ ስጋት፣ ስንፍና፣ ቁጣና ጥላቻ ወዘተ. ናቸው፡፡ ይህ ሂደት ያዳበረባቸው ያለመቻል ስሜት ከቤተሰብ መለያየ እድሜያቸው ላይ ሲደርስ ለመኖር ሲሉ የማይመረጥ ሁኔታ ውስጥ እዲገቡ ያደርጋቸዋል፡፡ የሚያውቁትንና የለመዱትን ነገር ግን

ተገቢ ምላሽ ያልሰጣቸውን ቤተሰብና ማህበረሰብ ትተው ርቀው ይኳዛሉ፡፡ ርቀው ተጉዘውም የሚገቡበት ስለሌላቸው ለልመና፣ ለጎዳና ተዳዳሪነት ወይንም ትኩረታችን ለሆነው የሰው ቤት አገልጋይነት ይዳረጋሉ፡፡

### 2.1.3.4. የትውልድ ቦታን መልቀቅ /መሰደድ/

አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሀገራችን ድህነት በተለይም የገጠሩ ማህበረሰብ ድህነት መጠኑ ጨምሯል። በተለይ ወጣት ሴቶች ሥራ ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ከፍተኛ ገቢ ወዳላቸው አገሮች ይሰደዳሉ። በተጨማሪም በተለያዩ ኋላ ቀር አስተሳሰቦችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ምክንያት ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና መኖር በርካታ ዜጎች ልጅነታቸውን ሳይጨርሱ አካባቢያቸውን በመልቀቅ ለሰው ቤት አገልጋይነት እንዲዳረጉ መነሻ ይሆናሉ፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው Marina de Regt and Felegebirhan Belesti የተባሉት ጥናት አቅራቢዎች በገፅ 2 ላይ ይህንን ሀሳብ በስፋት ይዳስሱታል፡፡

> “በኢትዮጵያ ያለው የዜጎች የስደት ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው ስደት ጋር በእጅጉ የተቆራኘና ቁጥሩም ከፍ ያለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ውጭ ሀገራት ከሚሰደዱት ዜጎች ይልቅ በሀገር ውስጥ ከቦታ ቦታ የሚፈልሱ ሰዎች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ የውስጥ ስደተኞች በበርካታ ምክንያቶች ከቤታቸውና ከአካባቢያቸው ለመሰደድ ይገደዳሉ፡፡ ከምክንያቶቹ መካከል ድህነት፣ ያለ እድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ የትምህርት እጦት፣ በርካታ ጨቋኝ የስርዓተ-ፆታ ድርጊቶች ሲሆኑ፣ እድሉን ሲያገኙ ብዙ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ከነዚህ ጫናዎች ለመላቀቅ የትውልድ ቦታቸውን ለቀው ለስደት ይዳረጋሉ።” (Marina and Felegebirhan, 2017,2)

አንዳንዴም ከተማ ያሉ ዘመዶቻቸው እናስተምራችኋለን ስለሚሏቸው እነሱን ተከትለው አካባቢያቸውን ይለቃሉ፡፡ ዓላማ ብለው የወጡት በተለያየ መንገድ የሰው ቤት አገልጋይነትን ይቀላቀላሉ፡፡ ዘመዶቻቸውን የተጠጉት ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚገጥማቸው ህይወት የተገባላቸውን ቃል ያክል ስለማይሆን ከአስጠጓቸው ቤተሰቦች በመሸሽ የሰው ቤት አገልጋይነትን ይቀላቀላሉ፡፡

ተሰዳጅ ግለሰቦች በተወለዱበትና ባደጉበት አካባቢ የሚያዳብሯቸው የኔ ብለው የሚይዟቸው በርካታ አካባቢያዊ ልምዶች አሏቸው፡፡ እነዚህ ልምዶች ደግሞ በአካላዊ፣

በአእምሯዊና በስነልቦናዊ እድገታቸው ዙሪያ የየራሳቸውን አሻራ ስለሚያሳርፉ ስደት ሲወጡም ተሸክመዋቸው ይጓዛሉ፡፡

ቦታ ወይንም አካባቢ ብለን የምንጠራቸው ቤቶች፣ ሕንፃዎች፣ ሰፈሮች፣ መሬቶች፣ የተለያዩ የውሀ አካላት፣ ተራራዎች ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በነዚህ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ የመኖሪያ ክልሎች ውስጥ የአካባቢውና የማህበረሰቡ ብቻ የሆኑ ወደ ሌላ ቦታ ቢኬድ ሊከናወኑ የማይችሉ ሁለንተናዊ ልምዶች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ልምዶች በኗሪዎቹ ውስጥ ዘልቀው በመቆየት ሰዎች ከቦታዎች ጋር ጥልቅ ስሜታዊ ትስስር እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡ የቦታና የጥልቅ ስሜት ትስስሩ አካባቢያቸውን ጥሎ የመሄድ ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም ከውስጣቸው በቀላሉ ሊፋቁ የማይችሉ ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ከቦታ ጋር ያለው ትስስር በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ ዘልቆ የሚገባ ብቻ ሳይሆን ብዙውን ጊዜ በአኗኗር ዘይቤዎቻችንና አመለካከቶቻችን ውስጥም የሚታይ ነው፡፡ Maria Vittoria Giuliani “Theory of Attachment and Place Attachment” በተባለ ሥራቸው ውስጥ ይህን ሀሳብ ያብራሩታል፡፡

> “...የሰው ልጅ ተወልዶ ያደገበት አካባቢ የቦታ አቀማመጥ በዕለት ተዕለት ህይወቱ ውስጥ አብሮ የሚቆይና ሲለቁት የሚረሳ ሳይሆን በየትኛውም ጊዜና ቦታ አብሮት የሚኖር ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሀሳቦች በሥነ-ጥበብ ውጤቶች ተወክለው ሲገለፁ ይታያል፡፡ ይሁን እንጂ የቦታና የስሜት ትስስር በሕይወታችን ውስጥ በስነጥበብ ውጤቶች ከሚገለፀውም በላይ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡...” (Giuliani,2003,7)

ሰዎች ከአካባቢያቸው የወረሱትን ልማድ በቀላሉ ከውስጣቸው ማስወገድ ስለማይችሉ በእያንዳንዱ የህይወት እንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ ሁሉ አብሯቸው እንዲዘልቅ ያደርጋሉ፡፡ በቀላሉ ማስወገድ የማይቻልን አካባቢያዊ ልማድ ይዞ ወደ ሌላ አካባቢና ማህበረሰብ ውስጥ ሲገባም ከፍተኛ የሆነ የእንግድነት ስሜት ይፈጠራል፡፡ በተለይም ለመኖር በሁለንተናዊ መልኩ የሌሎችን ድጋፍ የሚሹ ሰዎች አካባቢያቸውን ሲቀይሩ የሚያጋጥማቸው ችግር የጎላ ይሆናል፡፡

በልማዳዊ አስተሳሰብና በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ተጎጂዎች ደግሞ ከነችግሩም ቢሆን ቤተሰባቸውንና አካባቢያቸውን ለችግራቸው መጠለያ አድርገው ቆይተዋል፡፡

በመሆኑም አዲሱን አካባቢ ለመለማመድ የሚወስድባቸው ጊዜ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ተጎጂዎቹ ጉዳታቸውን ሲያስታምሙበት የነበረውን አካባቢ የሚረዱት አፈር፣ ድንጋይ፣ ሜዳ፣ ተራራ፣ ወንዝና ሽንተረር ወዘተ. መሆኑን ብቻ ሳይሆን የነሱ መጠለያም እንደሆነ ጭምር ነው፡፡ ለሚሰማቸው ስሜት ሁሉ መደበቂያ የሚያደርጉት ስለአካባቢያቸው ያላቸውን ፍቅርና ትዝታ ነው፡፡

ሁሉም አካባቢዎች ወደ ሰዎች የሚያጋቧቸው ስሜታዊ ትስስሮችን ከአካባቢው መልቀቅ ቢቻል እንኳን በቀላሉ ለማራገፍ በሚችሉበት ሁኔታ አይደለም፡፡ አንድ ቦታ ከጂኦግራፊያዊ ተፈጥሮው ባሻገር በነዋሪዎቹ ውስጥ ያሉ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን፣ ሃይማኖታዊ ትውፊቶችን ባህላዊና ልማዳዊ የሆኑ ማህበራዊ ስርዓቶችን አቅፎ የያዘ በመሆኑ ከነዋሪዎቹ ጋር ጥልቅ ቁርኝት አለው፡፡ ይህ ቁርኝት ከአካላዊ ቁርኝትም ይበልጥ ስነልቦናዊ በመሆኑ ቦታን በአካል ለመልቀቅ አስገዳጅ ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን ከውሰጥ ማስወገድ አይቻልም፡፡ የስነልቦና ባለሙያው Kay, Jerald. “Attachment and Its Disorders,” በሚለው መጽሐፉ የገለፀበት ሁኔታ አለ፡፡

> “ቦታዎች ለዓለማችን ከሚለግሱት ተፈጥሯዊ ውበትና ከመልክአ ምድራዊ ቅንጅቶችነታቸውም በላይ ከሰዎች ጋር ትክክለኛ አካላዊ እና መንፈሳዊ ትስስር ያላቸው በማህበራዊ ግንኙነቶችም ላይ ጥላቸውን የሚያሳርፉ ጥልቅ ትዝታዎች ናቸው፡፡” (Jerald,2012, 274)

በተለያዩ ምክንያቶች አካባቢያቸውን ለቀው ለስደት የሚዳረጉ ሰዎች በስፋት የሚጠብቃቸው የሰው ቤት አገልጋይነት ነው፡፡ ስደት ያደረሳቸው ቦታ ላይ ሲሆኑም አዲሱን ቦታ በቀላሉ ለመልመድ ይቸገራሉ፡፡ በቀላሉ አለመልመዳቸው ደግሞ ከአሰሪዎቻቸው ጋር እንዳይግባቡ በማድረግ ህይወታቸውን እንዲከብድ ያደርገዋል፡፡

### 2.2. ፅንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፎች /Conceptual background/

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የተወሰኑ ነጥቦችን የማነሳው ስለገጸባህሪ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ዙሪያ ማብራሪያ የምሰጥበት ምክንያት አገልጋይ ገጸባህሪያት የሚቀረፁት በዚህ ስነጽሁፋዊ መስፈርት ስለሆነና ማብራሪያ የሚሰጥባቸውን አገልጋይ ገጸባህሪያትንም ከዚህ ነጥብ አንፃር መመልከት አስፈላጊ ነው ብዬ ስላመንኩ ነው፡፡

### 2.2.1. የአገላጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብ

በፈጠራ ስራዎች ውስጥ ገጸባህሪያት እንዴት ይቀርባሉ ብለን ስንጠይቅ ርቱእ (ዘርዛሪ) እንዲሁም ኢ.ርቱእ (ተውኔታዊ) በሚባሉ ሁለት ዘዴዎች ሊቀርቡ እንደሚችሉ ዘሪሁን አስፋው ያስረዳሉ፡፡

> "ርቱእ አቀራረብ ገጸባህሪያቱን በቀጥታ በመግለፅ ወይም በመተንተን የሚያቀርብ ሲሆን ገጸባህሪያቱ ምን እንደሚመስሉ ተራኪው ወይም ደራሲ ቆሞ የሚታዘብ ገጸባህሪ ይነግረናል፡፡ በዚህ አይነቱ ዘዴ በአብዛኛው የገጸባህሪያቱ አካላዊና ህሊናዊ መልክ በዝርዝር ይገለፃል፡፡... ኢ.ርቱእ ወይም ተውኔታዊ አቀራረብ ገጸባህሪውን በድርጊት ያሳያል፡፡ ከገጸባህሪው አመል፣ ንግግር፣ አስተሳሰብና አመለካከት ሰብእናውን ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር ያለውን ግንኙነት መገንዘብ እንችላለን፡፡ ... በኢ.ርቱእ ዘዴ ከቀረቡ መልካቸውንም ሆነ ሰብእናቸውን ለማወቅ አይከብድም፡፡..." (ዘሪሁን፣2012፣167-169)

ይህንን ሀሳብ Perrine Laurence እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2016 ለ13ኛ ጊዜ ባሳተመችው LITERATURE STRUCTURE, SOUND & SENSE በሚለው መፅሐፏ በዝርዝር ያስቀመጠችበት ሁኔታ አለ፡፡ በተጠቀሰው መፅሐፍ ውስጥ ከገፅ 144 ጀምሮ የልቦለድ ገጸባህሪያት አቀራረብ "flat/ ርቱእ" or "round/ ኢ.ርቱእ" እንደሆነ ትጠቁምና እነዚህን ገጸባህሪያት በዘርዛሪ ዘዴ ወይንም በድርጊቶቻቸው ማወቅና መረዳት እንደሚቻል ታብራራለች፡፡

> "...የልቦለድ ገጸባህሪያት ቀጥተኛ ወይም ውስብስብ ባህሪ ያላቸው ሆነው ነው የሚቀርቡት፡፡ ቀጥተኛ /ርቱእ/ ብለን የምንጠራቸው ገጸባህሪያት በግልፅ የሚታወቁና የብዙዎችን የጋራ ባህሪ የተላበሱትን ነው፡፡ በተከሰቱበት ቅፅበት ስለነሱ ሰብእና ለማስረዳት የማያስቸግሩ ናቸው፡፡... በተቃራኒው ውስብስብ ገጸባህሪያት /ኢ.ርቱእ/ በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ ለማለፍ የሚገደዱና ብዙ ጎኖች ያሏቸው ሲሆኑ፣ እነዚህን ገጸባህሪያት እንዲህ ናቸው ብሎ ለማብራራት በድርጊቶቻቸውና በንግግሮቻቸው ውስጥ እንዲሁም ሌሎች ገጸባህሪት ስለነሱ በሚናገሩት ዙሪያ ሰፊ ግንዛቤ መጨበጥ ያስፈልጋል፡፡..." (Laurence, 2016,144-146)

### 2.2.2. የአገልጋይ ገጸባህሪያት አይነት

በፈጠራ ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸው ገጸባህርያት ሁለት አይነት መሆናቸውን ዘሪሁን አስፋው ይገልፃሉ፡፡ (ዘሪሁን፣ 2012፣ 171-172) ፈረጀ ብዙና ፈርጃንድ፡፡ የልቦለድ ታሪክ ማጠንጠኛ የሚሆኑትና በብዙ ምእራፎች ውስጥ የምናገኛቸው ፈርጀ ብዙ ገጸባህሪያትን ነው፡፡ እነዚህ ገጸባህሪያት ልዩ ልዩ ጸባዮችና ብዙ የህይወት ልምዶች የታጨቀባቸው ሆነው ስለሚቀረጹ ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር ያላቸው ግንኙነት የሰፋ፣ መውደቅ መነሳት የበዛባቸው፣ በቀላሉ ለስኬት የማይበቁ ተደራሲ በቀላሉ የማይረዳቸውና እንደሚገኙበት ሁኔታ ተለዋዋጭ ባህሪን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ደራሲው እንደየአስፈላጊነቱ የእነዚህን ገጸባህሪያት ማንነት እየዘረዘረ ለመሄድ ካልቻለ እነሱን በቀላሉ ማወቅ አይቻልም፡፡ የነዚህ ተቃራኒ የሆኑት ፈርጃንድ ገጸባህሪያትን በቀላሉ ለማወቅ ይቻላል፡፡ በልቦለድ ውስጥ ስፍራ የሚሰጣቸው የአጃቢነት ሲሆን እነሱን ለማወቅ የሚያጓጓ ሰብእና አይኖራቸውም፡፡ በተከሰቱበት ቅጽበት እንዲህ ናቸው ተብለው የሚገለጹና ውስብስብነት የሌላቸው ናቸው፡፡

### 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር ከጥናት ሥራው ጋር በአንድም በሌላም ቁርኝት ያላቸው ሌሎች የመመረቂያ ጽሑፎች ከዚህ ሥራ ጋር ያላቸው አንድነትና ልዩነት እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ይብራራል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚገኙ ቤተመጻህፍት ውስጥ ከኔ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው የመመረቂያ ጽሑፎችን ለማግኘት ብዙ ሞክሬያለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ለማግኘት የቻልኩት አንድ ብቻ ነው፡፡ “የአገልጋይ ገጸባህሪያት ጥናት ከ1966-1975 ዓ.ም በወጡ የአማርኛ ልቦለድ መፃህፍት ውስጥ” የሚለው ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል በ1976 ዓ.ም የቀረበ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ብቻ ነው፡፡

የዚህ መመረቂያ ጽሁፍ አቅራቢ ስማቸው አለሙ ሲሆን ጥናቱ በአጠቃላይ 61 ገጾች ያሉት ነው፡፡ ስማቸው በጥናቱ ያተኮረባቸው ልቦለዶች ከዚህ በታች የተጠቀሱት ናቸው፡፡

| ደራሲው | አርእስት | የታተሙበት ዓ.ም. እ.ኢ.አ |
|---|---|---|
| በአሉ ግርማ | የህሊና ደወል | 1966 |
| ገብሬ አድማሱ | እያወቁ ማለቅ | 1968 |
| ግርማ ወንድሙ | የውቢቱ ጣጣ | 1968 |
| በዓሉ ግርማ | ደራሲው | 1972 |
| በዓሉ ግርማ | የቀይ ኮከብ ጥሪ | 1972 |
| ብርሀኑ ዘሪሁን | ማዕበል የአብዮት መባቻ | 1973 |
| ሀዲስ አለማየሁ | ወንጀለኛው ዳኛ | 1974 |
| ለማ መንገሻ | ድርብ ልሳን | 1974 |

በስማቸው ማብራሪያ መሰረት በእነዚህ ስምንት ልቦለዶች ውስጥ ስድስት ሴት እንዲሁም ሶስት የወንድ በአጠቃላይ ዘጠኝ አገልጋይ ገጸባህሪያት አሉ፡፡ ከ"የህሊና ደወል" ቶሎሳ፣ ከ"እያወቁ ማለቅ" እማማ አንኮዬ /ሰው ባጣ/ እና ወለቱ፣ ፣ ከ"የውቢቱ ጣጣ" ፍቅርተ፣ ከ"ደራሲው" ውባንቺ፣ ከ"የቀይ ኮከብ ጥሪ" ደርቤ፣ ከ"ማዕበል የአብዮት መባቻ" ዘይኔ፣ ከ"ወንጀለኛው ዳኛ" ጣሰው እንዲሁም ከ"ድርብ ልሳን" ኑኑዬ ናቸው፡፡ እነዚህን ገጸባህሪያትም ከገጸባህሪያት አቀራረብ አንጻር አጥንቷቸዋል፡፡ ይህ ጥናት ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር ከኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ስለሚቀራረብ ከሁለት ነጥቦች አንፃር እመለከተዋለሁ፡፡

የስማቸው ዓለሙን ጥናት የተመለከትኩት ከቅርጽና ይዘት አኳያ ከኔ ጥናት ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት ነው፡፡ ይህ ጥናት ስድስት ክፍሎች ያሉት ነው፡፡ መግቢያ፣ ምእራፍ አንድ፣ ምእራፍ ሁለት እና ምእራፍ ሶስት፣ የግርጌ ማስታወሻ፣ በ10 ዓመታት የወጡት ልቦለድ መፃህፍት ዝርዝሮችና ዋቢ መጻህፍትን በማቅረብ ጥናቱን አጠቃሏል፡፡

ስማቸው መግቢያ በሚል ርእስ ስር ሰባት ነጥቦችን ያሰፈረ ሲሆን ለጥናቱ ያነሳሱትን ምክንያቶች፣ የጥናቱን ጠቀሜታዎች፣ ለምርምር ርእሱ የመረጣቸውን መጻህፍትን መጠንና የማንበብ ሂደቱን በተመለከተ የተከተላቸውን ሂደቶች ጠቅሷል፡፡ ትኩረት ባደረገባቸው

አስር አመታት ውስጥ ከታተሙት ልቦለድ መጻህፍት መካከል ስምንቱን ለይቶ ያጠናበትን ምክንያትም አብራርቷል፡፡ ስማቸው መግቢያውን ከማጠቃለሉ በፊት የጥናቱን አጠቃላይ ይዘትና በጥናት ሂደት ከልቦለዶቹ ውጭ የአገልጋይ የህብረተሰብ ክፍሎችን ዳራ የሚጠቁም ጸሑፍ አለማግኘቱ ችግር እንደሆነበት ጠቁሟል፡፡

ከመግቢያው ቀጥሎ በሰፈረው ምዕራፍ አንድ ላይ "በልቦለዱ ውስጥ የታዩት አገልጋይ ገጸባህሪያት ከገጸባህሪ ጥናት አንፃር" የሚል ርእስ ያለው ትንታኔ ቀርቧል፡፡ በዚህ ርእስ ስር "ገጸባህሪ" ሚለው ቃል ትርጉም ምን እንደሆነና በተለያዩ ጸሀፊዎች ልዩ ልዩ ስያሜ እንደሚሰጠው አብራርቷል፡፡ የገጸባህሪያት ድርሻ በእድሜ፣ በጾታና በትምህርት ዝግጅት ወዘተ. ገደብ የተበጀለት መሆኑን ይጠቅስና "የተዋጣለት ገጸባህሪ አሳሳል የምናገኘው በታዋቂ ደራሲያን የፈጠራ ጽሁፍ ውስጥ ነው…(ስማቸው፣ 1976፣ 4)" የሚል መደምደሚያ ሰጥቶ ያልፋል፡፡

በዚህ ክፍል ገጸባህሪ መሆን ስለሚገባው ንድፈ ሀሳባዊ ማብራሪያ ይሰጥና ያቀረበውን ማብራሪያ ሊያጠነክርለት የሚችል ማስረጃ ከተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ መርጦ ያሳያል፡፡ በዚህም ገጸባህሪያት የተሳሉበትን ማህበረሰብ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ማሳየት እንዳለባቸው ያስረዳና ማስረጃ እንዲሆነው ከተጠቀሱት ልቦለዶች ውስጥ ምሳሌ ይሆናሉ የሚላቸውን ገጸባህሪያት ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም የገፀባህሪያት እንቅስቃሴ በተጨባጭ የሆነ ሳይሆን ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብ መሆኑን በማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የገጸባህሪያትን ፍፃሜ ከድርጊታቸው፣ ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር ባላቸው ግንኙነት፣ በደራሲው ትረካ ወዘተ. ለማወቅ እንደሚቻል ያስረዳል፡፡

ስማቸው በዚሁ ምእራፍ ውስጥ የገጸባህሪ አይነቶች ሁለት መሆናቸውን ጠቁሞ ወጥ ገጸባህሪና አስተኔ ገጸባህሪ እንደሚባሉ ያብራራል፡፡ በማብራሪያውም ወጥ ገጸባህሪያት ውስጣዊ ገጽታቸው የሰፋ፣ ችግሮቻቸው የበዙና የተንዛዙ፣ ፀባያቸው እንዲህ ነው ብሎ ወዲያውኑ ለመወሰን የሚያስቸግርና የፀባይ መለዋወጥ ስለሚታይባቸው አንድ ጊዜ መጥፎ፣ ሌላ ጊዜ ጥሩ የሚባል ባህሪ እንዳላቸው ያስረዳል፡፡ አስከትሎም በተመረጡት ስምንት መጽሀፍት ውስጥ ከሚገኙ ዘጠኝ አገልጋይ ገጸባህሪያት መካከል ይህን አይነት ገጸባህሪ እነደሆነ መጥቀስ የሚቻለው የቀይ ኮከብ ጥሪ ገጸባህሪ የሆነውን "ደርቤ"ን ብቻ ነው በማለት ይጠቅሳል፡፡

በስማቸው ማብራሪያ መሰረት አስተኔ ገጸባህሪያት በማንኛውም ጊዜ ማንነታቸውን ለማስታወስ ያመቻሉ፡፡ ድርጊታቸውና እንቅስቃሴያቸው ውስብስብ አይደለም፡፡ አንድ የተወሰነ ባህሪ ብቻ ጎልቶ ይታይባቸዋል፡፡ ያንን የጎላ ባህሪያቸውን ብቻ ይዘው በትረካው ውስጥ ይዘልቃሉ፡፡ ለዚህም ከልቦለዶቹ ውስጥ የተመረጡት ስምንት ገጸባህሪያት በሙሉ በዚህ ስር የሚጠቃለሉ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡

በምዕራፍ ሁለት "የአገልጋይ ገጸባህሪያቱ ውጫዊና ውስጣዊ ገጽታዎች" በሚል ርእስ ስር ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከማስረዳት ይጀምራል፡፡ በማስከተልም ትንታኔ ከሚሰጥባቸው ገጸባህርያት መካካል የሁለት ገጸባህሪያትን ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታቸውን ከድርሰቶቹ ለማግኘት ስላልተቻለ ከገጸባህሪያቱ ድርጊትና ከሚናገሩት ጥቂት ቃላት መነሻነት ማንነታቸውን ለመግለጽ መሞከሩን ይናገራል፤ የውባንቺ፣ ዘይኔ፣ እማማ አንኮዬ /ሰው ባጣ/፣ ወለቱ፣ ፍቅርተ፣ ኑኑዬ፣ ደርቤ፣ ቶሎሳ እና ጣሰው ማንነታቸው የተብራራላቸው ዘጠኝ ገጸባህሪያት ናቸው፡፡

በምእራፍ ሶስት የቀረበው አቢይ ርእስ "ገጸባህሪያቱ የሚወክሉት የማህበረሰብ ክፍል" የሚል ነው፡፤ በዚህ ክፍል እነዚህ ገጸባህሪያት በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ቦታ ምን እንደሚመስልና ማንን ወክለው እንደቀረቡ በታሪኩ ውስጥ ከተሳሉበት ዘመን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለማሳየት ጥረት እንደተደረገ ስማቸው ይገልጻል፡፡ አራት ንኡሳን ክፍሎች ባሉት በዚህ ምእራፍ ገጸባህሪያቱን ለአገልጋይነት የዳረጓቸውን ምክንያቶችና አሰሪዎቻቸው እነሱን የሚይዙበትን ሁኔታ በስፋት ይተነትናል፡፡

"ተፈጥሮ ባደረስባቸው ችግር ምክንያት ወደ እማይመኙት የህይወት ገጽታ የገቡ ገጸባህሪያት" በሚል ንኡስ ርእስ ከ"ደራሲው" ውባንቺን እንዲሁም ከሶስቱ ማእበሎች ዘይኔን ምሳሌ በማድረግ ለማሳየት ይሞክራል፡፡ ሁለቱ ገጸባህሪያት የድርቅ ችግር ከተከሰተበት የወሎ ክፍለ ሀገር ተሰደው ለሰው ቤት አገልጋይነት መዳረጋቸውንና በሚኖሩበት ቤት ውስጥም የሚገጥማቸውን በጎና ክፉ አጋጣሚ እንዲሁም የኖሩበት ማህበረሰብ የሳደረባቸውን ተጽእኖ ጭምር አብራርቶ አቅርቧል፡፡ በማስከተልም የሁለቱን ገጸባህሪያት እንዲሁም የአሰሪዎቻቸውን አንድነትና ልዩነት በማስረዳት ማጠቃለያውን ያስቀምጣል፡፡ በተለይም አሰሪዎቻቸው ያላቸው የመደብ ወይንም የንቃተ ህሊና ልዩነት በአገልጋዮቹ አኗኗር ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ በዝርዝር ለማሳየት ሞክሯል፡፡

ስማቸው በሁለተኛ ደረጃ የተመለከተው በነበረው መደባዊ ስርዓት “ባርያ” ተብለው በተለየ ሁኔታ የሚታዩ ገጸባህሪያትን ነው፡፡ እነዚህ ገጸባህሪያት በአሰሪዎቻቸውም ሆነ በሌላው የማህበረሰብ ክፍል እንደ ሰው የማይቆጠሩና የትኛውም አይነት ግፍ ቢፈፀምባቸው የሚጠይቅላቸው አካል የሌላቸውን አሳዛኝ ገጸባህሪያት ናቸው፡፡ ለዚህ ማብራሪያው ማንጸሪያነት የተመለከታቸው “እንኮዬ” እና “ወለቱ” የተባሉትን ሁለት ገጸባህሪያት ነው፡፡ እነዚህ ገጸባህሪያት እንደ ከብት ወይን እንደ እቃ በስጦታ መልክ ለአሰሪዎቻቸው የተበረከቱትን እንዲሁም ወላጆቻቸው ሲያገለግሉ በነበረበት ቤት ውስጥ ለማገልገል የተሰማሩትንና አቅም ሲያጥራቸው የተወረወሩትን ገጸባህሪያት የሚወክሉ ናቸው፡፡

“የህይወት አጋጣሚ የጣላቸው” በሚል ንኡስ ርእስ ስር ሁለት ገጸባህሪያትን ተመልክቷል፡፡ እናትና አባቱን ስላጣ የሰው ቤት አገልጋይ የሆነው ደርቤ እና እናትና አባቷን አጥታ በብዙ ጥረት ሀብት ካፈራች በኋላ ያገባችው ባል አታሏት ለአገልጋይነት የተዳረገችው “የውቢቱ ጣጣ” ገጸባህሪ ፍቅርተ የዚህ ነጥብ ትኩረቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ገጸባህሪያት ወላጆቻቸውን ባያጡ ይህንን የስራ መስክ አይቀላቀሉም  ነበር፡፡ በሂደትም ደርቤ በከፍተኛ ትግል እራሱን ለውጦ የተሻለ ደረጃ ሲደርስ ፍቅርተ ግን ከአገልጋይነት ሳትላቀቅ ታሪኩ መጠናቀቁን የሁለቱን ገጸባህሪያት አንድነትና ልዩነት ለማሳየት ባቀረበው ትንታኔ ስማቸው ይነግረናል፡፡

በአራተኛ ደረጃ የተመለከታቸው “አጠቃላይ ሁኔታን የሚያሳዩ” በሚል ንኡስ ርእስ ስር ሶስት ገጸባህሪያትን ቃኝቷል፡፡ እነዚህ ገጸባህሪያት አሠሪዎቻቸው ከሚያቀርቡላቸው የእለት ከእለት ህይወት ውጭ ሌላ ያለ የማይመስላቸውና በራሳቸውም ላይ ሆነ በሌሎች ላይ የሚፈጸምን በደል ትክክል እንደሆነ የሚቀበሉ ናቸው፡፡ ትክክለኛ የሚባለውንና እነሱ ያሉበትን የጭቆና ህይወት ለማወዳደር የሚያስችል ንቃት የሌላቸው ናቸው፡፡ ቶሎሳ፣ ጣሰውና ኑኑዬ ከቀረቡባቸው አጠቃላይ ሁኔታ አንፃር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት በማስቀመጥ ትንታኔውን ያጠቃልላል፡፡

በአጠቃላይ በስማቸው ዓለሙ የተጠኑት አገልጋይ ገጸባህሪያት ከደርቤ በስተቀር ሁሉም የአጃቢነት ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ የጋራ ሁኔታቸውን ስናይም ምቹ ኑሮ ስለሌላቸው እንደሚበሳጩ፣ የሴት አገልጋዮች ቁጥር እንደሚበልጥ፣ ዘይኔ ብቻ ደመወዝ እንዳላትና ሌሎቹ ያለ ደመወዝ እንደሚገዙ ለማየት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የኑሯቸው ሁኔታ እንደሚሰጡት ጥቅምና እንደ አሰሪዎቻቸው አጠቃላይ ባህሪና የኑሮ ደረጃ እንደሚለያይ፤

በሚኖሩበት ቤት የተወሰኑ ወይንም አጠቃላይ ስራዎችን እንደሚሰሩ፤ የአመቤቶቻቸው ቅናት አገልጋዮቹን የአካል ጉዳት እስከማድረስ ብሎም እስከመግደል ሊደረስ እንደሚችልና በዚህም ተጠያቂ እንደማይሆኑ፤ ሴት አገልጋዮች ስራ እንደሚበዛባቸውና አብዛኞቹ አገልጋዮች ከገጠር ወደ ከተማ ስለመፍለሳቸው ጥናቱ አሳይቶናል፡፡

ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት ቀጥሎ የተመለከትኩት ነው፡፡ ከመነሻው በአገልጋይ ገጸባህሪያት ዙሪያ ጥናት ለማድረግ መወሰናችንና እነዚህ ገጸባህሪያት የቀረቡበትን መንገድ ማጥናታችን የጋራ ጉዳያችን ነው፡፡ ከጥናት ወረቀቶቻችን የቅርጽ አቀራረብ ልዩነት ከማስከተሉ ውጭ በገጸባህሪያት አይነትና አቀራረብ ዙሪያ ንድፈ ሀሳቦችን እያቀረበና በምሳሌ እያስደገፈ ማብራራቱ የሚያመሳስለን ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠኚዎቹን ገጸባህሪያት ከሚኖሩበት የማህበረሰብ ክፍል አንፃር ያሳየበት የምእራፍ ሶስት አቀራረቡ እኔ በምእራፍ ሁለት “ለአገልጋይነት የሚዳርጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?” በሚለው አብይ ርዕስ ስር ትንታኔ ከሰጠሁባቸው የተሻለ ህይወት ፍለጋ፣ አለመማር፣ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና፣ የትውልድ ቦታን መልቀቅ /መሰደድ/ ከሚሉት ንኡሳን ርእሶች ጋር አንድነት ያለው በመሆኑ የጥናት ስራዎቻችንን የሚያመሳስላቸው ተጨማሪ ነጥብ ነው፡፡

የስማቸው ዓለሙና የኔ ጥናት ልዩነት ትኩረት ካደረግንበት ዘመን ይጀምራል፡፡ የእሱ ከ1966 ዓ.ም እስከ 1975 ዓ.ም ባሉት አስር አመታት የታተሙ ልቦለዶች ላይ የሚያተኩር ሲሆን የእኔ ግን ከ1990 ዓ.ም እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙት የሃያ አመታት ልቦለዶች ላይ ነው፡፡ ስማቸው ልቦለዶቹን ሲመርጥ ከደራሲያን አንፃር የተመለከተው ሁኔታ የለም፡፡ የኔ ጥናት ግን በሴት ደራሲያን ስራዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡

ከላይ እንደጠቀምኩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚገኙ ቤተመጻህፍት ውስጥ ከኔ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው የመመረቂያ ጽሑፎችን ለማግኘት ስፈልግ በሴት ደራሲያን ስራዎች ዙሪያ የቀረቡ ጥቂት ጥናቶችን አግኝቻለሁ፡፡ በ1985 ዓ.ም ለባችለር ዲግሪ ማሟያ በአይናለም ጋሻው ጠና የቀረበው ጥናት የደራሲ ፀሐይ መላኩ ልቦለዶች “ቋሳ” እና “አንጉዝ” የአተራረክ ቴክኒካቸው ምን እንደሚመስል ሂስ የተሰጠበት ነው፡፡ በተመሳሳይ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ በ1998 ዓ.ም “የአተራረክ ዘዴ በሙሉወርቅ አስራት “ንቡት” ልቦለድ ውስጥ” በሚል ርእስ በመንበረ አባተ ጥናት ቀርቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ2000 ዓ.ም ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ “እንስታዊ የስነ ጽሁፍ ሂስ ከ1984-1997 በታተሙ የሴቶች

የግጥም መጻሕፍት ውስጥ” በሚል ርእስ በአዲሱ ዘገየ ጥናት ቀርቧል፡፡ እነዚህ ጥናቶችን የሴት ደራሲያን የፈጠራ ሥራዎች ከመሆናቸው ውጭ ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ምንም ነጥብ የለም፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. አገልጋይ ገፀባህርያት" ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙና በተመረጡ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ

### 3.1. አገልጋይ ገፀባህርያት"ን ወደዚህ ሙያ የመራቸው ምክንያት

በዚህ ምእራፍ ትንታኔ የሚሰጥባቸው ንኡሳን ርእሰ ጉዳዮች አራት ናቸው፡፡ የተሻለ ህይወት ፍለጋ፣ አለመማር፣ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና እንዲሁም የትውልድ ቦታን መልቀቅ /መሰደድ/ የሚሉት ናቸው፡፡ የልቦለድ ሥራዎቹን ከነዚህ ነጥቦች አንፃር ለመመርመር ሲሞከር በአንድ ገጸባህሪ ህይወት ውስጥ ሁሉም ምክንያቶች ወይንም ሁለቱ ካለበለዚያም ሶስቱ አገልጋይ ለመሆናቸው ሰበብ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በመሆኑም አገልጋይ ገጸባህሪያቱ በቀረቡበት ልክ ምክንያታቸውን በመመርመር ትንታኔ እሰጣለሁ፡፡

#### 3.1.1. የተሻለ ህይወት ፍለጋ

ከወላጆቻቸው ወይንም ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር በመሆን በሚኖሩበት ወቅት ህይወት ያልተመቻቸው አገልጋይ ገጸባህሪያት የዚህ ጥናት ትኩረት በሆኑት ልቦለድ መጻህፍት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ታዳጊዎችና ወጣቶች ካሉበት ያልተመቻቸ ሁኔታ በማምለጥ የተሻለ ህይወት ፍለጋ የሰው ቤት አገልጋይ ሆነው ሲሰማሩ በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ እናነባለን፡፡ ከሶስት ገጸባህሪያት መካከል ሁለቱ ከነበሩበት አስቸጋሪ ህይወት የተሻለ ለመኖር በማሰብ ነው የሰው ቤት አገልጋይነትን የተቀላቀሉት፡፡ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ስርም የምንመረምራቸው እነዚህን ገጸባህሪያት ይሆናል፡፡ በእንዬ ሺበሺ "የገቦ ፍሬ" ልቦለድ ውስጥ ዋና ገጸባህሪ የሆነችው ነፃነት ክብሩ ግን ስለህይወት ምንም ሳትረዳና ከቤተሰቦቿ መለየት ሳትፈልግ በግድ የሰው ቤት አገልጋይ በመሆኗ ይህ ርእሰ ጉዳይ አይመለከታትም፡፡

##### 3.1.1.1. ቢስ ራሔል

የተሻለ ህይወትን ፍለጋ የሰው ቤት አገልጋይ ከሆኑ ገጸባህሪያት መካከል አንዷ ራሔል ዳርጌ ናት፡፡ ራሔል ዳርጌ የደራሲ ፀሐይ መላኩ ረጅም ልቦለድ በሆነው "ቢስ ራሔል" ውስጥ በዋና ገጸባህሪነት የተሳለች ወጣት ሴት ስትሆን፣ ማለፊያ አሩዋ ፊላባ "በወላጆቻቸው ወይም በአሳዲጊዎቻቸው መኖሪያ ውስጥ ያለው ጥልቅ ድህነት ይህንን ሙያ እንዲመርጡ

ያደረጋቸው" በማለት በምዕራፍ ሁለት ላይ በሰጡት ትንታኔ ውስጥ ከሚካተቱ አገልጋይ ገጸባህሪያት መካከል የምትመደብ ናት፡፡

ልቦለዱ የዋናዋን የራሔል ዳርጌንና የቤተሰቦቿን ብሎም ታሪኩን ለማስቀጠል በአስፈላጊ ቦታና ጊዜ የተካተቱ የልዩ ልዩ ገጸባህርያትን ድርሻ የያዘ ነው፡፡ ረጅም ልቦለዱ የተገነባበት መሰረታዊ ሀሳብ በድንገተኛ አጋጣሚ ለተፈጠረ አካላዊ ጉዳት ማህበረሰቡ የሰጠው ምላሽ የአንድን ቤተሰብ ህይወት ባመሰቃቀለበት ሂደት ላይ ነው፡፡ የራሔል እናት ወ/ሮ ጠጂቱ ገድለብዙ ገና በወጣትነት እድሜያቸው በትውልድ መንደራቸው ውስጥ አጎታቸው በስህተት በተኮሱት ጥይት አራት የእጅ ጣቶቻቸውን ማጣታቸውን ያልተረዱት አሁን የሚኖሩበት አካባቢ ሰዎች፣ ጉዳታቸውን ከስጋ ደዌ ህመም ጋር በማዛመድ ሙሉ ቤተሰቡ ላይ ተፅእኖ ያሳድሩ ነበር፡፡

በልቦለዱ ውስጥ "አገልጋይ ገጸባህርይ" ሆና የተገኘችው ራሔል ዳርጌ ከላይ እንደተገለፀው የልቦለዱ ዋና ገጸባህሪይ ከመሆኗም ባሻገር ወ/ሮ ጠጂቱ ካሏቸው አምስት ልጆች መካከል ሁለተኛዋ ልጃቸው ናት፡፡ የቤተሰቡ ብቸኛ የገቢ ምንጭ አስገኚ የነበሩት አባታቸው አቶ ዳርጌ ምናለሽዋ ከሞቱ በኋላ የቤት እመቤት የነበሩት ወ/ሮ ጠጂ በአነስተኛ የጉልት ንግድ ለመሰማራት ተገደዋል፡፡ የበኩር ልጃቸው ለሥራ ብሎ ወደ ድሬደዋ ከሄደ ጀምሮ ለዓመታት አግኝተውትም ስለሱም ሰምተው አያውቁም፡፡ ራሔል በቤት ውስጥ ያሉትን ሶስት ታናናሽ እህቶቿንና ያለአባት ለዕለት ጉርስ እንኳን የማይበቃውን የጉልት ሸቀጥ ቸርችረው የሚያሳድጓቸውን እናታቸውን ገደብ የለሽ ጉስቁልና ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት ታደርግ ነበር፡፡

ለዚህም እንዲረዳት የማትሞክረው ገቢ ማስገኛ ሥራ አልነበረም፡፡ ወደ ብዙ መሥሪያ ቤቶች በመሄድ ደጋግማ የሞከረችው የመንግስት ሥራ ባይሳካላትም በመንገድ ዳር ተቀምጣ በቆሎ እሸት እየሸጠች፣ በጨርቅ ላይ ጥልፎችን እየጠለፈች ለገበያ በማቅረብ፣ እናቷ በሚውሉበት የጉልት ንግድ አብራ እየዋለች ወዘተ. የቤተሰቡን ኑሮ ወደ ተሻለ ሁኔታ ለመቀየር ብዙ ትደክም ነበር፡፡ አጋር ይሆነኛል ብላ የተማመነችበት ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ ለአራት ዓመታት አብሯት የዘለቀው ፍቅረኛዋ ኤፍሬም የመንደሩ ሰዎች የሚያናፍሱትን የቤተሰቡን ቢስ ገላነት ከሰማ በኋላ በቁራጭ ወረቀት ነበር በቃኝ ብሎ የተለያት፡፡ ለጊዜው ብታዝንም ኑሮዋን ለመቀየርና የተሻለች ሆና ለመገኘት ይህ አጋጣሚ ተጨማሪ ጉልበት ነበር የሆናት፡፡

> "ከእንግዲህ ዋናው ቁምነገሬ ሰው መሆን ነው፡፡ በዚህ በናቀኝ ሰውና ኅብረተሰብ መካከል ሰው ሆኜ መገኘት አለብኝ፡፡ ሰው ለመሆን ከመቼውም ዛሬ ወስኛለሁ በቃ.....በሞራልና በኢኮኖሚ ድህነት ታንቆ አሉባልታ ሲያናፍስ በስንፍና ተርመጥምጦ ካለው ኅብረተሰብ መካከል እንደምንም ራሴን መንጭቄ ወደ ከፍታ ማድረስ ነው፡፡ አምናለሁ ሰው እንደምሆን ...ያኔ ነው ኤፍሬምንም የማነጋግረው..." (ፀሐይ፣ 1996፣17-18)

በዚህ በራስ የመተማመን መንፈሷ በዓላማዋ ላይ እምነት የነበራት እራሷ ብቻ እንጂ ከልብ የምትወዳት እሷ ግን ከአክስቷ ጋር ሆና ውድቀቷን የምታመቻችላት ጓደኛዋ ቀለሟ አልነበረችም፡፡ "በምን ተዓምር ነው ከዚህ ማህበረሰብ የተሻልኩ እሆናለሁ ብለሽ የምታስቢው?" እያለች ዓላማዋን ታጣጥልባት ነበር፡፡ ይህ የጓደኛዋ ነቀፋ ወደኋላ አልጎተታትም፡፡ ይልቁንም እሷ ልክ እንደሆነች ለማሳየት ያሉትን አጋጣሚዎች በሙሉ ለማባከን አልፈለገችም፡፡ በተገናኙ ቁጥር ይህንኑ ሀሳቧን ለማስረዳት ትሞክራለች፡፡

> "ለማየት ያብቃሽ ቀለሟ ... በጉልት ንግድም ሆነ በሚያጋጥመኝ አነስተኛ ሥራ ተነስቼ ዓላማዬን ተመርኩዤ ከግብ እደርሳለሁ ... አልፍ አልፎ ከእናቴ ጋር የምነግደውን የጉልት ንግድ መደበኛ ሥራዬ አድርጌ እይዘዋለሁ ... እግረ መንገዴንም በተማርኩት ትምህርት ልሠራበት የምችልበትን አጋጣሚ እከታተላለሁ... ይሄው ነው የመነሻ ነጥቤ ... ይገባኛል አንቺ ብቻ አይደለሽም ሥራውን ብዙ ሰዎች የሚንቁት ነው፡፡ ሥራዬ ብሎ ለያዘው ሰው ደግሞ ሰው ለመሆን ያበቃል፡፡ ለማየት ያብቃሽ ሰዎች ዝቅተኛ ብለው ከሚንቁት ደረጃ ተነስቼ ምናልባት ጥቂት ሰዎች ከሚደርሱበት ትልቅ ቦታ እደርሳለሁ፡፡" (ፀሐይ፣ 1996፣19)

ይህን ዓላማዋን ለማሳካት ማውራት ብቻ ሳይሆን በተግባር የምትሞክራቸው ነገሮች በርካታ ነበሩ፡፡ የጉልት ሥራ፣ የጥልፍ ሥራ፣ የሥራ ማስታወቂያ ወጥቷል በተባለችባቸው መሥሪያ ቤቶች የትምህርት ማስረጃዎቿን በመበተን ከፍተኛ ሙከራ ማድረግ፣ በደላላ አማካኝነት ግለሰብ ቀጣሪዎችን ማፈላለግ ወዘተ. ጊዜና ጉልበቷን የወሰዱ ሙከራዎቿ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ነገሮች እንዳሰበቻቸው አልሆን እያሏት ብዙ ትቸገር ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እሷ ለቤተሰቦቿ ቤተሰቦቿ ደግሞ ለእሷ ያላቸው ጥልቅ ፍቅር የኢኮኖሚ

ችግሮቻቸውን እየዘነጉና የተገኘውን በፍቅር እየተካፈሉ መኖርን ስላስለመዳት ዓላማዋ ላይ በቶሎ ተስፋ አልቆረጠችም፡፡ ቀን በጨመረ ቁጥር ሙከራዋን በስፋት ቀጠለች፡፡

ለብዙ ጊዜያት ሥራ እንዲያፈላልግላት ስትጠይቀው የነበረው ደላላም ከወራቶች በኋላ በኬኒያ አምባሳደር መኖሪያ ቤት ውስጥ በአገልጋይነት መቀጠር ከፈለገች እንደምትችል ይነግራታል፡፡ ለዚህ የአገልጋይነት ሥራ ደመወዙ 100 ብር መሆኑን ስትሰማ ደግማ ማሰብ አልፈለገችም፡፡ በደስታ ነበር የተስማማችው፡፡ የመጽሐፉ መቼት በነበረው ወቅት በሀገራችን 100 ብር ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጥ ስለነበር ሥራውን በደስታ መቀበሏ አስገራሚ ነገር ሊሆን አይችልም፡፡ ራሔል እንዳሰበችውም የቤተሰቦቿን መሰረታዊ ፍላጎት በማሟላት እናቷን “ለለልጆቼ ምን ልስጥ” ከሚል የየዕለት ሰቆቃ ታድጋቻቸዋለች፡፡

> “ይህ ጅምር ተግባር አካሏንና መንፈሷን ከማፍታታት አልፎ ለቤተሰቡም ተስፋና አለኝታ ሆነ፡፡ የእናቷ የወ/ሮ ጠጇ መልክ እንኳን ሳይቀር የጥንት ቀለሙን ሲላበስ የጠቋቆረው ቆዳቸው ፈካ ማለት ጀመረ፡፡ ገመናቸውም ሞቀ … ከራሷና ከቤተሰቧም አልፋ በየወሩ ደመወዟን ስትቀበል ለጓደኛዋ ለቀለሟ የቅባት መግዣ፣ የአውቶቡስ መሳፈሪያ እያለች እጇን ትዘረጋ ነበር፡፡” (ፀሐይ፣ 1996፣53)

ራሔል የቤተሰቦቿን ችግር ከመቅረፍ አኳያ እፎይ ያስባላትን የሰው ቤት አገልጋይነት በትጋትና በታማኝነት ቀጠለችበት፡፡ ሆኖም ባለችበት መርገጥ የምትፈልግ ሴት አይደለችምና ይህ ሥራ በቃኝ ብላ አልተቀመጠችም፡፡ ዝቅተኛና አድካሚ በሆነው የዛሬ ኑሮዋ ላይ ተንጠላጥላ ነገ የተሻለ ኑሮ ለራሷና ለቤተሰቦቿ የምታልም ናት፡፡ ይህን ህልሟን ለማሳካትም አንድ ብላ የጀመረችው ከሰው ቤት አገልጋይነት ቢሆንም ውጤታማ እንደምትሆን በራሷ ላይ ከፍተኛ እምነት ነበራት፡፡

ከቤተሰቦቿ ጀምሮ በዙሪያዋ ያሉትን ጎረቤቶቿንና የሥራ ባልደረቦቿን በዚህ ህልሟ ውስጥ እያካተተች ጥሩ እንዲያስቡ ትጥራለች፡፡ ነገን በተስፋ ማየትንና ጥሩ ማሰብን በዙሪያዋ ላሉ ሁሉ ታጋባባቸዋለች፡፡ ሌላው ቀርቶ የእናቷ ጓደኛ የሆኑት በብቸኝነታቸው ሁሌም የሚያለቅሱትን ባልቴት የምታረሳሳቸው እጅግ ከፍተኛ የሆነ ህፃናት ማሳደጊያና የአዛውንቶች መጦሪያ ከፍታ በዛ ድርጅት ውስጥ ሥራ አስኪያጅ እንደምታደርጋቸው በመንገር ነበር፡፡ ይህን ጨዋታ ደግሞ ወ/ሮ ዳሮ ስለሚወዱት ከሀዘናቸው መፅናናት ብቻ

ሳይሆን ነገን በተስፋ ጭምር ያዩበት ነበር፡፡ በድርጅቱ ህልውና ጉዳይም እርግጠኛ ሆነው ጥርጣሬ ያደረባቸውን እናቷን ለማሳመን ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡

> "ወደ ፊት ራሔል ሥራ ይዛ፣ ሀብት አፍርታ የምታቋቁመው ድርጅት አላት፡፡ በዚያ ድርጅት ውስጥ ታዲያ ለኔ ትልቅ ሥራ አስባልኛለች… አንዳንዴ የእግዜርን ሰፊ ቸርነት የምትረሺው መሰለኝ…ምን ይሳነዋል? 'ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ' ሲባል አልሰማሽም… ስለተመኙ ብቻ ማግኘት ይቻላል ማለት አይደለም፡፡ በልቡ የተመኘ ጠንካራ ሰው ምኞቱን ይጨብጣል፡፡ ራሔልም ቁም ነገረኛ ልጅ ስለሆነች ያሰበችውን ታደርገዋለች… አምንባታለሁ፡፡" (ፀሐይ፣1996፣74)

በአንባሳደሩ መኖሪያ ቤት በተቀጠረች በስድስት ወሯ አንድ ምሽት ላይ የነበረ የእራት ግብዣ ሲጠናቀቅ የጽዳት ሥራ ማከናወን ነበረባት፡፡ ሥራዋን ሥትሠራ በዶላር የተሞላ የኪስ ቦርሳ አግኝታ ባለቤቱን አፈላልጋ መመለሷ ቀጣሪዎቿ ለሷ ያላቸውን ግምት ከፍ እንዲል ያደረገ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ደመወዟ ወደ ሁለት መቶ ብር እንዲያድግ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ የቦርሳው ባለቤት የነበረው የአንባሳደሩ ፀሐፊ ጀምስ ዊሊ ከአድናቆትም አልፎ ጓደኛዋ ለመሆን ያስቻለው ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

ጀምስ ከራሔል ጋር መቀራረቡ የእሷንና የቤተሰቦቿን ኑሮ በቅርበት እንዲረዳ አስችሎታል፡፡ በተገነዘበው ልክም ክፍተቶቹን ለመሙላት የእሷን ፈቃድ እየጠየቀ ሙከራ ያደርግ ነበር፡፡ ከጊዜያዊ የቁሳቁስ ድጋፉ ባሻገርም በዘላቂነት ህይወቷ የሚቀየርበትን መንገድ ያስብ ስለነበር እሚያውቃቸውን ባለስልጣናት በማጠያየቅ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ አስተናጋጅ ሆና እንድትቀጠር የሚችለውን በሙሉ አደረገ፡፡ ይህም ዕድል የራሔልንና የቤተሰቦቿን ኑሮ ከመሰረቱ የለውጠ አጋጣሚ ለመሆን ቻለ፡፡

ወደ ተለያዩ ሀገራት ለሥራ የምታደርገውን ጉዞ በአድካሚ ሥራ ጉልበታቸውን የሚጨርሱትን ታናናሽ እህቶቿን ህይወት ለመቀየር ተጠቀመችበት፡፡ በአዲስ አበባ ሁለት የተለያዩ ቦታዎች ላይ የልብስና የኮስሞቲክልስ እቃዎችን አቅራቢ ሱቅ በመክፈት የራሳቸውን ገቢ እንዲያገኙ አደረገች፡፡ እናቷን ወ/ሮ ጠጄንም መርዳት በሚችሉት ቦታ ላይ ብቻ በማሰማራት እረፍት እንዲያደርጉ አስችላቸዋለች፡፡ በጉስቁልና የሚኖሩበትን መንደርም ጥለው ልጃቸው ወደ ገዛችላቸው ቪላ ቤት ተዛወሩ፡፡ ራሔል "ከእንግዲህ ዋናው

ቁምነገሬ ሰው መሆን ነው” ብላ ያስቀመጠችውን ግብ ሳትዘነጋ ለስኬቱ ጥረት ታደርግ ስለ ነበር እንዳሰበችው ከዓመታት በኋላ ሊሳካላት ችሏል፡፡ የተሻለ ህይወት ፍለጋ የተቀላቀለችው የሰው ቤት አገልጋይነት ብዙ መልካም ዕድሎችን እንድታገኝ መነሻ ሆኗት ለራሷና ለቤተሰቦቿ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ችግረኞች መፍትሄ ስትሆን አንብበናል፡፡

### 3.1.1.2. የደራሲዋ ፋይል

ደራሲ የዝና ወርቁ በ2002 ዓ.ም ለአንባቢ ያቀረበችው “የደራሲዋ ፋይል” የዚህ ጥናት ትኩረት ከሆኑት ረጅም ልቦለዶች መካከል አንዱ ነው፡፡ 255 ገጾች ያሉት የደራሲዋ ፋይል ዋና ገጸባህርይ ፅዮን ታምሩ ነች፡፡ የታሪኩን መከናወኛ ቦታ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ ያደረገው ይህ ረጅም ልቦለድ የሚጀምረው የዋና ባለታሪኳ አባት አቶ ታምሩ ከሞቱበት ማግስት ነው፡፡ ለሀዘን በተተከለው ድንኳን ውስጥ የተሰበሰቡትን ሀዘነተኞች ሸሽታ በጠባቧ ቤታቸው ውስጥ በመኝታዋ ላይ የተኮራመተችው ፅዮን አባቷ ከመሞታቸው በፊት የነበራቸውን ቤተሰባዊ ህይወት በምልሰት ታስቃኘናለች፡፡

አባቷ በመምህርነት ሙያቸው የሚከፈላቸው ደመወዝ የእናቷን፣ የእሷንና የታናሽ ወንድሟን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት አይችልም ነበር፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን አቶ ታምሩ በሚኖራቸው ትርፍ ጊዜ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ከመፈለግ ይልቅ የደራሲነት ዝንባሌያቸው እያየለባቸው ማንበብና መፃፍ ላይ ያተኩሩ ነበር፡፡ ፅዮንም ከአባቷ ስር አለመለየቷ የማንበብና መፃፍ ልምድን እንድታዳብር ከማድረጉም በተጨማሪ በሁለቱ መካከል ያለው የአባትና ልጅ ፍቅር ስር የሰደደ እንዲሆን ያስቻለ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ይህ አጋጣሚ ከእሳቸው ሳትለይ የማጀት ሥራዎችን እንድታከናውን ከሚፈልጉት እናቷ እንድትራራቅ መነሻ ሆኗል፡፡ ብቻቸውን ደፋ ቀና እያሉ ከሚያመሹበት ቤተሰባዊ ሥራ የጽዮንንና የአባቷን ስነጽሁፋዊ ውይይት እየሰሙ መብሸቅ የየእለት ተግባራቸው ሆነ፡፡ የበዛባቸው ዕለትም ዱላ ይሰነዝሩባት ነበር፡፡

> “ኤዲያ! የታደሉት ኑሯቸውን ያሞቃሉ፤ የእኛ ቤት ሁልጊዜ ባዶ ወረቀት! … ነይ ውጪ፤ ያንቺ ወረቀት ከስራ ማምለጫ ነው፡፡ አጋሰስ! … ደሞ የዚችኛዋ ይባስ እንጂ፤ ‘በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ’ ነይ ውጭ!’ ይሉና አንድ ጊዜ ሲያሳርፉባት አባቷ የያዙትን ወረቀት በንዴት ይበትናሉ፡፡ ወደ ፊት እየሰገረ የነበረ

> ብዕራቸውም ይደነብራል፡፡ ጠብ ይፈጠራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የጎረቤት ገላጋይ ገብቶ ያበርዳቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የፅዮን ስም በወ/ሮ የተመኝና በወዳጅ ዘመዶቻቸው በመጥፎ ይነሳል፡፡…" (የዝና፣2002፣11)

የፅዮንንና የአባቷን ሁኔታ ለመረዳት የትምህርት ዝግጅታቸው የማይፈቅድላቸው ወ/ሮ የተመኝ የተረጋጋ ቤተሰባዊ ህይወት ያጡት በባለቤታቸው ፋይዳ የለሽ ማንበብና መፃፍ ምክንያት ነው ብለው ስለሚያምኑ ዘወትር እንደተጨቃጨቁና እንደተጣሉ ነበር፡፡ ይህ ጭቅጭቅና ፀብ ካልተሳካው የድርሰት ሥራቸው ጋር ተደምሮ አቶ ታምሩን በሰፈሩ የታወቁ ሰካራም እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ በየእለቱ ካለ በቂ ምግብ የሚወስዱት አልኮል መጠጥም ሞታቸውን እንዳፋጠነው ከታሪኩ እንረዳለን፡፡

ፅዮን በእናትና አባቷ ጭቅጭቅ ለአባቷ አድልታ እናቷን ብታማርርም የሁልጊዜም ምኞቷ በፍጥነት አድጋ ለቤተሰቦቿ በተለይ ለአባቷ የተሻለ ኑሮ ማመቻቸት ነበር፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ዘወትር አባቷ እንደሚያስቡት የሙሉ ጊዜ ደራሲ እንዲሆኑ ማድረግ እንዳለባት ታቅዳለች፡፡

> "…ተስፋ በማይቆርጠው ምኞቷ ግን አንድ ቀን ሥራ ይዛ ለአባቷ አዲስ ህይወት ፈጥራ ወደ ድርሰት ዓለም እንዲመለሱ ማድረግንና የፃፉትንም በገንዘቧ አሳትማ ሲደሰቱ ማየትን ዘወትር ታልም ነበር፡፡ ሆኖም ለብዙ ወራት ያለ በቂ ምግብ የተጋተሩት መጠጥ የመሞቻ ጊዜያቸውን አፋጠነው፡፡" (የዝና፣2002፣17)

ይሁን እንጂ አብዝታ የምትወዳቸው አባቷ እሷ አድጋ ያሰበችውን ሳታደርግላቸው 12ኛ ክፍል ለመፈተን ሳምንታት ብቻ በቀሯት ጊዜ ላይ በሞት ተለዩዋት፡፡ "አባቴን፣ ጓደኛዬን አጣሁ፡፡ ምነው ለአንድ ቀን እንኳን ራሴን ችዬ የሚፈልገውን ባደረግሁለት" (የዝና፣2002፣18) እያለች መሪር እንባ በማንባት ሀዘኗን ለማቅለል ትሞክር ነበር፡፡

ከአባቷ ሞት በኋላ የአባቷ ሞት ምክንያት አድርጋ ከምትቆጥራቸው እናቷ ጋር መስማማት ይቸግራት ነበር፡፡ በዚህ መካከል ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት የሚያበቃ ውጤት ብታመጣም ከመደበኛ ትምህርቷ ይልቅ የአባቴ ማስታወሻ ብላ የምታስበው የድርሰት ሥራዋ ላይ በማተኮሯ የመጀመሪያውን ሴሚስተር ማለፍ አልቻለችም፡፡ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ወስጥ አይዞሽ እያለ ከጎኗ የነበረው ፍቅረኛዋ ግርማ በቀጣዩ ዓመት ትምህርቷን እስክትጀምር

ከእርሱ ጋር ሆና የድርሰት ሥራዋን እንድታከናውን ቢጠይቃትም “ምንም ነገር ሳይኖረኝ ሚስት ልሆን አይገባም፡፡” በሚለው አቋሟ ምክንያት ፈቃደኛ ሳትሆን ወደ እናቷ ቤት ተመለሰች፡፡

ይሁን እንጂ ከእናቷ ጋርም ባለመስማማቷ ህይወት በጣም አሰልቺ ሆነባት፡፡ ከዚህ የተሻለ ብላ የምታስበውን ህይወት ለመምራት የሚያግዟትን አማራጮች ተቀምጣም ሆነ ተኝታ ማሰብ የየዕለት ተግባሯ ሆነ፡፡ በጓደኛዋ በብዙነሽ በኩል የቢሮ ሥራ እንደሚያስቀጥሯት የተመሰከረላቸው ባለስልጣንም ሴትነቷን እንደክፍያ እንደሚፈልጉ ስትረዳ በቢሮ ሥራ በኩል ተስፋ ቆረጠች፡፡ የመጨረሻ አማራጭ አድርጋ የወሰደችው የሰው ቤት ሠራተኝነትን ስለነበር ከሚያውቋት ሰዎች ሁሉ ተደብቃ በደላላ አማካኝነት በወ/ሮ ባፈና ቤት ተቀጠረች፡፡

በሰው ቤት ሠራተኝነት የመጀመሪያ ልምድ ያካበተችበትን የወ/ሮ ባፈና ቤት እንዳሰበችው ለድርሰት ሥራዋ የሚተርፍ ጊዜና በቂ ገንዘብ ባይለግሳትም እሷ የምትማረርበት የእናቷ ቤት ኑሮ ምንያህል አስደሳችና ሰብዓዊነት የሚታይበት እንደ ሆነ እንድትረዳ አግዟታል፡፡ ወ/ሮ ባፈና እና ባለቤታቸው በግዙፉ ኑሮዋቸው ውስጥ ሶስት ልጆቻቸውን ከአካላዊም ሆነ ከስነልቦናዊ ጉዳት ተከላክለው ለማሳደግ የተቸገሩበት ሁኔታ የህይወትን ሌላ ገፅታ ለመመልከት ያስቻላት ነበር፡፡ ከአንድ ዓመት በላይ በዚህ ቤት ውስጥ እንዳዘዟት እየሆነች ስትኖር በእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ግንኙነት ውስጥ የሚንተከተከውን የታመቀ ቁጣ እንዳይፈነዳና ድርሻ እንዳይኖራት ዘወትር ትጸልያለች፡፡

ከዚህ ቤት ወጥታ የተቀጠረችበት ወንደላጤው ከሊል የኢኮኖሚ አቅሙ ለብዙ ችግር የዳረገው መልካም ሰብዕና ያለው ጎልማሳ ነበር፡፡ ብቸኛው ከሊል የበዛ የቤት ውስጥ ሥራ ስላልነበረው ያሰበችውን የድርሰት ሥራ ለመሥራት ችላ ነበር፡፡ ከመላመድ ብዛት የከሊል ስሜት ከአሠሪነት ወደ ፍቅር ቢያደላም ስለሚያከብራትና ስለሚፈራት ሊጠይቃት አልቻለም፡፡ አንድ ምሽት በመጠጥ ኀፋፌነት ሊደፍራት ሲታገል እራሷን ለመከላከል ስትገፈትረው ወለል ላይ ወድቆ አደጋ ይደርስበታል፡፡ በተፈጠረው ግርግርም የከሊል ጎረቤቶች ፖሊስ ጣቢያ እንድትታሰር ያደርጋሉ፡፡ ከህክምና መልስ ሊከሳት እንደማይፈልግ ከሊል በማሳወቁ ዋስ እንድትጠራ ይደረጋል፡፡ በፖሊስ ጣቢያ ቆይታዋ ከዓመት በፊት ፍቅረኛዋ ግርማ እንደጠፋችበት ያስመዘገባት ሴት መሆኗ ስለታወቀ ተጠርቶ በዋስትና ወደ ቤቱ ይወስዳታል፡፡

ፅዮን ታምሩ ከዩኒቨርሲቲ ስትባረርና ከእናቷ መስማማት ስትቸገር ይሻለኛል ብላ የገባችበት የሰው ቤት ሠራተኝነት እንዳሰበችው ገንዘብና በቂ የድርሰት መፃፊያ ጊዜ ባይሰጣትም የምታማርረው ቤተሰባዊ ህይወቷ ምን ያክል ሰላማዊ እንደሆነ እንድታውቅ አስችሏታል፡፡ ምርጫ አጥታ ወደ ሁለት ዓመታት የተጠጋው የሰው ቤት ሠራተኝነት ቆይታዋ በሌላ ባላሰበችው መንገድ **የተሻለ ህይወትን** ለመምራት ምን ማድረግ እንዳለባት ለማቀድ የሚያስችላትን ተሞክሮ ለግሷታል፡፡ እስከዛሬ ከነበረችበት የህይወት ስልት በተለየ መንገድ የምትራመድበትን ብስለት እንድትላበስ አድርጓታል፡፡

### 3.1.2. አለመማር

በዚህ የጥናት ሥራ ውስጥ ለጥናት ከተመረጡት ሶስት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ትንታኔ ከተሰጠባቸው ሶስት አገልጋይ ገጸባህሪያት መካከል ሁሉም ገጸባህሪያት “ያልተማሩ” በሚለው ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ከሶስቱ ገጸባህሪያት በትምህርት የተሻለ ደረጃ ላይ ናት ብለን ካሰብን “የደራሲዋ ፋይል” ገጸባህሪ ጽዮን የአንደኛ ዓመት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆና በመጀመሪያ ሴሚስተር የተባረረች ናት፡፡ ሌሎቹን ያየን እንደሆነ የ”ቢስ ራሔል” ራሔል ዳርጌ 12ኛ ክፍል ተፈትና ማለፊያ ነጥብ ያላገኘች፣ “የገቦ ፍሬዋ” ነፃነት ክብረት ገና ከሰባተኛ ክፍል ወደ ስምንተኛ ክፍል እንዳለፈች ከቤተሰቦቿ ለመለየት የተገደደች እና በሰው ቤት ውስጥ እያገለገለች 12ኛ ክፍል ለመጨረስ የተፍጨረጨረች ሆና እናገኛታለን፡፡ ስለዚህም በዚህ ጥናት ውስጥ ትኩረት የተሰጠባቸውን ሶስቱንም ገጸባህሪያት ከዚህ ነጥብ አንፃር ትንታኔ እሰጥባቸዋለሁ፡፡

#### 3.1.2.1. ቢስ ራሔል

የ”ቢስ ራሔሏ” ራሔል ዳርጌ በዚህ ንኡስ ርዕስ ስር ማብራሪያ ከሚሰጥባቸው ገጸባህሪያት መካከል አንደኛዋ ናት፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከቤተሰቦቿ ጋር ያደገችው ራሔል ዕድሜዋ በፈቀደላት ጊዜ ወደ መደበኛ ትምህርት እንዳትሰማራ እንቅፋት የሆነባት አንዳችም ሁኔታ የለም፡፡ በየእርከኑ ያሉትን የክፍል ደራጃዎች ተሸላሚ እየሆነች ነበር የ12ኛ ክፍልን ያጠናቀቀችው፡፡ እንደውም የትምህርት አቀባበሏ ጥሩ እንደ ነበርና “ጠንካራ ተማሪ” ምድብ ውስጥ ልትካተት የምትችል ሰለመሆኗ የምንረዳበት ትንታኔ በመጽሐፉ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ በመደበኛ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ክበባትም ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እያደረገች የተለያዩ ሰርተፍኬቶችን ለማግኘት ችላ ነበር፡፡

ራሔልን አለመማሯ ለሰው ቤት አገልጋይነት ዳረጋት እንድንል ያስቻለን የተሻሉ ናቸው ብለን የምናስባቸውን የመንግስትም ሆነ የድርጅት ሥራዎች ለማግኘት ከ12ኛ ክፍልም በላይ የዲፕሎማ ወይንም የዲግሪ ምሩቅ መሆን ቅድሚያ ስለሚሰጠው ነው፡፡ የሀገሪቱ የትምህርት አስተዳደር ስልት እነዚህን እድሎች በቀላሉ ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ እንዳይኖር አድርጓል፡፡ በልቦለዱም ውስጥ ይህንን ሀሳብ የሚያብራራ ነጥብ በስፋት ተቀምጧል፡፡

> "በትምህርትሽ ታታሪና ምስጉን እንደነበርሽ ውጤትሽ ይናገራል … መጨረሻው ላይ ባለው ጠባብ መንገድ ለማላፍ አለመቻልሽ ግን ያሳዝናል፡፡ የሚታዘነው ጥበቱን በፈጠረው ችግርና በችግሩ ፈጣሪዎች ነው፡፡ አንቺ በውጤትሽ እንደገመትኩሽ ለከፍተኛ ትምህርት የምትገቢ ነበርሽ፡፡ የአገሪቱ አቅም መመንመን የትምህርት ተቋሞች እድገት እንዲቀጭጭ አድርጓል፡፡ ስለዚህም ብሩህ ህሊና ባላቸው ለጋ ልጆች ህይወትና ዕድል ላይ ጅምላ የግፍ ፍርድ በየዓመቱ ሲፈረድ እናያለን፡፡ አንቺም ከነዚህ ብዙዎች አንዷ ነሽ፡፡ ላለሽበት ችግር መንስኤው አንቺ ሳትሆኚ ሌላ ግዙፍ አካል ነው … ስለዚህ አንቺ ባንቺነትሽ ተስፋ እንዳትቆርጪ ላስገነዝብሽ እፈልጋለሁ፡፡ ባለሽ ብሩህ አእምሮ በመጠቀም ሰው ለመሆን እልህና ወኔ ይኑርሽ፡፡" (ፀሐይ፣1996፣38)

ምንም ይሁን ምን ራሔል ከ12ኛ ክፍል በላይ ተምራ ሥራ ማግኘት አለመቻሏ በሷም ሆነ በቤተሰቧ ህይወት ላይ የፈጠረው ጫና በቀላሉ የሚታለፍ አልነበረም፡፡ ችግራቸው ፋታ የሚሰጥ ስላልነበረም ተምራ ሥራ ባታገኝም በደላላ አማካኝነት ወዳገኘችው የሰው ቤት አገልጋይነት ለመሰማራት ተገዳለች፡፡

### 3.1.2.2. የደራሲዋ ፋይል

"አለመማር" የሚለውን ቃል በንፅፅር ካየነው የዚህ መፅሐፍ ዋና ገጸባህሪይ ፅዮን ታምሩ አይመለከታትም ተብሎ ሊታሰብ ይችል ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ የ6ወራት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ አንዳችም የጨመረላት የሕይወት ጠብታ የለም፡፡ በባህሪም ሆነ በእውቀት እንዲሁም ገንዘብ ሊያስገኝ በሚያስችል ተግባር ልትሰማራበት የሚረዳ አዲስ ሰብዕና እንድታገኝ አልረዳትም፡፡ ለዚህም ነው በዚህ ንኡስ ርዕሰ ጉዳይ ስር ስለ ፅዮን ትንታኔ መስጠት ያስፈለገው፡፡

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ ትምህርቷ ላይ ሳይሆን በድርሰት ሥራዋ ላይ ማተኮሯ ለዘላቂ ህይወቷ አስጊ ነው ብሎ የሚያምነው ፍቅረኛዋ ግርማ ሁልጊዜም ትክክለኛው መንገድ ትምህርት መሆኑን ሊያሳያት ይሞክር ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ተግባር ውስጥ ትምህርት ያለውን ዋጋ እንድትገነዘብ ይፈልጋል፡፡

> "… እንደኔ ግን በዚህ ዓመት ሙሉ ትኩረትሽን ትምህርትሽ ላይ ብታደርጊ ይሻላል፡፡ በዚያም ስለህይወት ላይ ያለሽ ተሞክሮ ጠባብ ይመስለኛል፡፡ … ነገሮችን የምትገነዘቢበትና የምትመዝኚበት የዳበረ በቂ ተሞክሮ ያለሽ ስለማይመስለኝ ይህን ለማሳካት ትምህርትሽን አስቀድሚ፡፡ … ድርሰቱን አልተውም ካልሽም ለትምህርትሽ ቅድሚያ እየሰጠሽ ብትሞክሪው ይሻላል፡፡ ትምህርትና ድርሰቱን ጎን ለጎን ማከናወን ከቻልሽ ደግሞ የመጀመሪያ መጽሐፍሽን በታይፕ የማስፃፍ እድል እንደማትነፍጊኝ እተማመናለሁ፡፡…" (የዝና፣2002፣70)

አባቷ ሞተው የ12ኛ ክፍል ውጤት እየጠበቀች ከእናቷ ጋር የቆየችባቸውንና ከዩኒቨርሲቲ በአንደኛው ሴሚስተር ተባራ ወደ እናቷ ቤት የተመለሰባቸውን ጊዜያት በጭቅጭቅ፣ በቁጣና በጥላቻ ስላሳለፈቻቸው ከዚህ ሁኔታ ለመገላገል ያስችሉኛል ብላ የምታስባቸውን ሙከራዎች በሙሉ ታደርግ ነበር፡፡

በሙከራዎቿ ሁሉ ግን የተማረችው ዲፕሎማና ዲግሪ ከሌለ የተለየ መንገድ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ የቀረበቻቸው ጓደኞቿ ብዙነሽና ሶስና ደግሞ ማትሪክ ማለፍ ሲከብዳቸው የተለየ አቋራጭ መንገድ አድርገው የወሰዱት ሴትነታቸውን ብቻ ነው፡፡ ሥራ ይዘዋልና ለእሷም እንዲፈልጉላት ስትጠይቃቸው ሶስና ዘመዴን ላስተዋውቅሽ ብላ አቶ አሻግራቸው ቤት ይዛት ለመሄድ አማከረቻት፡፡ ፅዮን ሌላው ጉዳይ ሳይገባት ሥራ በዘመድ ብቻ የሚገኝበት መንገድ ቢያበሳጫትም ለመሞከር ወሰነች፡፡ "ሂደቱ ትክክል አይደለም" ብላ ስትሞግታቸው እነሱ ያለፉበት መንገድ ከእሷ በጣም የተለየ ስለሆነ ሊሰሚት እንኳን አይፈልጉም ነበር፡፡

> "… እንደኔ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ የሌለው ሰው ባለስልጣን የሆነ ዘመድ ሊኖረው ወይንም የሚችለውን ሌላ አማራጭ መጠቀም መቻል አለበት፡፡ አንቺ ለምን እውነታውን መቀበል ያቅትሻል? እንደ ጥቂቶቹ ከፍተኛ ትምህርት መማር መቻል ይኖርብሻል፡፡ እንደ ብዙዎቹ

ከታች ከቀረሽ ደግሞ ልዩ የሚያደርግሽን መንገድ
መፍጠር መቻል ይኖርብሻል፡፡…" (የዝና፣2002፣130)

"አጎቴ ነው ሥራ ይፈልግልሻል" በሚለው ማሳመኛ የግዷን ሶስናን ተከትላ ብትሄድ እንዳሰበችው ሊሆንላት አልቻለም፡፡ አቶ አሻግራቸው "ቡና አፍይልን" በሚል ትእዛዝ ሶስናን ከሳሎን አስወጥተው ሊደፍሯት ሲሞክሩ በደመነፍስ አምልጣቸው ከቤታቸው ከወጣች በኋላ የቢሮ ሥራ ፍላጋዋን በመተው ለማንም ሳታማክር ወደ ሰው ቤት አገልጋይነት በደላላ አማካኝነት ተሰማራች፡፡

### 3.1.2.3. የገቦ ፍሬ

ህንዳዊው Dr. Patil በምዕራፍ ሁለት ላይ "ትምህርት ግለሰቦች የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የባህል መብቶችን እንዲጠቀሙ ስለሚያስችል በእጅጉ አስፈላጊ ነው።" ሲሉ የሰጡትን ማብራሪያ መጥቀሳችን የሚታወስ ነው፡፡ ይህንን የተንታኙን መነሻ ሀሳብ ይዘን የገቦ ፍሬዋን ነፃነት ክብረትን እንመልከት ስንል የምንረዳው ሀሳብ አለ፡፡

ገና በለጋ ዕድሜዋ በርካታ ጫናዎችን ያስተናገደችው ነፃነት ክብሩ ተወልዳ ከኖረችበት በጎንደር የምትገኝ ትንሽ የገጠር መንደር አንፃር ለትምህርት የነበራት ፍቅር እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስከደረሰችበት የትምህርት ደረጃ ድረስ የተማረችው ካለምንም ሰላም ነው፡፡ አባቷ ባሰኛቸው ቁጥር ሲያስቀሯት መምህራን እየደጋገሙ ወደ ትምህርት ቤት ሲመልሷት፣ ህፃናት ጓደኞቿ በአካል ጉዳቷ እያሾፉ መፈጠሯን እንድትጠላ ሲያደርጉ፣ የባሰባቸው በቸኮለች ፊት አውራሪነት ከማሾፍ አልፈው አካላዊ ቅጣት ሲያደርሱባት ወዘተ. ብዙ ትግል ነበረባት፡፡ ይህንን ሁሉ ችግር ግን ለመምህራን ነግራ ማስቆም ስትችል አላደረገችውም፡፡

እንደዚህም ተሰቃይታ ለመማር ብትሞክርም እስከ ታሪኩ ፍፃሜ ድረስ ለህይወቷ ስኬት ዋስትና ሊሆን የሚችል ዕውቀት ባለቤት አልነበረችም፡፡ የብስለትና የዕውቀት ማነስ ስለነበረባትም መብቷን ማስከበር አልቻለችም፡፡ በክብር ስም ዘላቂ ህይወቷን አዘቅት ውስጥ የሚጥል ውሳኔ ወላጆቿ ሳያማክሯት ሲወስኑ ተባራሪ ወሬ ብትሰማም ተግባራዊ የሚደረግበትን ቀን በፍርሃት ከመጠበቅ ውጭ አንዳችም እርምጃ አልወሰደችም፡፡ ወላጆቿ በዘር ይስተካከለናል ላሉት የአእምሮ ጤና ችግር ላለበት ወጣት ሊድሯት ሲሞክሩ

ለተቃውሞ አንዲትም ቃል አልወጣትም፡፡ ይልቅ ወስና የነበረው እራሷን ስለማጥፋት ብቻ ነበር፡፡

> "… ባለበት የጤና ችግር ሊገድለኝ የሚችል ባል ሊድሩኛ እየተነጋገሩ ነው … አጥብቄ መቃወም ያለብኝን ይህን ጉዳይ እንዴት እንደምጋፌጠው ግራ ገባኝ፡፡ ከቤቴና ከት/ቤት ውጭ ሌላ ቦታ ስለማላውቅ መጥፋት የሚታሰብ አልነበረም፡፡ ከዚህ ሁሉ ለመገላገል ግን አንድ ሀሳብ መጣልኝ፡፡ ቀላል ነው፡፡ ከእናቴ የውሃ እቃ ላይ አንድ ጠፍር ፈቶ ራሴን ማንጠልጠል … የሞቴ እለት ደግሞ የሰረጌ ዋዜማ ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡ ወላጆቼ የሚደግሱት ድግስ ቢያንስ ለሀዘነተኛ እንዲሆን፡፡ ቢያንስ ከእነሱ ፀፀት የሚማር ቢኖርም የሚል ተስፋ አድሮብኛል፡፡…"
> (እነዬ፣2002፣47)

ማህበራዊ መብቶቿን ባለማወቋ ይህንን ችግር እልባት ልትሰጠው ያቀደችው እራሷን በማጥፋት ነበር፡፡ ባላወቀችው ምክንያት ሰርጉ መሰረዙ በጃት እንጂ የጠፍር እራት ይሆን ነበር ፍፃሜዋ፡፡

አዲስ አበባም ከመጣች በኋላ በብዙ የህይወቷ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ሰዎች ውሳኔ ሲያሳልፉ እምብዛም ስትቃወም አናያትም፡፡ የውሳኔያቸውን ገፈት እየተጋተች በዝምታና በእንባዋ ብቻ ከአንዱ ቀጣሪ ወደሌላው እያለች ችግሮቿን ለመወጣት ትጥራለች፡፡ የቀጣሪዎች ብቻ አይደለም ፈተናዋ የማታ ትምህርቷን ስትከታተል ያፈራቻቸው ጓደኞቿም ሌላ ችግር ነበሩ፡፡ የቀጣሪዎቿ ልጅ የነበረው አብላንተ ሙሉ ትኩረቱን እሷ ላይ ማድረጉ አስቀንቷቸው ጫና ሲፈጥሩባት ምንም ምላሽ አትሰጥም ነበር፡፡ በአሽሙር ሲጎነትሏት፣ በግልፅ ስድብ ሲያጣድፏት እንዲሁም ተባብረው በጨለማ ሲደበድቧት ተገቢና ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እየቻለች በመፍራቷ ምክንያት ለማድረግ አልቻለችም፡፡

> "… ፈትለ ወርቅ እግሬን ጠልፋ ሁለታችንንም ከመሬት አገናኘችን፡፡ ከዛ በኋላ ቀሪ አቅም አልነበረኝም፡፡ እየተጋገዙ የሚያወርዱብኝ ዱላ መቀበል ብቻ ነበር ምርጫዬ፡፡ ሰርካለም ግን ከእጇና ከእግሯ በበለጠ የተጠቀመችው በጥርሷ ነበር፡፡ ከተለያየ ቦታ እንደ አጥንት ስትነጨኝ ደሜ ከዚህም ከዚያም መፍለቅ ጀመረ፡፡ ደግነቱ እነሱው እየደበደቡ እነሱው ይጮሁ ስለነበር ገላጋይ ጠሩልኝ፡፡ ከየት

እንደመጡ እንጂ ፖሊሶች ደርሰው ህይወቴን አተረፏት፡፡…" (እነዬ፣2002፣ 210)

ከጓደኞቿ ድብደባ ካስጣሏት ፖሊሶች መካከል አንደኛው ህክምና እንድታገኝ ካደረግ በኋላ ክስ እንድትመሰርት ጠይቋት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ "ክስ" የሚለውን ሀሳብ በፍርሀቷ ምክንያት ልትቀበለው አልቻለችም፡፡ በራሷ ላይ ያላት እምነት ዜሮ መሆኑና ተደጋጋሚ ስነልቦናዊ ጉዳቶችን ማስተናገዷ ሰዎች እሷ ላይ የሚወስዱትን አሉታዊም ሆነ አወንታዊ እርምጃ እንደመብታቸው አድርጋ ትቆጥረዋለች፡፡ ይህ ደግሞ ካለመማር የሚመጣ እራስን ዝቅ የማድረግ ችግር ነው፡፡ በአጠቃላይ አለመማሯ የተማሩ ሴቶች ሊውሉባቸው የሚችሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ ሥራዎችን እንዳትይዝ ስላደረጋት ለመኖር ስትል የሰው ቤት አገልጋይነትን ተቀላቅላለች፡፡

### 3.1.3. ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና

በዚህ ንኡስ ርእሰ ጉዳይ የምንመለከተው ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊውን ጫና መቋቋም አቅቷቸው የሰው ቤት አገልጋይ ለመሆን የተገደዱ ገጸባህሪያትን ነው፡፡ በዚህ ጥናት የተካተቱ ሁሉም ገጸባህሪያት ይህ ጫና ለሰው ቤት አገልጋይነት የዳረጋቸው ናቸው፡፡ ራሔል ዳርጌ፣ ፅዮን ታምሩና ነፃነት ክብረት ያሉበትን አስከፊ የጉስቁልና ህይወት ለማስተካከል ልዩ ልዩ አማራጮችን የሚሞክሩና በዚህም ተስፋ የነበራቸው፤ በብዙ መንገድ አስከፊ የነበረውን ቤተሰባዊ ህይወታቸውን ወደ በጎ መስመር መምራት የሚያስቡ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ ባሰቡት ልክ እንዳይራመዱ ቤተሰባቸውና ማህበረሰባቸው ያስከተለባቸው ጫና እንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡ ሶስቱም ባለታሪኮች ለማህበረሰቡና ለቤተሰባቸው ጎጂ ልማድ ዋጋ ከፍለዋል፡፡ ከአቅም በላይ ሲሆንባቸውም ማህበረሰቡንና ቤተሰባቸውን ሽሽት የሰው ቤት አገልጋይ ለመሆን የተገደዱበትን ሁኔታ እናነባለን፡፡

#### 3.1.3.1. ቢስ ራሔል

ደራሲ ፀሐይ መልአኩ የዚህን ልቦለድ ገጸባህሪያት ስትቀርጽ ነባራዊውን ዓለም መነሻ እንዳደረገች የምንረዳባቸው ምስክሮችን ከታሪኩ ውስጥ ለመጥቀስ አንቸገርም፡፡ በኛ ማህበረሰብ ተለምዶ ታሪኩ በቀረበበት ጊዜና ሁኔታ ውስጥ የምናገኛቸውን ገጸባህሪያት በነባራዊው ዓለም ፈልገን የምናጣቸው አይደሉም፡፡ ለዚህም ደራሲዋ የህይወት ልምዷን፣ ቅኝቷንና ትዝብቷን በመጠቀም ገጸባህሪያቱን ቀርጻቸዋለች ለማለት ይቻላል፡፡

በልቦለዱ ውስጥ በራሔልና በቤተሰቦቿ ውጫዊ ውበትና በጎ ምግባር እንዲሁም ታታሪነት እየተሳቡ ሰፊ አላማ ይዘው የሚቀርቧቸው ሰዎች በሙሉ "የስጋ ደዌ በሽታ ተጠቂ" ናቸው በሚለው መሰረተ ቢስ ወሬ በቅጽበት ሲለዩዋቸው እናነባለን፡፡ ሌላው ቀርቶ ለአራት አመታት የራሔል ፍቅረኛ የነበረው ኤፍሬም ወሬውን እንደሰማ ሲለያት ደቂቃዎችን መፍጀት አልፈለገም፡፡ ይህ ደግሞ ማህበረሰባችን በተጠቀሰው የልቦለዱ ዘመን አይደለም ዛሬም ድረስ "የስጋ ደዌ" በሽታ ቁጣና መአት እንጂ በህይወት አጋጣሚ የሚከሰትና ታክሞ መዳን የሚችል በሽታ እንደሆነ አለማወቁን እንድናስተውል አድርጋለች፡፡

የራሔልን ማህበረሰባዊ ትግል የምናነበው ገና ታሪኩ ሲጀምር ነው፡፡ የነራሔል ጎረቤት የሆነችው  አሰገደች ወልዴ በአረቄና በጠላ ንግድ የምትተዳደር ታታሪ ሴት ናት፡፡ በአንድ ወቅት ቤቷ እየተመላለሰ የነበረ ጠጪ ሰብእናው ማርኳት ከዛሬ ነገ ለፍቅር ጓደኝነት ጠይቆኝ አብሬው እሆናለሁ ብላ ስታስብ የሱ ቤቷ የመመላለሱ ዓላማ ለመጠጣትም ሆነ እሷን ፍለጋ ሳይሆን ጎረቤቷን ራሔልን ፍለጋ መሆኑንና ለዚህም እንድታግዘው እሷን እንደ አማላጅ ማሰቡን ከነገራት ጀምሮ ልዩ ልዩ አጋጣሚዎችን እየፈጠረች ራሔልን መተንኮስ፣ በፊት ለፊት መሳደብ፣ ጓደኛዋ እንድትለያት ተጽእኖ መፍጠር፣ የአራት ዓመታት ፍቅረኛዋን ኤፍሬምን ጨምሮ ሌሎች እሷን ለፍቅር ጓደኝነት የሚቀርቧትንና ህይወቷን ሊቀይሩላት የሚችሉ ሰዎች እንዲሸሿት ታደርግ ነበር፡፡ ለሚመለከታቸውም ሆነ ለማይመለከታቸው ሰዎች "ከዘር የተወረሰ የስጋ ደዌ" በሽታ ተጠቂ ናት እያለች በማስወራት ብዙ ችግሮችን እንደፈጠረችባት ከታሪኩ እንረዳለን፡፡

> "… ነገሩ ገብቶኛል እባክሽ! … ይልቅ፣ ከማይላቀቀው ጠንቅ ውስጥ ገብቶ እንዳይዘፈቅ መካሪ ቢያገኝ ጥሩ ነበር፡፡ ይኸው ቀይ ቆዳዋ ማርኮት ይሆናል በሰበብ አስባቡ የተጠጋት፡፡ ይልቅ ምከሪው ታውቂው እንደሆን … ምነው እኔ ባወቅሁት … ተዝቆ ከማያልቅ ችግርና ጠንቅ ሳይነከር አድነው ነበር፡፡ … የሚወድቅበትን መከራ ያላወቀ አሳዛኝ ሰው ነው … ወደድኩ ብሎ ሲመላለስ የነበረውን ያንን የኮሌጅ ተማሪ እንዳዳንኩት ይሄንንም አድነዋለሁ … ፍርጥርጥ አድርጌ ነገርኩት፡፡ ያንን የመሰለ ልጅ ገደል ሲገባ ዝም ብዬ ማየት የለብኝም፡፡ እኔ አሰገደች እንዳንቺ መሰልኩሽ መሰሪነት የለብኝም … ጉዳዩን (የራሔልን ቢስ ገላነት) ከስር መሰረቱ የሚያውቅ ነው የነገረኝ … የኛ አቡካቶ፡፡ እንዳቅምሽ የጓደኛሽን ነውር መሸፈንሽ ነው፡፡

> ድንቁም መሸፈን … ፀሐይ የሞቀው አገረ ያወቀው ነገር
> ነው … ገባሽ?" (ፀሐይ፣1996፣22-23)

ይህም ብቻ አይደለም የራሔል ቤተሰቦች የስጋ ደዌ በሽታ ተጠቂዎች ናቸው የሚለው ያልተረጋገጠ ወሬ ከብዙ ማህበራዊ ግንኙነት አሸሽቷቸዋል፡፡ ማህበረሰቡ አንድን የተናፈሰ ወሬ ትክክለኛነቱን ከማረጋገጥ ይልቅ በሰው ህይወት ላይ አሉታዊ ሚና ቢኖረውም እንኳን በሰማበት ቅጽበት አምኖ በመቀበል ተገቢ የማይባሉ እርምጃዎችን ሲወስድ ከዚህ ልቦለድ ታሪክ እንረዳለን፡፡ የነራሔል ጎረቤቶች ባላጣሩት ወሬ የቤተሰቡን ሕይወት ሲያመሳቅሉ፤ በቁምነገር ለዘላቂ የህይወት አጋርነት የተመኟት ወንዶች ሁሉ እንዲሸሿት ሲያደርጉ፤ በቤተሰቡ ላይ ድህነት ያደረሰው መጎሳቆል ሳያንስ የሰፈር ሰዎች ሲወጡና ሲገቡ በሚያደርሱባቸው ስነልቦናዊ ጥቃት ባይተዋርነት ይሰማቸው ነበር፡፡

> "ወ/ሮ ጠጄና ልጆቻቸው ለበርካታ ዓመታት በኖሩበት መንደር ከአካባቢው ሰው ጋር የሚገናኙት ወይም መንደረተኛው የሚቀርባቸው ጎላ ብሎ የሚታይ የደስታ ወይም የችግር ጊዜ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ችምችም ባለው የመኖሪያ መንደር ውስጥ ብቸኛ ነበሩ፡፡"
> (ፀሐይ፣1996፣101-102)

እነዚህ ማህበረሰባዊ እንከኖች በራሔል እና በቤተሰቦቿ ላይ ያደረሱት ቀላል የማይባል ጫና እስከምን እንደሆነ በጥልቀት ተተርኳል፡፡ ብቸኛው ወንድና የበኩር ልጃቸው ጎሹ በዙሪያው ያሉ ሰዎችን ትችትና ጥላቻ ፈርቶ ለስምንት ዓመታት ከእናቱና ከእህቶቹ ተለይቶ ኖሯል፡፡ ሚስቱ ካረገዘች በኋላ ጽንስ ለማቋረጥ እስከታስብ ድረስ ይህ ወሬ የትውልድ ከተማውን ትቶ የሄደበት ሐረር ድረስ ተከትሎት በመሄድ ክፉኛ ትዳራቸውን ረብሾት ነበር፡፡ በሚስቱ ብርታት እስከተስተካከለ ድረስም ውስጥ ውስጡን በናፍቆታቸው እየተብሰለሰለ እናቱንና እህቶቹን ለማግኘት ይቸገር እንደ ነበር ከታሪኩ ተረድተናል፡፡ ወ/ሮ ጠጄም ይህ የመንደረተኛው ጫና የዘወትር ሀዘንተኛ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ነበሩ፡፡ አጠገባቸው ሆነው የኑሮ ሸክምን አብረዋቸው የተጋፈጡት ሴት ልጆቻቸውን ልፋት እያሰቡ፤ በተለይም የራሔል ሙከራዎች በሙሉ አልሳካ ሲሉ ልባቸው ስብር ይላል፡፡ ብሶታቸውን ዕለት በዕለት ለፈጣሪያቸው ከማሰማት በዘለለ ለማንም አይተነፍሱም፡፡ አንዳንዴ ብቻ አብሮ አደጋቸውና የእጃቸውን ጉዳት ትክክለኛ ምክንያት ለሚያውቁት ወ/ሮ ዳሮ ያዋዩዋቸው ነበር፡፡

> "ዳሮዬ የመልክማ ነገር ዋጋ ቢኖረው ኖሮ የኔ ልጆች አይንከራተቱም፣ አይንገላቱም ነበር፡፡ ባዶ መልክ ባዶ ነው፡፡ በዕድል በረከት ካልተሟሸ፡፡ ይኸው የምታይው ነው፡፡ ከመልክ፣ ከቁመና፣ ከሙያ፣ ከባሕሪ የጎደላቸው የለም፡፡ ልጆቼን ለትዳር የሚመኝ ግን አላየሁም፡፡ ድንቅ ይለኛል፡፡ የቡዳ፣ የቆማጣ ዘር ያለብኝ ይመስል ሰው ሸሽቶኛል፡፡ ይሂ ሕዝብ ክፉ ነው፡፡ በጥርሱ እየሳቀልኝ በልቡ ለምን እንደሚያርቀኝ ሳስበው እዝን እላለሁ፡፡ ዳሮዬ ስንት ብሶት አለኝ … ምንስ ይጠፋኛል፡፡…" (ፀሐይ፣1996፣92)

ራሔል የእለት ገቢ ለማግኘት የጉልት ንግድ ላይ የተሰማሩትን እናቷንና ታናሽ እህቷን ለማገዝም ሆነ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ተለያዩ ቦታዎች ለመሄድ ከቤቷ ስትወጣ ይህ ጫና የተለመደ ነበር፡፡ የግድ ካልሆነባቸው ከቤታቸው መውጣት አይፈልጉም፡፡ መውጣት ካለባቸው ስድቡና ነቀፌታው በግልፅም በአሽሙርም አይቀርላቸውም፡፡ የአካባቢው ጎረምሶችም ሆኑ ከስር ከስራቸው የሚሉት ህፃናት ከጎረምሶቹና ከወላጆቻቸው የሰሙትን ሀሜትና ግልፅ ስድብ እየደገሙ በጣም ያስቸግሯቸዋል፡፡ "…ቢስ…ቢስ ራሔል…ቢስ ኩባንያ…ቢስ እንደገና… እያሏት ሲሮጡና ሲደበቁ ሰምታ እንዳልሰማ ንቃቸው አለፈች…" (ፀሐይ፣ 1996፣ 33)

ራሔል የሰፈሯ ሰዎች እንዳዋከቧትና እንደተመኙላት ተስፋ ቆርጣ አልተቀመጠችም፡፡ ይልቁንም "…ከእንግዲህ ዋናው ቁም ነገሬ ሰው መሆን ነው፡፡ በዚህ በናቀኝ ሰውና ህብረተሰብ መካከል ሰው ሆኜ መገኘት አለብኝ፡፡…" (ፀሐይ፣ 1996፣ 17) በሚል እልህ እራሷንና ቤተሰቧን ከተጫናቸው ድህነት ለማላቀቅ ቆርጣ ስትነሳ ታሪኩ ይነግረናል፡፡ ይሁን እንጂ ከ12ኛ ክፍል በላይ መቀጠል ባለመቻሏ እሷ እንዳሰበችው የትኛውንም አይነት የቢሮ ሥራ አግኝታ የቤተሰቦቿን ኑሮ መደገፍ አልቻለችም፡፡ በዚህ ዙሪያ የምታደርገው ተደጋጋሚ ሙከራዋ ስለከሸፈም በደላላ አማካኝነት በኬኒያ አምባሳደር መኖሪያ ቤት ውስጥ በአገልጋይነት ተቀጠረች፡፡

በዚህ የሥራ መስክ ውስጥ ከተሰማራች በኋላ የዋናውን ቤት ልዩ ልዩ ክፍሎችና ጊቢውን ከማጽዳት ጀምሮ ተጨማሪ የመስተንገዶ ሥራዎችን እንድትሠራ ይደረግ ነበር፡፡ ራሔል ከየቀኑ አድካሚና አሰልቺ ሥራዋ ይልቅ በየወሩ የምታገኘው 100 /አንድ መቶ/ ብር ደመወዝ ቤተሰቦቿን ለማገዝ ያስቻላት ነበርና ሥራዋን በትጋት ትወጣ ነበር፡፡ ይህም

ጥረቷ በአማባሳደሩ ቤተሰቦችና በእንግዶቻቸው ስለተወደደ ጉርሻ እየሰጡ ማበረታታቸውን ቀጠሉ፡፡

ጉርብትናዋንና ጓደኝነቷን አስባ ደመወዝ ሲሰጣት ትናንሽ ስጦታዎችን የምታበረክትላቸው አሰገደች ወልዴና ቀለሚ ግን ሥራዋን "...ግርድና ነው፡፡ ደመወዙም የሚረባ አይደለም፡፡ ይሁን ከማጣት ይሻላል... አሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ከተማሩ በኋላ ገረድ መሆን ውርደት ነው፡፡ መቼም ከምንም ምናምን ይሻላልና ግርድና ተቀጥራለች..." (ፀሐይ፣ 1996፣ 54-56) እያሉ ቢያጣጥሉባትም ጥንካሬዋን መፈታተን አልቻሉም፡፡ ይልቁኑም "አዎ ከመቀመጥ ይሻላል...ምናልባትም በዚህ ሰበብ ከሰውም ከመ/ቤቶችም ጋር መተዋወቅ ይቻልና የተሻለ ሥራ ማግኘት ይመጣል...መቼም ተስፋ አልቆርጥም..." (ፀሐይ፣ 1996፣ 55) በማለት ያለችበትን ሁኔታ ማጣጣላቸው በእሷ ህይወት ላይ የሚያመጣው ለውጥ እንደሌለ በተግባር ታሳያቸው ነበር፡፡

ራሔል ለራሷ የነበራት አመለካከት ጠንካራና ነገን በተሻለ ለመለወጥ የምትጥር በመሆኗ የአካባቢው ሰዎች የሚያደርሱባትን ጫና ሁሉ ተቋቁማ ለምታስበው ግብ መድረስ ችላለች፡፡ ስድባቸው ለጊዜው አንገት ቢያስደፋትም፣ የፈለገችውን ያክል የጉርብትናና የጓደኝነት ህይወትን እንዳታጣጥም ቢያደርጋትም ማህበረሰባዊ ድርጊቱ የፈጠረባት እልህና ቁጣ የተሻለ ህይወትን እንደታልምና ተግባራዊ እንድታደርግ መነሻ ሆኗታል፡፡

### 3.1.3.2. የደራሲዋ ፋይል

በደራሲዋ ፋይል ዋና ገጸባህሪ ፅዮን ታምሩ ላይ የሚደርሰው ተጽእኖ የሚጀምረው ከአባቷና ከእናቷ ነው፡፡ ገና በልጅነት እድሜዋ ከአባቷ ስር ስር በማለቷ ውስጧ የሰረፀው የስነጽሁፍ ፍቅር ታሪኩ ተጀምሮ እስኪያልቅ ለበርካታ የህይወት ምስቅልቅሎሽ ዳርጓታል፡፡ አባቷ የሳቸውን የጉስቁልና ኑሮ በማየት ልጃቸውን ከዚህ እንድትታቀብ አላደረጓትም፡፡ ይልቁንም የህይወት ፍልስፍናቸውን እየሰበኩ "እሳቸው ብቻ ትክክል ናቸው፡፡" ብላ እስክታምን ድረስ የአስተሳሰባቸው ተገዢ ሆነች፡፡

ዋናዋን ገጸባህሪ ፅዮን ታምሩን በታሪኩ ውስጥ ከተከሰተችበት የመጀመሪያ ገፅ ጀምሮ ሙሉው ልቦለድ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የተቀረፀችበት ሂደት አሳማኝና እንዴት ይሆናል የሚያስበል ሁኔታ የለበትም፡፡ ከአባቷ ጋር በነበራት ጥብቅ ቁርኝት የተነሳ ለእሳቸው በአምልኮ ደረጃ የሚገለፅ ፍቅር እንዳላት አንብበናል፡፡ ይህ የአባትና የልጅ ፍቅር ገና

ማመዛዘን በማትችልበት እድሜ ላይ እያለች የሰረፀባት በመሆኑ አባቷ በሳቸውም ላይ ሆነ በቤተሰባቸው ህይወት ላይ የሚፈፅሙትን ስህተት ለመመልከት እንኳን አልቻለችም፡፡ በጭፍን የሳቸው ደጋፊ ሆና ከእናቷና ከሌሎች ሰዎች ጋር ስትጣላላቸው እናነባለን፡፡ ይህ ሚዛናዊ ያልሆነ አቋሟ ግን ባታስተውለውም ወደ ጥልቅ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና ነው የከተታት፡፡

የቤተሰቡ ብቸኛ የገቢ ምንጭ የነበሩት አባቷ ባደረባቸው የስነጽሁፍ ፍቅር ምክንያት ለዘርፉ ብዙ ውድቀት ተዳርገው ቤተሰባቸውን መመገብ እንኳን አቅቷቸው እንደ ነበር ከታሪኩ እንረዳለን፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ዘርፉ ብዙ ኪሳራ ለጥበብ እንደሚከፈል ዋጋ በመቁጠር ልጃቸው የሳቸውን ውድቀት እንዳትደግም በማስተዋል አልመረጡትም፡፡ ይልቁንም በዚሁ መስመር እንድትጓዝ ዘወትር ያበረታቷት ነበር፡፡

> "እኔን መስለሽ እንደወጣሽ ገና ልጅ ሳለሽ አይቻለሁና፣ ለስነጽሁፍ ያለሽን ተሰጥኦና ፍቅርም አውቄዋለሁና የሚሰማኝን የከንቱነትና የባዶነት ስሜት ይቀንሰዋል፡፡ … በህይወት ውስጥ ትዳር መመስረት፣ ልጆችም መውለድ እንደ ሂሳብ በቀመር ሊሠራ ይችል ይሆናል፡፡ ያም ሆኖ ግን ለተሰጥኦ ጥሪ ተገቢውን መልስ መስጠት ካልተቻለ ሁሉም ባዶ የሆነ ያህል ነው የሚሠማ፡፡" (የዝና፣ 2002፣ 6-7)

ተጨባጩን የቤተሰባቸውን የጉስቁልና ኑሮ ምክንያትና ውጤት መዝና ከአባቷ ፍላጎት ከመሸሽ ይልቅ እንደ ወረደ የአባቷን ህልም ለመጋራት ትሞክር ነበር፡፡ በዚህም በህይወቷ ብዙ ዋጋ እንድትከፍል ያደረገ ምስቅልቅል ውስጥ ለመግባቷ ምክንያት ሆነዋል፡፡

ይህንን እውነት የተገነዘበው አባቷን ከሷ በፊት የሚያውቃቸው ፍቅረኛዋ ግረማም በጣም ይናደድባቸው ነበር፡፡

> "…በተለይም ለአባቷ ያላት አመለካከት የተዛባና ጭፍን ነው ስለሚል ይሄንን ማስወገድ ቢችል በህይወቷ ውስጥ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ያስባል፡፡ ልጅ ሳለች ከልጆች ጋር እንዳትቦርቅ ጓደኛ አድርገዋት፣ ወጣትነቷንም ነጻ ሆና እንዳትኖረው ሲሰክሩ በየመንገድ በሚሆኑት እያፈረች ለብቸኝነት ዳርገዋት፣ ያለ አቅሟ እሳቸውን ለመንከባከብ ስትጨነቅ እንድትኖር ምክንያት ሆነው የህይወት ግንዛቤዋን

አዛብተውባታል ስለሚል አባቷን ስለራሱ ከሚወዳቸው ባሻገር ስለ እሷ ይናደድባቸዋል፡፡…" (የዝና፣ 2002፣ 125)

ይህን ሁኔታ ግን በምንም ልትገነዘበው አልቻለችም፡፡ ይልቁንም ለቤተሰቡ ሰላም ማጣትና ለአባትየው ጠጪ መሆን ምክንያት እምታደርገው እናቷን ነው፡፡ ይህ አስተሳሰቧ ደግሞ ርቀታቸውን እያሰፋው በእናትና ልጅ መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅርበት እንዲኖር አላደረገም፡፡ የአባትየው ተፅእኖና የእሷም ብስለት አልባ መሆን በጭፍን እንድትወዳቸውና "ትክክል" ናቸው ብላ እንድታስብ ብሎም እሳቸውን ብቻ እንድትደግፍ አድርጓታል፡፡

አቶ ታምሩ በህይወት እያሉ የቤታቸውን ጉድለት መሸፈን ስለማይችሉ ከባለቤታቸው ጋር በየቀኑ የሚጣሉ ሲሆን እሷም በባልና ሚስቱ መካከል ዘወትር ለሚፈጠረው ጠብ ምክንያት የምታደርገው እናቷን ብቻ ነበር፡፡ እናቷ ከትምህርት ደረጃቸውም ሆነ ካዳበሩት የኑሮ ልምድ ተነስተው ትክክል ነው ብለው የሚያስቡት የየቀኑን መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ስለመሟላቱ ብቻ ነው፡፡ ይህንን ከመረዳትና ማድረግ የምትችለውን ከማድረግ ይልቅ አባቷ ስር በመሸሸጓ እናቷ እንዲጠሏትና ተስፋ እንዲቆርጡባት ሆነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከእናቷ ያገኘችው የእናትነት ፍቅራቸውን ሳይሆን የዘወትር ጭቅጭቅና ጥላቻቸውን አልፎ አልፎም አካላዊ ቅጣታቸውን ነበር፡፡

"… ሴት ልጅ ልትሰራው ይገባታል ብለው የሚያምኑትን የቤት ውስጥ ሥራ ፅዮን እርግፍ አድርጋ ትታ ከትምህርት ቤት መልስም እንደ አባቷ ስታነብና ስትፅፍ ማምሸቷን አልወደዱትም፡፡ በዚያም ላይ የአባቷን ስሜት የተንከባከበች እየመሰላት በቤት ውስጥ ያለውንም ሆነ የሚዘጋጀውን ጥሩ ነገር ሁሉ ለአቶ ታምሩ እንዲሆን ስለምትፈልግ እናቷን ያናድዳቸዋል…" (የዝና፣ 2002፣ 9)

ከእናትና ከአባቷ ጋር ያላት ግንኙነት ከእሷ እድሜ በሚጠበቀው ልክ ደስተኛ የሆነችበት አልነበረም፡፡ በቤተሰቧ ውስጥ ያዳበረቻቸው የህይወት ልምዶች ፍርሀትንና ብቸኝነትን የምታስተናግድባቸው፣ የወደፊት ህይወቷን በጥርጣሬ የምትመለከትባቸው እንዲሁም ከሰዎች ጋር ያላትን ግንኙነት እርግጠኛ ሆና እንዳትመራ የሚያደርጓት ነበሩ፡፡ እነዚህን ስነልቦናዊ ጉዳቶች ይዛ ለቀጣይ ህይወቷ የሚጠቅሙ ተግባራትን ብትሞክርም ሲሳኩላት አናይም፡፡

ለአባቷ ያላት ሚዛን አልባ ድጋፏም በህይወቷ ላይ ትክክል የማይባል ውሳኔ እንድትወስን አድርጓታል፡፡ በሕይወት የመኖር ዓላማ ለእሳቸው ያልሰመረላቸውን የደራሲነት ተልዕኮ ከግብ ማድረስ ነው ብላ ለራሷ በመንገር እያንዳንዱ እንቅስቃሴዋን ከጽሁፍ ሥራዋ ጋር ብቻ እንዲዛመድ አደረገችው፡፡ አባቷ በሞቱ በጥቂት ወራት ልዩነት የተቀላቀለችውን ዩኒቨርሲቲም ትምህርት ለመማሪያ ሳይሆን የድርሰት ሥራዋን ብቻ ማከናወኛ አድርጋ ስለወሰደችው በመጀመሪያ ሴሚስተር ውጤቷ ስትባረር ብዙም የተገረመ አልነበረም፡፡

ከዩኒቨርሲቲ ወጥታ ወደእናቷ ቤት ስትገባ የድርሰት ሥራዋን አልተወችምና ከእናቷ ጋር ለነበራት አለመስማማት መነሻም ጭምር ሆነ፡፡ ይህ ደግሞ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እንድትጋፈጥ አድርጓታል፡፡ የየእለቱ የእሷና የእናቷ ግንኙነት በፀብና ክርክር የተሞላ ነበር፡፡ በተለይም ከዩኒቨርሲቲ ተባራ እቤት ስትውል እንደሳቸው ፍላጎት ሥራ ፈልጋ ገቢ ከማግኘት ይልቅ ወረቀት ላይ ማቀርቀሯ የሚዋጥላቸው ጉዳይ አልነበረም፡፡ “ባዶ ወረቀት ብትጭሪው ብትጭሪው ምን ይሰራልሻል ልጄ? ወጣ ወጣ እያሉ ሥራ መፈለግ አይሻልም?...” (የዝና፣ 2002፣ 136) በማለት ምክር ቢጤም ጣል ቢያደርጉላት ለውጥ ማየት አለመቻላቸው እኔን አትሰማኝም ወደሚል መደምደሚያ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን ለመፃፍ በሚል ለሊት እየተነሳች መቀመጧና መብራት መጠቀሟ ከጎረቤቶቻቸው ጋር በጋራ ከሚጠቀሙት የመብራት ቆጣሪ ጋር ተያይዞ ችግር እንዳይስከትልባቸው ይሰጋሉ፡፡ ይህን ስጋታቸውንም ሆነ ለእሷ የሚመኙትን ሥራ ይዛ ገቢ የማግኘቱን መሰረታዊ ነጥብ ጥበባዊ በሆነ የእናትናት አቀራረብ አያስረዷትም፡፡ መናገር የሚፈልጉትን ጉዳይ ዘወትር የሚያቀርቡት በቁጣና በጩኸት ስለሆነ የእናትና ልጅ ግንኙነት በየቀኑ እየሻከረ ነበር የሚሄደው፡፡

> “…ወጣ ወጣ እያለች ሥራ አትፈልግም፤ ከጓደኛ ከዘመድ ቤትም አትሄድም፡፡ ሌሊት ከእንቅልፋቸው ሲባንኑ እንኳ መብራት አብርታና ወረቀት ላይ አቀርቅራ ብዙ ቀን አግኝተዋታል፡፡ የመብራት ቆጣሪም ከጎረቤቶቻቸው ጋር የጋራ ስለሆነ ነገር እንዳይመጣባቸው ፈርተዋል፡፡ ቢቸግራቸው ‹እየወጣች ሥራ እንድትፈልግ ምከራት› ብለው በተደጋጋሚ ለግርማ ነግረውት ነበር፡፡ ሆኖም ለውጥ ባለማግኘታቸው ‹ይህች እንደ አባቷ መላ ቢስ፤ ግራ› እያሉ ማጉረምረም ከጀመሩ ውለው አድረዋል፡፡ በትንሹም በትልቁም ብስጭትጭት ይላሉ፡፡…” (የዝና፣ 2002፣ 136)

በልጃቸው ሁኔታ የሚበሳጩት እናቷን ፍላጎት ልታሟላ ስላልቻለች ካለበቂ ምክንያት ጎረቤቶቻቸው ባሉበትም ጭምር ይዘልፏት ጀመር፡፡ ከእናቷ ጋር አለመስማማቷ ከቤተሰብ አልፎ ማህበራዊ ግንኙነቷም ላይ አሉታዊ ሚና አሳድሮባታል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች ለፅዮን ጥሩ አመለካከት አልነበራቸውም፡፡ አባቷ በነበሩም ጊዜ በብዙ ጎረቤቶቻቸው ዘንድ የባልና ሚስቱ ፀብ መነሻ ፅዮን እንደ ሆነች ተደርጎ ስለሚታሰብ "ባለጌ" ብሎ መጠሪያ ከመለጠፍ ውጭ አሁንም በሷ ላይ የደረሰውን ጫና ቀርቦ የተረዳላት አልነበረም፡፡ በዚህም ትእግስት አጥታ ከእናቷና ከወንድሟ ጋር የምትኖርበትን ቤት ጥላ ስለመውጣት ማሰብ ጀመረች፡፡

ፍቅረኛዋ ግርማ ከዩኒቨርሲቲ ተባራ ስትወጣ ከእናቷ ጋር ያላትን የሻከረ ግንኙነት በጥልቀት ስለሚረዳ አብራው እንድትኖር ጠይቋት ፈቃደኛ አልሆነችም፡፡ ሊያስገድዳት አልቻለም፡፡ ይልቁኑም የድርሰት ሥራዋ ያሉበትን እንከኖች አስወግዳ ለህትመት እንዲበቃላት ያግዛት ነበር፡፡ በመጨረሻም አጠናቅቄያለሁ ብላ የሰጠችውን ወጥ ድርሰት በጥንቃቄ በማንበብ ያሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንድታርም አስተያየት አቀረበላት፡፡ አስተያየቱን ተቀብላ ለማሻሻል ከመሞከር ይልቅ በሰጣት አስተያየት ስለተናደደች አዘናግታው ከምሽቱ አራት ሰዓት ጥላው ወደ ቤቷ ሄደች፡፡

እቤቷ ስትደርስ ግን በማምሸቷ ከእናቷ ጋር ለመደባደብ በቃች፡፡ ለማገላገል የመጡት ጎረቤቶችም "ፅዮን ሰክራ እናቷን ደበደበቻቸው"(የዝና፣ 2002፣ 150) የሚል ወሬ በማናፈሳቸው በዛ ሁኔታ ቤቷም ውስጥ ሆነ ከጎረቤት ጋር ለመኖር አቅም አልነበራትም፡፡ ራቅ ብላ ሄዳም ችግሩን ለማሳለፍ የምትችልበት ዘመድ የላትም፡፡ ለጊዜው ብላ ሻንጣዋን ይዛ የገባችበት የጓደኛዋ ቤተሰቦችም "ሰክራ እናቷን ደበደበቻቸው" በሚለው ወሬ ምክንያት ፊት ነስተዋታል፡፡

ጓደኛዋ ብዙነሽም ከአሁን በፊት ሥራ ያሲዙሻል ብላ ያገናኘቻት አቶ አሻግራቸው ለወሲብ ጥያቄያቸው በቀላሉ ፈቃደኛ ስላልሆነችላቸው ጨዋነቷን አድንቀው በሷ ላይ ያላቸው ፍላጎት እንደ ጨመረ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅማ ገለፀችላት፡፡ ባለችበት ሁኔታም ውስጥ ቢሆን ሴትነቷን እንደ ገቢ ምንጭ ማሰብ ስለማትፈልግ ከብዙነሽ ጋር ያላት ግንኙነት በዚህ ምክንያት ወደ መበጠሱ ደረሰ፡፡

እጮኛዋ ግርማ በምሽት አዘናግተው ጥላው መሄዱ በጣም ስላናደደው በቀጣዮቹ ቀናት ተፀፅታ ስትደውልለት “ሥራ ላይ ነው” በማስባል ሊያገኛት አልፈለገም፡፡ ይህ የሱ ሁኔታ ሞራሏን ከመንካቱም በተጨማሪ እልህ ውስጥ ከተታት፡፡ እናቷም ቢሆኑ ለሁለት ቀናት ከሳቸው ተለይታ ጓደኛዋ ቤት መሆኗን እያወቁ እንድትመለስ አልጠየቋትም፡፡ ይህ ደግሞ ተግባራዊ ለማድረግ ፈርታ በውስጧ ስታስበው የነበረውን የሰው ቤት ሠራተኛነት ጉዳይ እንድትወስን አደረጋት፡፡

> “…ግርማ ሊያናግራት እንኳ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ እናቷ በሁለት ቀን ውስጥ ብቅ አላሉም፡፡ ብዙነሽም ስሜቷን ስላልተረዳችላትና ጭንቀቷን ስላልተጋራቻት ወደ ቤታቸው ተመልሳ መሄድ አስጠላት፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ገብቷት እንደቆየች… ወደ ፈራችው ግን አማራጭ ወደ አጣችለት የሰው ቤት ሠራተኛነት…” (የዝና፣ 2002፣ 154)

ፅዮን ያለችበትን ሁኔታ የምትቋቋመው ስላልመሰላት ለጊዜው አማራጭ የመሰላትን ትልቅ ውሳኔ በህይወቷ ለማሳለፍ ተገዳለች፡፡ ይህንን ውሳኔዋንም ለማንም ሳትናገር በደላላ አማካኝነት የሰው ቤት አገልጋይ ለመሆን በቅታለች፡፡

በተወለደችበት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እየኖረች፣ ከእናቷና ከወንድሟ ጋር ተስማምታ መኖር እየቻለች፣ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ቆይታም ቢሆን መቀጠል እየቻለች፣ አይዞሽ ባይ አክባሪና ፍላጎቷን የሚረዳ ፍቅረኛ እያላት ለምን ለሰው ቤት አገልጋይነት በቃች? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ከላይ በተብራሩት መነሻዎች ከማህበረሰባዊው አመለካካትና ከትእግስት አልበኛነቷ የሚመነጭ ነው፡፡

ዓመት ከመንፈቅ አካባቢ የቆየችባው ሁለት የተለያዩ ሰዎች መኖሪያ ቤት ሲሆን በሁለቱም ቤቶች ውስጥ ያሳለፈችው የማይገናኝ ህይወትን ነበር፡፡ በመጀመሪያ የተቀጠረችባቸው ቤተሰቦች ገና ወደ ጊቢያቸው ስትገባ ነበር በሷና በነሱ መካከል የነበረው የኑሮ ልዩነት የገዘፈባት፡፡

> “…ለመናፈሻ ይቅርና ለመተንፈሻ እንኳ ጓሮ ሳይኖራቸው ለኖሩ ሰዎች፤ አንድ ቤተሰብ እንደዛ በመሰለ ጊቢ ይኖራል ብሎ ለመገመት ቀላል አይደለም… እሷ የኖረችበት ሰፈር ሰዎችና እዚህ ጊቢ ውስጥ ያሉ ሰዎች እንዴት የአንዲት አገር ዜጎች ተደርገው ሊታሰቡ እንደሚችሉም ግራ ገባት… ይህንን ቤተሰብ

ለማገልገል የመቻሏ ብቃት አጠራጥሯት መንፈሷ ተረበሸ፡፡… ”
(የዝና፣ 2002፣ 159-160)

በዚህ የኑሮ ልዩነት እንደ ተደናገጠችና ልዩነቱንም ማመን እንደ ከበዳት የተቀላቀለቻችው የቤተሰብ አባላት አብራቸው መኖር ከጀመረች በኋላም በቶሎ እንግድነቷ ሊለቃት አልቻለም፡፡ የኩሽና መገልገያ እቃዎቻቸው በአይነትም ሆነ በጥራት ስለመኖራቸውም የማታውቃቸው ነበሩ፡፡ ቤተሰባዊ የቤት ሥራ ልማዳቸውም ሌላ መደናገር ውስጥ የከተታት ሁኔታ ሲሆን ምግብ ሲዘጋጅ፣ ቡና ሲፈላ፣ እቃ ሲታጠብ፣ ቤት ሲፀዳ እሷ እምታውቀውና እነሱ እንዲሆን የሚፈልጉት እጅግ በጣም የተራራቀ ነበር፡፡

ከዚህም በላይ ግን በዋናነት የከበዳት ውላ ስታድር የተገነዘበችው አምስት አባላት ያሉት ቤተሰብ የእርስ በርስ ግንኙነት ነው፡፡ አባትየው ለቤተሰቡ የበኩር ልጅ ለሆነችው የእንጀራ ልጃቸው እንጂ ለባለቤታቸውም ሆነ ለሁለቱ ልጆቻቸው ግድ የላቸውም፡፡ ባልና ሚስቱ ሲጋቡ እርጉዝ አንደነበሩ ደብቀው ስላገቧቸው በሚስታቸው ላይ የያዙትን ቂም አባቴ ብላ በምትወዳቸው ልጅ ላይ አስነዋሪ ድርጊት በመፈፀም ይበቀሉ ነበር፡፡ ይህን ድርጊታቸውን ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ልጅቷም ተቀብላዋለች፤ እናትየውና ብቸኛ ወንድ ልጃቸውም ያውቃሉ፡፡ አስደንጋጩ ነጥብ ግን የማስተካከያ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ሁሉም በየፊናቸው የአፈንጋጭነት ኑሮውን መቀጠሉ ነበር ለፅዮን እንቆቅልሽ የሆነባት፡፡ ይህንን ቤተሰባዊ ነውር ያልተረዳቸው የመጨረሻዋ ልጅ ቬሮኒካ ብቻ ስትቀር የተቀሩት በሙሉ በፅዮን ላይ የየራሳቸውን ጫና ይፈጥሩባት ነበር፡፡

“ሁሉም ባለባቸው ስነልቦናዊ ጫና ስለሚረበሹ ይሆናል” ብላ ለመረዳት ብትሞክርም እነሱ ግን ከሰውም ሳይቆጥሯት ግራ የሚያጋባ ፍላጎታቸውን ይጭኑባት ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት “አስቸኳይ ስለሆነ አሁኑኑ ይድረስ” በሚል በጊዜ የተገደበ ትእዛዝ ከሶስት ሰው የሚመጣላት ሁኔታ ነበር፡፡ የቀደመ ትእዛዝ አለብኝ ብትልም የሚሰማት የለም፡፡ ያለ ቅፅበታዊ እረፍት ቀናት እየመሹ ይነጋሉ፡፡ ከዚህ ቤት ብትወጣ የባሰ እንጂ የተሻለ ይገጥመኛል ብላ ስላላሰበች ባልገመተችው ጫና ውስጥ ሆና መኖሯን ቀጠለችበት፡፡

ቀጣሪዎቿ የየራሳቸውን ስሜት ከማዳመጥ ውጭ እንደ ሰው ቆጥረው ያለችበትን ሁኔታ አለመረዳታቸው የሰው ቤት አገልጋይነት አያያዝ ስልት እስኪመስላት ድረስ ባይተዋር ሆና ኑሮዋን ትገፋ ነበር፡፡ ይህ የማታውቀው የህይወት ገፅታ ግራ እያጋባት በምትደናበርበት

ወቅት አንድ ዓመት አካባቢ በኖረችበት ቤት ውስጥ የሚስታቸውን አለመኖር ተግን አድርገው የቤቱ አባወራ ሊደፍሯት ሲሞክሩ አምልጣ በመውጣት ከዚህ ቤት ለቀቀች፡፡

በአንድ ዓመት ቆይታዋ ይሆናል ብላ ካሰበችው ውጭ ያዳበረችው የኑሮ ልምድ ቀጣዩን ህይወቷን በስጋት እንድትመለከት ቢያደርጋትም ቀጥታ የሄደችው ወደ ደላላ ቤት ነበር፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የገባችበት ቤት ቀጣሪዋ በብዙ የህይወት ውጣ ውረዶች የተጎዳው ከሊል ነበር፡፡ ከሊል ቤት በቆየችባቸው የወራት ጊዜያቶች ጥቂትና መሰረታዊ የሚባሉ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ካከናወነች በኋላ የሚተርፋት ጊዜ ስለ አለ እንደምትፈልገው ለማንበብና አንዳንዴም ድርሰቶቿን ለመመልከት ችላ ነበር፡፡ ከወራት በኋላ ግን ከጠፋችው እህቱ ጋር በተያያዘ አሳዛኝ ወሬ የሰማው ከሊል ሰክሮ ገብቶ ሊደፍራት ሲሞክር ለመከላከል ስትገፋው አደጋ አድርሳበት ለመታሰር በቃች፡፡ ከአንድ ቀን የእስር ቤት አዳር በኋላ ከሊል ጥፋቱ የራሱ መሆኑን ስላመነና ክስም ስላልመሰረተባት በዋስ እንድትፈታ ተወሰነ፡፡ የታሰረችበት ፖሊስ ጣቢያ የእለት ሁኔታ መዝጋቢ ፖሊስም ከአሁን ቀደም ፎቶግራፏን አያይዞ እንደ ተሰወረችበት ያስመዘገበ ፈላጊዋን ግርማን አስጠርቶ ዋስ ሆኖ እንዲያስወጣት ካደረገ በኋላ የአገልጋይነት ኑሮዋ ይጠናቀቃል፡፡

ፅዮን ካደገችበት የህይወት ልምድ ወጥታ በአገልጋይነት በተቀላቀለቻቸው ሁለቱ የተለያዩ ቤተሰቦች ውስጥ በቀሰመችው የህይወት ልምድ የአስተሳሰብ አድማሷ ሰፍቷል፡፡ ባይተዋር እና ሆደባሻ ሆና በኖረችባቸው ሁለት ዓመታት ያልሞሉ ጊዜያት "ይህም አለ ለካ" የሚያስብሉ ገጠመኞቿ እይታዋን የተስተካከለ እንዲሆኑ አድርገውታል፡፡ አስፈሪ፣ አስጨናቂና በድብብቆሽ የተሞሉት የአገልጋይነት ወቅቶችን በተለይም ከወ/ሮ ባፈና ቤተሰቦች ጋር ያሳለፈቻቸውን ሁነቶች በቀላሉ መርሳት ከባድ ሆኖባታል፡፡ ከዛ ሁኔታ በመገላገሏም እነዚያ ገጠመኞች ያሳደሩባትን የመንፈስ ጫና በማራገፍ የህይወት ተልእኮዬ ብላ ለምታስበው የድርሰት ሥራ ሙሉ ጊዜዋን መስጠት እንዳለባት ተረድታለች፡፡ እነዚህ የአገልጋይነት ወራቶቿ የሷና የቤተሰቦቿን እንዲሁም ከሌሎች የቅርብ ሰዎቿ ጋር የነበራትን ግንኙነት እንድትፈትሽና በነበሯት የራሷ የተሳሳቱ ውሳኔዎች ዙሪያ የማስተካካያ እርምጃዎችን እንድትነድፍ አግዘዋታል፡፡

### 3.1.3.3. የገቦ ፍሬ

የዚህ ልቦለድ ዋና ገጸባህሪ ነፃነት ክብረት በምልሰት የትረካ ቴክኒክ ሙሉ ህይወቷን ሳታስቃኘን በፊት በፍርድ ቤት የተከሳሽ ሳጥን ውስጥ ሆና "… ነገዬ ሲበዛ አሳስቦኛል፡፡ ዛሬን በስቃይ ነገን በተስፋ እንደተሸከምኩ ነው ህይወቴን የገፋሁት፡፡…" (እንዬ፣ 2003፣ 10) በማለት ነበር ያለፈችባቸውን ውጣ ውረዶች ያስነበበችን፡፡ ነፃነትን በተለየ ዓይን ማየት የጀመሩት እራሳቸው ቤተሰቦቿ ሲሆኑ ምክንያት የሚያደርጉት ሁለት ዓመት ከመንፈቅ እያለች በአባቷ ስህተት ከከብቶች ጋጣ ውስጥ ወድቃ በሬ እረግጧት የአንድ እግሯ ተረከዟ ውስን ክፍል በመጎዳቱ ነው፡፡

ይህ ጉዳቷ ከእንቅስቃሴ የሚያግዳት ባለመሆኑ ከእኩዮቿ ጋር እንደልቧ እየዘለለችና እየተሯሯጠች ስለመኖሩ መሳቀቅ አይደለም ትዝ ሳይላት ህፃንነቷን አሳልፋ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በዘጠኝ ዓመቷ በመማሪያ ክፍል ውስጥ እያለች የሌላ ክፍል ተማሪ የሆነችው ቸኮለች "አንቺ! ጅብ ነው አይደል ተረከዝሽን የገመጠው;" (እንዬ፣ 2003፣ 18) በማለት አሰቃቂ በሚባል ሁኔታ ሰድባ ለሰዳቢ ከሰጠቻት በኋላ ልጅነቷን አጥታ የምትሰቃይ ገጸባህሪ ናት፡፡ ከዚህ አጋጣሚ ጀምሮ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫናው ፋታ አልሰጥ ብሎ ዘወትር እንድታዝን እስካደረገበት ጊዜ ድረስ ነፃነት የእግር ጉዳቷን እምታስታውስበት ምንም ሁኔታ አልነበረም፡፡

> "… የተረከዜ መጎዳት ብዙ የሚያስቸግረኝ ባለመሆኑ እያለ እረስቼዋለሁ፡፡ ለምንስ ላስታውሰው? ከጓደኞቼ ጋር እሮጣለሁ እጫወታለሁ፡፡ ልዩነቴን አምኖ ሰድቦኝ የሚያውቅ አልነበረም፡፡ ወላጆቼም እንኳን ምክንያቱን ሲያወሩ ሰምቼ አላውቅም፡፡ … ጉድለቴ ለራሴ ታይቶኝ አያውቅ፡፡ ለምንስ ይታየኛል; እንደ ጓደኞቼ ከመጫወት አላገደኝ! ስለ ውበት ለማሰብ አልደረስኩ…" (እንዬ፣ 2003፣ 19-26)

እንዳለ እንኳን የማታስታውሰውን ጉዳቷን ስድብ አድርገው ጓደኞቿ ሲያቀርቡት የተረጋጋው የልጅነት አለሟ ክፉኛ ተበጠበጠ፡፡ ከዚህ አጋጣሚ በኋላ ቤተሰቦቿም ሆኑ ሌላው ሰው በተለየ ሁኔታ እንደሚያያት በማመን እራሷን ከቤተሰቦቿና ከአካባቢው ማህበረሰብ በማግለል በብቸኝነት ስትሰቃይ ትታያለች፡፡ እስከ ዘጠኝ ዓመቷ ያልተገነዘበችውን እውነት በተረዳችበት ቅፅበት ልጅነቷ ጠፍቶ ህይወትን በፍርሀትና በጥርጣሬ እንዲሁም በፍራቻ የምትመለከት ታዳጊ ሆነች፡፡

የተለመደው የታዳጊነት ፍልቅልቅነቷ ጠፍቶና በዝምታ ተውጣ ወደ ቤቷ ስትገባ ባልተለመደው ሁኔታዋ የተደናገጡት እናቷ "ምን ሆንሽብኝ እናቴ? መቱሽ? ወይስ አመመሽ?" በማለት ላቀረቡላት የጭንቀት ጥያቄ ምክንያቱን መናገር አልፈለገችም፡፡ ይልቁንም "... ግማሽ ተረከዜን ጎምዶ ‹የጅብ ትራፊ! ቆራጣ! ቆማጣ!› በማስባል የሚያሰድበኝን ምክንያት ለማወቅ ጓጓሁ፡፡..." (እንዬ፣ 2003፣ 25) በሚል መነሻ የተረከዟን ጉዳት ምክንያት ትጠይቃቸዋለች፡፡ እናት ደንግጠው እያለቀሱ ምክንያቱንና ጉዳቱን ለመቀነስ ወይም ለማዳን እንደ ወላጅ የወሰዱት እርምጃ እስከ ምን ድረስ እንደነበር ይገልፁላታል፡፡ እሳቸውም ሆኑ አባቷ በቸልተኝነት ለጉዳት የዳረጓትን ያክል ለማሳከም ምንም ሙከራ አለማድረጋቸውን ከንግግራቸው ለመረዳት ችላለች፡፡

ከትምህርት ቤት ይዛው የገባችው ስድብ ሁለመናዋን እንዳናወጠውና የተለመደውን ባህሪዋን እንደቀየረው እያዩ ቤተሰቦቿ ተራ የልጅ ጠብ እንጂ የከበደ ነገር አድርገው አልወሰዱትም፡፡ የቾከለች ጥቃት ግን መጠኑን ጨምሮ ባስከተለባት መሸማቀቅ "አሞኛል" በሚል ሰበብ ከሰው ለመሸሽ ስትል ለተወሰኑ ቀናት ከትምህርት ቤት ቀረች፡፡ "... ውስጤ በታላቅ ፍርሀትና ይሉኝታ ተሸብቦ ነበር፡፡ መፍትሄ ብዬ የወሰድኩት ከሁሉም ሰው ጋር ያለኝን ግንኙነት ማቋረጥ ብቻ ነው፡፡..." (እነዬ፣ 2003፣ 39)

በመምህራን ተደጋጋሚ ሙከራ ወደ ትምህርት ቤት ብትመለስም ለነቾከለች ባደረባት ጥልቅ ፍራቻ የተነሳ የመቅረቷን ምክንያት አልገለፀችላቸውም፡፡ በራሱ ግፊትም ችግሯን ቀርቦ የተረዳላት አንድም የቤተሰብ አባልም ሆነ ሌላ አካል አልነበረም፡፡ ይልቁንም ከመምህራኖቿ የየእለት ጥሪ በተጨማሪ እቤታቸው በእንግድነት ያረፉት የህዝብ ቆጠራ ባለሙያዎች ጉትጎታ ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ አስችሏታል፡፡ "...ቾከለች በችኮላ ሰባብራ ያስቀመጠችውን ስብርባሪ መንፈሴን እንደያዝኩ ተምሬ ለነገሩኝ ሙያ መድረስ እንዳለብኝ ወስኛለሁ፡፡..." (እነዬ፣ 2003፣ 39)

ይሁን እንጂ የይህን ብርቱ ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ የምትችልበት አንዳችም እፎይታ በቤትም በውጭም አላገኘችም፡፡ አባቷና ወንድሞቿ እያንዳንዱን እንቅስቃሴዋን በጥላቻ እየተከታተሉ ጥፋት ባልሆነው ሁሉ ተወቃሽና ተቀጪ ያደርጓታል፡፡ ትምህርት ቤት ስትሄድም በቾከለች መሪነት ስርዓት አልበኛ ተማሪዎች ማሾፊያ ያደርጓታል፡፡ ይህ ደግሞ ለ11 ዓመት ታዳጊ ልጅ ሰቆቃ ነበር፡፡

> "ልጅነት ማለት በራሱ ፅናት ይመስለኛል፡፡ እኔ ግን ከዛም በላይ ፈጣሪ ለማያልቅ ችግሩ ፅኑ አድርጎ የፈጠረኝ ሳልሆን አልቀርም፡፡ እንደ አህያ ሁሉን እየቻልኩ ትምህርቴን ቀጠልኩ፡፡ የሚገጥመኝን ፈተና ሁሉ ለመቋቋም ጠንካራ ባልባልም ተስፋ መቁረጤን በበርካታ የእንባ ዘለላዎች እያጠብኩ መልሼ እገባበታለሁ፡፡ በቤትም በውጭም እየተዋከብኩ ነኝ፡፡ በዚህ ሁኔታ መዝለቅ እንደማልችል ባውቅም፣ ይህችን የተጠጋኋትን ሚኒስትሪ ፈተና ሳልወስድ የትም መሄድ ግን አልፈለኩም፡፡ ሆኖም የወላጆቼና የቸኮለች ፈተና እንደ ትምህርቱ በጥናት የሚታለፍ አልሆነም፡፡" (እነዬ፣ 2003፣ 59)

በዝምታ ውስጥ እየተብሰለሰለች ውሳኔዋን ተግባራዊ ለማድረግ ስትሞክር፣ ‹ከዚህ ጫና የማመልጠው በትምህርት ብቻ ነው!› በማለት ትምህርቷ ላይ ስትበረታና ውጤታማ ስትሆን፤ በሰዳቢዎቿ ተማሪዎች ፊት የሚያቅታት ነገር እንደሌለ ለማሳየት መምህራኖቿ እስፖርት እንድትወዳደር ሲያደርጉና ስታሸንፍ ወዘተ. ከቤተሰቦቿ የሚጠብቃት "ጎበዝ፣ በርቺ፣ ቀጥይበት" የሚል ሙገሳና ማበረታቻ ሳይሆን በተቃራኒው ሌላ የማሸማቀቂያ ተፅእኖ ነበር፡፡

እሁድ ቀን ወላጆች በተሰበሰቡበት የሩጫ ውድድር በተማሪዎች መካከል ተካሂዶ አንደኛ ወጥታ ስታሸንፍ ትምህርት ቤቱ ሸልሟት ነበር፡፡ እቤት ስትጋባ ግን አባቷ ቅስም ሰባሪ ቃላትን እየተጠቀሙ እንድትሸማቀቅና መፈጠሯን እንድትጠላ ነበር ያደረጓት፡፡

> "…ወሮ በላ! አንቺ ምን ታደርጊ መረን የወጣሽ ባለጌ! ሆነሻል እኮ! ተሰድበሽ እንደምታሰድቢኝ መች አወቅሽና!?... እንደው እንደ ባለጌ ይህን ሰውነት ማስገምገሚያ ለብሰሽ ከስንት ህዝብ መሀል ሜዳ ላይ ስትራገጪ ሰው ምን ይለኛል አትይም?... ምነው ብትተይኝ ልጄ እኔ በአንቺ ስንት ጊዜ ልጠቃ?... ከዛሬ በኋላ ከዛ ሜዳ ላይ እንዳህያ ስትራገጭ ባይ አንችን አያድርገኝ!" (እንዬ፣ 2003፣ 42-44)

በሌላ ቀንም አብሯት የሚማር የክፍል ጓደኛዋ እረስታ ሳትሰጠው የመጣችውን የጋራ የሂሳብ መጽሐፋቸውን ሊቀበላት በቤቷ አቅራቢያ ሲያነጋግራት ወንድሟ ያያል፡፡ ይህ ዕለታዊ የሚባል የተማሪዎች ንፁህ ግንኙነት በአባቷና በወንድሟ የተወሰደው በልጆቹ አእምሮ ለቅፅበት እንኳን ሊታሰብ በማይችል ሀሳብ ነበር፡፡ ለዚህም የነበረው ምላሽ እጅግ

በጣም አስጸያፊና በነፃነት ላይ ትልቅ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ያስከተለ ነበር፡፡ አሳዛኙ ነገር ለወንድምየው ጭፍን ድርጊት አባትየውም ተባብረው በሷ ብቻ ሳይሆን ሊገላግሉ በሚሞክሩት እንቷም ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ነው፡፡

> "…አንቺ መድረሻ ቢስ ማጋታ! ደሞ ከፊታችን ማሽኳለል ይመርሽ እንዴ? … አንቺ ምን ታደርጊ አትንኳት እየተባልሽ በአንቺ እየተሸማቀቅን ተቀምጠናል፡፡ አንቺ ወራዳ! ልክስክስ! … ይህቺ መላቀቂያ ቢስ ጋለሞታ! … ተከብረን በኖርንበት ቦታ መቀመጫ ስትነሳን ዝም ብለን ማየት አለብን? … "
> (እንዬ፣ 2003፣ 68)

በማለት ከዱላ ለማምለጥ በተሸሸገችበት የከብቶች በረት ውስጥ ሲያንገላታትና ከፍተኛ አካላዊ ጉዳት ሲያደርስባት ባይሳካላቸውም ለማስጣል የሚሞክሩትን እናቷ ብቻ ናቸው፡፡ አባቷ የወንዱ ልጃቸው ደጋፊ በመሆን እኩል የደበደቧት ሲሆን ሁለቱንም በደም ተጥለቅልቃ በወደቀችበት በረት ውስጥ መማታታቸውን እንዲያቆሙ ያደረጋቸው የራሳቸው መድከም ብቻ ነበር፡፡

ኀረቤትና ወዳጅ ዘመድ የእናትየውን እሪታ ሰምቶ ለመገላገል ከመምጣት ይልቅ ‹ባል ሚስቱን፤ ወንድም እህቱን መቅጣት የተለመደ ነው› በሚል ተልካሻ ምክንያት ሊያስጥሏት አልሞከሩም ነበር፡፡ በሌላ ወቅትም ቢሆን የአካባቢ ሰዎች በአምስት አመቷ ተድራ ከቤት አልወጣችምና ቤተክርስቲያን እንኳን እንዳትሳለም እገዳ ጥለውባት ነበር፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ከእሷ በእድሜ እኩያ የሆነችው የወንድሟ ሚስት በየጊዜው ቤተክርስቲያን ሄዳ ስትመለስ የመንደሩ ሰው "እንዲህ እያለ ያነሳሻል" በማለት ተጨማሪ ህመም ትፈጥርባት ነበር፡፡

ይህ የቤተሰቦቿና የማህበረሰብ ጥቃት በተደጋጋሚ እንደምትጠላውና እንደምትፈራው የምትገልፀውን የአዲስ አበባ ስደት የማይቀር እንደ ሆነ እንድታስብ አድርጓታል፡፡

> "… ለመኖር ያለኝ ተስፋ በመነመነ ቁጥር ለከተማ ኑሮ ያለኝ ጥላቻ እየጨመረ መምጣቱ ደግሞ ሌላው ጭንቀቴ ነበር… አዲስ አበባ ለገጠር ልጆች እግዚአብሄር ለአዳም ከሰጣት ገነት ትመረጣለች፡፡… እኔ ግን ጠንቋይ አዲስ አባባ ክፍልሽ አይደለም ያለኝ ይመስል ስሙ እራሱ እንደ እሬት ነው የሚመረኝ፡፡ ብዙዎቹ ጓደኞቼ

> ሲንገበገቡለት የእኔ ጥላቻ ግን የተለየ ነበር፡፡…” (እንዬ፣ 2003፣ 65-66)

ባለታሪኳ ነፃነትን በተለየ ሁኔታ እንድትታይ ያደረጋት የቤተሰብና የማህበረሰብ ጫና የትውልድ ቀየዋን ለቃ ለስደት እንድትወጣ ስላስገደዳት የሚጠብቃትን የባይተዋርነት ጫና መጋፈጥ ግድ እንደሚሆንባት እያሰበች በርካታ ቀናትን በጭንቀት አሳልፋ ነበር፡፡ ይሆናል ብላ ባልጠበቀችው ቀን አባቷ ከአጎቷ ጋር አያይዘው ወደ አዲስ አበባ ሲልኳት እህት ወንድሞቿን ለመሰናበት እንኳን እድል አልሰጧትም፡፡ በጥልቅ ሀዘን እንደተጎዳችና ቅስሟ እንደተሰበረ አባቷ እንዳቀዱት ወደ አዲስ አበባ ለመሰደድ በቃች፡፡

እዚህ ላይም ነፃነት ከቁጣ፣ ከፍርሀትና ከስጋቷ ባሻገር ‹አባቴ ተገዶ ነው ወደ ማልፈልገው አዲስ አበባ እንድሰደድ ያደረገኝ እንጂ እኔን ጠልቶ አይደለም› የሚል የጥፋተኝነት ስሜት ሲያድርባት እናነባለን፡፡

> “… በእኔ ምክንያት ቤተክርስቲያን መሳሚያ፣ ለቅሶ መድረሻ፣ ሸንጎ መነጋገሪያ ሙሉ ነፃነት ሲያጣ ቢጠላኝ ምን ይፈረደበታል፡፡ ሰው በየቀኑ ስሜቱ እየተጎዳ፣ በተወለደና በኖረበት ሃገር እያፈረ እንዴት ኖረ ማለት ይቻላል? የከረረና የገነነን ባህል ድንገት ተነስተህ ቅረፍ ብዬ ስለፈረድኩበት አፈርኩ፡፡…” (እነዬ፣ 2003፣ 90)

ቤተሰብና ማህበረሰብ ጫና በፈጠሩ ቁጥር ተጠቂው ይህንኑ አምኖ በመቀበል እራሱን የሚወቅስበት ሁኔታም ይፈጠራል የሚለው የምእራፍ ሁለት ጠቅለል ያለሀሳብ በነፃነት ህይወት ውስጥ ተግባራዊ ሲሆን እናነባለን፡፡ ይህች ገጸባህሪ ወላጆቿ በቸልተኝነት ጉዳት እንዲደርስባት ማድረጋቸው አንሶ ጉዳቱንም ለማሳከም ምንም እርምጃ አለመውሰዳቸውን ጠንቅቃ ታውቃለች፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ይኸው ጉዳት መልሶ በቤተሰቦቿ፣ በማህበረሰቡና በትምህርት ቤት ውስጥ ለሁለንተናዊ ጥቃት እንደዳረጋትም ትገነዘባለች፡፡ በአምስት ዓመት ዕድሜያቸው የተዳሩት ሁለት ታላላቅ እህቶቿና የእሷን እኩዮች ያገቡት ጎረቤት ወንድሞቿ አባትየውና የመንደሩ አባወራዎች በሚፈልጉት ወቅት ስለሆነ ለወግ የበቁት የነፃነት እስከ ዘጠኝ ዓመቷ ድረስ  ጠያቂ ባል መጥፋቱ የሷ ጥፋት የሆነ እስኪመስል ድረስ ያፍሩባት ነበር፡፡ በአካባቢው በአድናቆት የሚወራለትን ቤተሰባዊ ልምድ አዛባች በሚል አስተሳሰብ ካለጥፋቷ እሷን መውቀስ ቀኗቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ የጉዳቷ ዋና ተጠያቂ የሆኑት አባቷ ‹ማህበረሰባዊ ወግና ልማዱን ተጋፍጦ ሊያስተምረኝ ይገባ ነበር!› ከማለት ይልቅ የቀለላት እራሷን መውቀስና አባቷን ከተጠያቂነት ነፃ ማድረግ ነበር፡፡ አባቷና ወንድሞቿ የሚያደርሱባትን ከፍተኛ በደል “ባህል” ስለሆነ ነው በሚል እራሷን ለማፅናናት ትሞክራለች፡፡

> “አባቴ ዘርተው ካፈራላቸው፣ ወልደው ካደገላቸው ውስጥ የሚመደብ ኮርቶ የሚያኮራ አባት ነው፡፡ ጎምላላ በሬዎቹ ተጠምደው፣ ስናር በቅሎዎቹ ተጭነው ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ አስቀርተውት አያውቁም፡፡ የእሱ አገቡኝ ለመሆን የማይመኝ አባወራ፣ አማች ለመሆን የማይመኝ ወጣት ባለመኖሩ ሴት ልጆቹ አምስት፣ ወንድ ልጆቹ አስራ ስምንት እስኪደፍኑ በወላጆቻቸው ቤት ከጋብቻ ውጭ የመቆየት እድል አግኝተው አያውቁም፡፡ … ከሴቶቹም ሆነ ከወንዶቹ ልጆች አማቾች ጋር ሞቅ ባለ ድግስ መገባበዝ ያረካዋል፡፡ በአቻነት ተመዝነው የሚመጡት አማቾችም ቢሆኑ ይህን ባህሪውን ይወዱለታል፡፡ … ባህል ነዋ!” (እንዬ፣ 2003፣ 11)

ነፃነት እራሷን በተለየ መንገድ ታይ እንደ ነበር የሚያስረዳን ሌላው ነጥብ ስለወንድና ሴት ግንኙነት ሲነሳ የሚሰማት ጥልቅ የሆነ የበታችነት ስሜት ነው፡፡ ገና በአምስት ዓመት እድሜዋ ባለባት አካል ጉዳት ምክንያት ለሚስትነት የሚጠይቃት ቤተሰብ አጥታ ነበር፡፡ ይህን አጋጣሚ ግን እሷ በቁጭትና በጥልቅ መጎዳት ውስጥ ሆና ነበር እምታስበው፡፡

> “… እንደ እውነቱ ከሆነ ተድረው እርባንና ድሪ ባሰሩ፤ ጥቁር ባውንድ በጠመጠሙ ሕፃናት ያልቀናሁበት ጊዜ አልነበረም፡፡… ባላቸው ቤት ሲሄዱና ተጠርተው ሲመጡ ሳይ ጭምር እቀና ነበር፡፡ ስለሚገጥማቸው ነገር ግን አስቤ አላውቅም፡፡ ብቻ እንደነሱ መሞሽርና እየሄዱ መምጣት ከተመኘሁ ወዲህ ልዩነቴን እየተገነዘብኩ ራሴን መጥላት ከጀመርኩ ቆይቻለሁ፡፡…” (እንዬ፣ 2003፣ 38)

ይሁን እንጂ ወደ መንደራቸው ለመንግስታዊ ሥራ የተሰማሩት መምህራንና የህዝብ ቆጠራ ባለሙያዎች በዚህ እድሜዋ የእሷ ትዳር አለመያዝ መታደል መሆኑን ትዳር የያዙት ህፃናት የሚደርስባቸውን ሁለንተናዊ ስቃይ በማስረዳት ትምህርቷ ላይ እንድትበረታ ያደርጉ ነበር፡፡ ቤተሰቦቿ ደግሞ በተቃራኒው የሚጠይቅ ጤነኛ ባል ቢያጡ የአእምሮ ህመም ላለበት የመንደሩ ነዋሪ ሊድሯት ጭምር ወስነው ነበር፡፡ ሳይሳካ ቀረ እንጂ፡፡

የጋብቻው ነገር አለመሳካቱ ደግሞ የሷ ጥፋት የሆነ ያክል አባቷና አንዱ ወንድሟ እንዲሁም የመንደሩ ነዋሪዎች ቅስም ሰባሪ ስድብ ከመስደብም አልፈው አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳትን እንድታስተናግድ አድርገዋት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የሴትና የወንድ ጤናማ ግንኙነትን ለማከናወን ችግር እንደለባት ቆጥረው መግቢያ መውጫ አሳጧት፡፡ ይህንን የግፍ ውሳኔ ደግሞ ካለምንም ተቃውሞ ተቀብላ በዚህ ዙሪያ ከማንም ያነስኩ ነኝ የሚል ጤናማ ያልሆነ መደምደሚያ ላይ ደረሰች፡፡ ይህ መደምደሚያም በቀጣይ ህይወቷ ውሰጥ የተከሰቱ ወንዶችን በጥልቅ ፍርሃት እንድትሸሻቸው ያደረገ ነበር፡፡

በአዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ዓመታትን አሳልፋ በአንድ ወቅት ቀጣሪዎቿ የነበሩ ሰዎች ልጅ የነበረው አብላንተ በአጠቃላይ ሁኔታዋ ተማርኮ ለፍቅር ጓደኝነት ሲቀርባት ያስተናገደችው በዚህ የበታችነት ስሜት ውስጥ ሆና ነበር፡፡ ከእሱ ጋር የነበራትን ቅርበት በትንግርትነቱ እያሰበች ከመጽሐፍ ሰጪነቱና ከወንድምነቱ የዘለለ ሌላ ሀሳብ ላለማሰብ ብርቱ ጥንቃቄ ታደርግ ነበር፡፡

> "… ለእኔ የሚያስፈልገኝ ውበቱ ሳይሆን ደግነቱ ነው፡፡ … ውበቱ የሚያስጨንቀውም የሚጠቅመውም ሌሎቹን ነው፡፡ ነፃነት! እንዲህ አይነቱን ማሰብ ለአንቺ ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም፡፡ ሆ…! አባትሽ እንኳ ስንት ገንዘብ ይዞ ለአንቺ አንድ ገበሬ ማጣቱን እረሳሽ እንዴ? … ስንት ስንት የተስተካከለ ቁመና ያላቸው ጉብሎች ይጠብቁታል፡፡ አንቺ እስከምታነክሽ ለመጠበቅ ጊዜ የለውም፡፡ ከውስጤ በሚወጣ ቃል ስደበደብ ለደቂቃዎች የት መሄድ እንዳለብኝ ረስቼ ነበር፡፡" (እንዬ፣ 2003፣ 190)

በዚህ ለዘመናት አብሯት በኖረው የበታችነት ስሜት ‹ለኔ አይገባም› ብላ በማሰብ የሌላ እንዲሆን ትገፋፋው ነበር፡፡ እሱ እሷን ፍለጋ ወደ እነሱ ሲሄድ ከጓደኞቿ ጋር በፍቅር እንዲቀራረብ የምታደርገው ማነሳሳት ዘወትር ያበሳጨውና ክፉ እንዲናገራት ያደርገው ነበር፡፡ "…ለምንድነው አይኔ ሌላ ሰው ሳያይ፣ ክንዴ ሌላ ሰው ሳያቅፍ፣ በባዶ ሜዳ ስሜን የምታጠፉት? አንችስ ለምን እውነታውን አዳፍነሽ ሁላችንንም አቅጣጫ ለማሳት ትሞክሪያለሽ?..." (እንዬ፣ 2003፣ 203) በዚህ ሁኔታ ቆይተው ከብዙ ልፋትና ጭቅጭቅ በኋላ ፍቅረኛሞች ቢሆኑም አብላንተ እሷን ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

ቤተሰቦቿ ወደ አዲስ አበባ እንድትሰደድ አድርገው በየሰዉ ቤት አገልጋይ ከሆነች በኋላም ከበርካታ ቀጣሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ጋር በመገናኘት የአገልጋይነትን አስከፊ ገፅታ

ለመገንዘብ እንደቻለችና በፍፁም የሚወደድ ሙያ እንዳልሆነ ትገልፃለች፡፡ አልፎ አልፎም በተቀጠረችባቸው ቤቶች ከስንት አንዴ በምታገኘው ትርፍ ሰዓት ለማንበብ የምተሞክራቸው የአማርኛ ልቦለዶች አገልጋይ ገጸባህሪያትን የሚቀርፁበት 'ተመሳሳይ የወረደ አመለካከት' ሳትፈልግ የተሰማራችበትን ሥራ የበለጠ እንድትጠላና ከወጥ ድርሰቶች ይልቅ የትርጉም ሥራዎች ላይ ትኩረት እንድታደርግ ምክንያት እንደሆኗት ትገልፃለች፡፡

> "ለእኛ ሃገር ዕሁፍና ድራማ መጠነኛ ጥላቻ ያዳበርኩት ሳላስበው ነው፡፡ …በዚች የማንበብ፣ የማየትና የማዳመጥ ልምዴ ውስጥ ሁሉም ላይ በእኔ የህይወት መስመር የተቀረፁ ገጸባሪያትን አልወዳቸውም፡፡ መድረሻ ባጣ እንጂ ስራዬን አምርሬ እንድጠላ አስተዋፅኦ ያደረጉ ይመስለኛል፡፡ የሚገፉው የህይወት መስመር በሌብነት፣ በውሸት፣ በለፍላፊነት፣ በአቃጣሪነት ሲፈረጅ ማን ይወዳል? ሁሉም በሚችሉት አጋጣሚ ለሙያው ያላቸውን ንቀት ለመግለፅ የሚሯሯጡ ነው የሚመስለኝ፡፡ …የተጠላን የሥራ ዘርፍ ማን ይወዳል? የህይወቴን መስመር ለመቀየር አቅም ባጣም ከእነሱ ለመሸሽ ብዙም አልከበደኝም፡፡ የቴሌቪዥንም ሆነ የሬዲዮ ድራማ የኔ አምሳያ ካለበት አላይም፤ አልሰማም፡፡ ይህችንም መብት ስለሰጠኝ ጌታ ምስጋና ይግባው፡፡" (እንዬ፣ 2003፣ 151)

ሌላው አሰቃቂ በሚባል ልክ አገልገይነቷ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ያደረሰባት ወ/ሮ ሶስናና አቶ ዘገየ የተባሉት ሴረኞች እጅ ከገባች በኋላ ነበር፡፡ የአቶ ዘገየ ህጋዊ ሚስት ልጅ መውለድ ባለመቻሏ ወ/ሮ ሶስና ሠራተኛ እንዲቀጥሩ በማድረግ ይህችን አገልጋይ ከተቻለ በውድ ከለበለዚያም በግድ ‹አገባሻለሁ› በሚል ማታለያ ለማስወለድ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ በአጋጣሚ የሴትየዋ ተቀጣሪ በመሆን የዚህ እቅድ ተጠቂ የሆነችው ነፃነት መደበኛ ሥራዋን እያከናወነች ሴትየዋና ሰውየው ባመቻቹት ሁኔታ ተገዳ ትደፈራለች፡፡ ከደፈሯት በኋላ ግን ሊያገቧትና ወደ ሚኖሩበት አሜሪካ ሊወስዷት እንደሚፈልጉ ያስረዷታል፡፡

ይህ ሁኔታ ግራ ስላጋባት ከአክስቷ ልጅ ከእመቤት ጋር ተመካክራ "ካገቡኝ ከሰው ቤት ይሻለኛል" በማለት ፈቃደኛ ትሆናለች፡፡ ግንኙነታቸው ቀጥሎ የሶስት ወር ነፍሰ ጡር እያለች ሴራውን ስትደርስበት አዘናግታቸው ከሰውየው ኪስ ብር በመስረቅና ፅንሱን በማስወረድ ታመልጣቸዋለች፡፡ አቶ ዘገየ ግን አፈላልገው በማስያዝ ሰዎች በመቅጠር አሰቃቂ ጉዳት ካደረሱባት በኋላም በመደበኛ ፍርድ ቤት የሀሰት ምስክር አዘጋጅተው እንድትታሰር ያደርጋሉ፡፡ በዚህ እስር ላይ ሆና ፍርድ ቤት በቀረበችበት ሰዓት ነበር ታሪኳን በምልሰት ለተደራሲ ያቀረበችው፡፡

### 3.1.4. የትውልድ ቦታን መልቀቅ /መሰደድ/

በዚህ ጥናት ትንታኔ ከተሰጠባቸው ሶስት ገጸባህሪያት መካከል የትውልድ መንደሯን ለቃ ለሰው ቤት አገልጋይነት የተዳረገችው "የገቦ ፍሬ" ዋና ገጸባህሪ ነፃነት ክብረት ብቻ ናት፡፡ በዙሪያችን በሚኖረን ምልከታ ለመገንዘብ እንደምንችለው ህፃናት በተፈጥሮ የሚታደሉትን ዕውቀት ለመተግበር ሲሞክሩ በቤተሰቦቻቸውና በማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ምላሽ ቀሪው ዘመናቸው ላይ አሻራውን ያሳርፋል፡፡

ይህ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ምላሽ መልካም ከሆነ በሰዎች ላይ እምነት ማሳደርን፣ በራስ መተማመንን፣ ለለውጥ መትጋትን፣ የእርስ በርስ ግንኙነትንና በጋራ ማደግን፣ መሪ የመሆን ፍላጎትን፣ ለፈጠራ መነሳሳትን፤ ባላቸው ነገር የመኩራትን ወዘተ. የመሳሰሉ በጎ ነገሮችን ያዳብራሉ፡፡ በተቃራኒው የሆነ ምላሽ ደግሞ ተጠራጣሪነትን፣ ሀፍረትን፣ ለዘብተኝነትን፣ የአጥፊነት ስሜትን፣ ግራ መጋባትን፣ የበታችነት ስሜትን፣ ባይተዋርነትና ስንፍናን ወዘተ የተላበሱ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

የነፃነት ክብረት እጣ ፈንታም አሉታዊ የሆነ ቤተሰባዊና ማኅበረሰባዊ ግንኙነት ነበርና ገና በለጋ ዕድሜዋ እያንዳንዱን ወደ እሷ የተጠጋ ሰው የምታስተናግደው በፍርሀት፣ በጥርጣሬና በበታችነት ስሜት ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ገና በአስራ አንድ ዓመት እድሜዋ አባቷ አስገድደው ወደ አዲስ አበባ ለሚያደርስ ሰው ሲሰጧትና ከትውልድ መንደሯ ስትሰደድ ለባይተዋርነት ዳርጓት ነበር፡፡

አባቷም ሆኑ እሷ አዲስ አበባ መምጣቷን እንጂ ለዕለቱ እንኳን "እከሌ ጋር ታርፋለች" የሚባልበት ዘመድ ቤት አልነበረም፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ትኖራለች የተባለችው የአክስቷ ልጅ እመቤትም የሰው ቤት ሠራተኛ እንጂ ዘመድ ለማስተናገድ የሚበቃ ኑሮ ያላት አልነበረችም፡፡ አባቷ ይህንን ሁሉ በደንብ ሳይረዱት ቀርተው ሳይሆን በአካል ጉዳቷ ምክንያት የሚያገባት አጥታ ቤት ውስጥ መቀመጧ የመንደሩ ሰው መተረቻ ያደርገኛል ብለው ስለፈሩ ብቻ ነው ሳትፈልግ ወደ አዲስ አበባ እንድትሰደድ ያደረጉት፡፡

> "…የአብዛኞቹ ሴት ልጆች አለማግባት ከማጫና ከሌሎች ነገሮች አለማሟላት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ እነሱ ደግሞ በዚህ የሚታሙ አለመሆናቸውን ማሳየት የዘወትር ህልማቸው ነው፡፡ ደስታቸው ሙሉ እንዳይሆን ግን፤ በአቻነት የሚጠብቋቸው አባወራዎች ለልጆቻቸው ጤነኛ ያልሆነች ልጅ የሚወስዱ አልነበሩም፡፡ እነሱ

ደፍረው ቢጠይቁ እንኳን የወደፊት አጋራቸውን በየጥምቀቱ አስሰው የሚያዩት ወጣቶች ‹ያችን ሸራፋ እግር ከማገባ ሞቼ እገኛለሁ!› ሲሉ ያፋርሱባቸዋል፡፡… እናም የአባቴ የዘውትር ወቀሳ ‹ምነው ብትተይኝ ልጄ እኔ በአንቺ ስንት ጊዜ ልጠቃ?› የሚል ነበር፡፡ እንደዋዛ የሚልካቸው ጠረኛ ቃላቶች ግን ልቤን በሳስተው እንዳደከሙት የተረዳ አይመስልም፡፡” (እነዬ፣2002፣44)

ይህ ማህበረሰባዊ ልማድ ለቤተሰቦቿ አንድ ችግር ቢሆንም መሪር እንባ እያነባች ሳትፈልግ የዕለት መጠጊያ ወደ ሌለበት አዲስ አበባ አስገድዶ መላክ ግን ሌላ ጭካኔ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ለሊት ወደ አዲስ አበባ እንደምትጓዝ የተነገራት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲል ሲል ነው፡፡

“… አባቴ እህቶቼን እንኳን ተሰናብቼ እንድሄድ ባለማመቻቸቱ ምን ያህል አላስፈላጊ እቃ አድርጎ እንደቆጠረኝ ቢሰማኝም … እንድማር የምታበረታታኝን ታላቅ እህቴን የዛብነሽን ሳላይ ለመሄድ አቅም አጣሁ፡፡ እሰነብታለሁ ወይም አልሄድም ማለት አልችልም፡፡ የሰው ቤት ነው! … አባቴ ስለ ትምህርት ምንም አያውቅም፣ ተምሬም ራሴን መለወጥ እችል እንደነበር አልተረዳም ማለት አይቻልም፡፡ ሆኖም የእኔን ጥቅም ከራሱ ስም ማስቀደም አልፈለገም፡፡ እናም የእሱ ልጅ እንዲህ ሆነች ሲባል እንዳይሰማ እኔን ከማያይበት ስለእኔ ከማይሰማበት ሃገር ሄጄ እንድኖር መረጠ፡፡ (እነዬ፣2002፣87)

መሪር እንባዋ፣ የልብ ስብራቷ እንዲሁም መማር መፈለጓና አዲስ አበባን መጥላቷ የአባቷን ውሳኔ አላስቀየረም፡፡ ሳትወድ በግዷ በለሊት ተነስታ አዲስ አበባ የታመመች ልጃቸውን ሊያመጡ የሚሄዱት አጎቷ ቤት ተገኘች፡፡ አዲስ አበባን ገና ከመርገጧ ያገኘቻት ታማሚዋ የአጎቷ ልጅ የአዲስ አበባ ጥላቻዋና ፍርሃቷ እንዲብስባት የሚያደርገውን ገጠመኟን ስለነገረቻት ፍርሀቷ ተባብሶ ቀጠለ፡፡ ያረፈችባቸው ሰዎችም ገና አንዲት ቀን ሳታድር ግልምጫቸውን ስላሳዩዋት ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ እንደተጋባች ነግቶ የሚመሽላት በጭንቅ ነበር፡፡ በሰው በሰው ያገኘቻት የአክስቷ ልጅ እመቤት በአሰሪዎቿ አማካኝነት የመጀመሪያውን የሰው ቤት ሥራ እንድታገኝ እረዳቻት፡፡ በመሆኑም ነፃነት

ክብረት ሳትፈልግ የወላጆቿን ቤት ለቃ ወደ አዲስ አበባ በመሰደድ ለሰው ቤት ሠራተኝነት የተዳረገች ገጸባህሪይ ናት፡፡

## 3.2. የአገልጋይ ገፀባህሪያት አይነትና አቀራረብ በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ

### 3.2.1. የአገልጋይ ገጸባህሪያት አይነት

#### 3.2.1.1. ቢስ ራሔል

በዚህ ልቦለድ ውስጥ ትኩረታችን የሆነችው ዋናዋ ገጸባህሪ ራሔል ዳርጌ ናት፡፡ በብዙ የህይወት ውጣ ውረዶች የተከበበችና ፈረጀ ብዙ ተብላ የምትለይ ገጸባህሪ ነች፡፡ ታሪኩ የሚጀምረውም የሚጨርሰውም በሷ ህይወት ዙሪያ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ምእራፍ ውስጥ በቀረበው ታሪክ ውስጥ ራሔል ትገኛለች፡፡ በልቦለዱ ውስጥ የቀረበ እያንዳንዱ ገጸባህሪ በአንድም በሌላም ከእሷ ጋር የሚገናኝበት መስመር ተዘርግቶለታል፡፡ ውጫዊውንም ሆነ ውስጣዊ ሰብእናዋን የምንገነዘበው በተለያዩ ቦታዎች ከተለያዩ ሰዎች ጋር በሚኖራት ግንኙነት የምታሳየውን ባህሪና የምትወስደውን እርምጃ በመከተል ነው፡፡

የተሻለ ነገር ለማግኘት በምታደርጋቸው ሙከራዎቿ ውስጥ ሁሉ ብዙ እንቅፋቶች ከብዙ አቅጣጫ ይደቀኑባት ነበር፡፡ የኔ የምትላቸው ጎረቤቶች፣ ጓደኞቿና ፍቅረኛዋም ጭምር መነሻው የማይታወቅን ወሬ በማዛመት የችግር መውጫ ብላ የምታስባቸውን ቀዳዳዎች ሁሉ ሲደፍኑባት እናነባለን፡፡ መንፈሰ ጠንካራ ስለነበረች ግን አንዱ ሲደፈንባት ሌላ መውጫ እያዘጋጀች ትግሏን ትቀጥላለች፡፡ በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ አልፋ አላማዋን ታሳካለች፡፡ በነዚህ ምክንያቶች ነው ራሔል ፈረጀ ብዙ ገጸባህሪ ተብላ የምትለየው፡፡

#### 3.2.1.2. የደራሲዋ ፋይል

ፅዮን ፈርጀብዙ የሚባለው የገጸባህሪ አይነት ናት፡፡ ለዚህም ገና ታሪኩ ሲጀምር የምትገኝበትን ጥልቅ ሀዘን መነሻ አድርገው በምልሰት ቴክኒክ የተነገሩን ያለፉ ታሪኮቿና ያለችበት ተጨባጭ ህይወት እማኝ ናቸው፡፡ ከቤታቸው ፊት ለፊት ለአባቷ ሀዘን በተተከለው ድንኳን ውስጥ እሷን ብቻ ብለው የመጡ ጭምር ብዙ ሰዎች እያሉ ብቸኝነትና ፍርሃት የሚሰማት ገጸባህሪ ነች፡፡ በታሪኩ ውስጥ ፅዮንን እየተከተልን ስንጓዝ ስለሷ እንዲህ ነች ብቻ ብለን ለመግለፅ የሚያስቸግሩን የተደባለቁ ባህሪያትን እናገኝባታለን፡፡ ከአባቷ ጋር ባላት ቅርብ ግንኙነት ይህንን ሁኔታ እንመለከታን፡፡ ስለ ስነጽሁፍ ሲጨዋወቱ ዘና ብላ እየተዝናናች ተደጋጋሚውን የእናቷን ጥሪ ችላ እያለች መቆየቷን የማንበባችንን ያክል

ስለ አባቷ አካላዊ ጉስቁልናና የጤና መቃወስ አጥብቃ ስትጨነቅ እናያለን፡፡ (የዝና፣ 2002፣ 7) ከአባቷ ስር ስር እያለች በምትሞካክራቸው የስነጽሁፍ ስራዎች በቋንቋ መምህሯና በት/ቤት ጓደኞቿ የመደነቋን ያክል በእናቷና በሳቸው ወዳጅ ጎረቤቶች ዘንድ ስሟ በመጥፎ ሲነሳ እናነባለን፡፡ (የዝና፣ 2002፣ 8-11)

ከላይ ለማስረጃነት የተጠቀሱት ተቀራኒ ሁነቶች በፅዮን ህይወት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ሲፈፀሙ ስለምናይ የህይወቷን ውስብስብነት ለመረዳት እንችላለን፡፡ በአስቸጋሪ የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ሆና አላማዋን ለማሳካት የምታደርገው መፍጨርጨር ለብዙ ችግሮች ሲዳርጋት እናያለን፡፡ የደራሲነት ህልሟን ለማሳካት መስዋእት የምታደርጋቸው የህይወቷ ክፍሎች አሉ፡፡ ቤተሰቧን ተለይታለች፤ ፍቅረኛዋ ግርማን እዚህ ሄድኩ ሳትለው ጥላው ጠፍታለች፡፡ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ለማቋረጥ ተገዳለች፡፡ ከምንም በላይ ምንም አይነት የቤት ሙያ እውቀት ሳይኖራት ለሰው ቤት አገልጋይነት ተዳርጋለች፡፡ በመዳፏ ያሉ የህይወት አማራጮችን እንዳትጠቀም ገና በልጅነት እድሜዋ "…በህይወት ውስጥ ትዳር መመስረት፣ ልጆችም መውለድ እንደ ሂሳብ በቀመር ሊሰራ ይችል ይሆናል፡፡ ያም ሆኖ ግን ለተሰጥኦ ጥሪ ተገቢ መልስ መስጠት ካልተቻለ ሁሉም ባዶ የሆነ ያህል ነው የሚሰማ፡፡…" (የዝና፣ 2002፣ 7) እያሉ የሚፈላሰፉትን አባቷን አስተሳሰብ ለመተግበር ስለምትፍጨረጨር ትክክለኛው ህይወትና ከሌሎች ጋር ያላትን ግንኙነት ጣእም አልባ አድርጎባታል፡፡

በአጠቃላይ ከቤተሰቧ ጋር ያላት የእርስ በርስ ግንኙነት፣ የሰው ቤት አገልጋይ ሆናም ይሁን ከምታውቃቸው ሰዎች ጋር እያለች የገጠሟት ፈተናዎችና እነሱን ለመወጣት የተጓዘችባቸው መንገዶች፣ የምትወስዳቸው ቀላልም ይሁኑ ከባድ የህይወት እርምጃዎች፣ አለማዋን ለማሳካት የተጋፈጠቻቸው መሰናክሎች ወዘተ. ፅዮንን ፈርጀብዙ ገጸባህሪ ነች ለማለት የሚያስችሉ ናቸው፡፡

### 3.2.1.3. የገቦ ፍሬ

የየገቦ ፍሬ ዋና ገጸባህሪ የሆነችው ነፃነት ክብሩ ፈርጀብዙ የምትባል ገጸባህሪ ሆና ነው የተሳለችው፡፡ ነፃነት የአካል ጉዳቷን ሳታስተውለው ቆይታ በአንድ መጥፎ አጋጣሚ አብራት የምትማረው ቸኮለች የተባለችው ከእሷ በእድሜ የምትበልጥ ተማሪ በጉዳቷ

እያሾፈች ከሰደበቻት በኋላ በጣም አስከፊና አሰቃቂ የሚባሉ የህይወት ውጣ ውረዶችን በጥቂት እድሜዋ ያሳለፈች ታዳጊ ነች፡፡

ገና ከዘጠኝ ዓመት እድሜዋ ጀምሮ ከአባቷ ቤት የሚጀምረውን ታሪኳን እያስነበበችን በተሰጣት ጊዜና ቦታ ውስጥ ድርጊቶችን እየፈፀመች አብራን ብዙ ቆይታለች፡፡ የልቦለዱ ታሪክ በዋናነት የሚያጠነጥነው በሷ የህይወት ውጣ ውረድ ዙሪያ ነው፡፡ አስበውላት ሳይሆን በመምህራን ግፊት ትምህርት ቤት የላኳት ወላጆቿ በአምስት አመቷ በጉዳቷ ምክንያት ሊያገባት የሚፈልግ ገበሬ አለመኖሩን የእሷ ጥፋት አድርገው ማየታቸው እንዲጠሏት አድርጓቸዋል፡፡ ይህ ጥላቻ ደግሞ ያስከተለባት ስደት፣ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት በመሆኑ ከዚህ ጉዳት ለመገላገል ተምራ ውጤታማ መሆንን የህይወት ግቧ አደረገችው፡፡ ይህንን ግብ ግን በቀላሉ ለማሳካት አልቻለችም፡፡ በወላጆቿ፣ በተወለደችበት ቀዬ ባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ውስጥ በነበሩ ቀጣሪዎቿ መኖሯን እስክትጠላ የሚያደርስ ጫና ይደርስባት ነበር፡፡ እነዚህና መሰል የገጸባህሪዋ ሁነቶች ፈርጀብዙ በሚባለው አይነት ውስጥ እንድትካተት አድርጓታል፡፡

### 3.2.2. የአገልጋይ ገጸባህሪያት አቀራረብ

#### 3.2.2.1. ቢስ ራሔል

ውጫዊ ሰብእናዋን በተመለከተ ራሔልን የምንተዋወቃት በተለያየ ቦታና በተለያዩ ድርጊቶች አማካኝነት ነው፡፡ ታሪኩ ሲጀምር ገና ከታሰረበት ሻሸ አምልጦ እህቷን አላስተኛ ሲላት የጸጉሯን ረጅምነትና ለስላሳነት እናውቃለን፡፡ በሌላ ገጽ ላይ ገላዋን ለመታጠብ ስትዘገጃጅ የቆዳዋን ቅላትና ልስላሴ እናነባለን፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ገፆች ውስጥ ዘንካታ ቁመና ያላት ስለመሆኗ፣ ጎላ ጎላ ያሉት አይኖቿ ስላላቸው ውበት ወዘተ. በአጠቃላይ የራሔል አካላዊ ገለፃ ቁንጅናዋን የሚያስረዳ ነው፡፡

የራሔልን ውስጣዊ ማንነት የምንረዳው ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በተለያዩ ድርጊቶችና ገለፃዎች አማካኝነት ነው፡፡ ጠንካራና በገጠማት ችግር ከማዘን ይልቅ የችግሩ መንስኤ ነው ብላ የምታምንበትን ጉዳይ ለመለወጥ የምትፍጨረጨር ሆና ተስላለች፡፡ የተረጋጋችና ላየችው ሁሉ የማትንሰፈሰፍ፣ የሰው ገንዘብ የማትፈልግ፣ ቀጥተኛና መናገር የምትፈልገውን በቀጥታና በትህትና የምታስረዳ፣ ከፍተኛ የሆነ የመንፈስ ፅናት የተላበሰች ጠንካራ ገጸባህሪ ናት፡፡ ደግና ሰው አክባሪ፣ አላማዋን ለማሳካት እንደምትችል በረሷ ላይ

ከፍተኛ እምነት ያላት፤ ባለውለታዎቿንና በችግር ጊዜ አብረዋት የነበሩትን የማትረሳ፤ ሰው አፍቃሪነትና የዋህነት የሚያጠቃት ባለታሪክ ናት፡፡ በአጠቃላይ ከገጸባህሪዋ ፈረጀብዙነት አንፃር ውጫዊና ውስጣዊ ሰብእናዋ የተገለጸበት ስልት የደራሲዋን ብልህነት የሚያሳይ ነው፡፡

### 3.2.2.2. የደራሲዋ ፋይል

የፅዮን ውጫዊ መልክ እንደ ዋና ገጸባህሪነቷ በበቂ ባይገለፅም እሷን ያስተዋወቁን ጥቂት አካላዊ ክፍሎቿ ግን በተለያዩ ገጾችና ድርጊቶች እየተዋዙ በመቅረባቸው የደራሲዋን ችሎታ አሳይተውናል፡፡ የቀይ ዳማ ፊት፣ ጎላ ጎላ ያሉ አይኖች፣ ቀጠን ረዘም ያለ ለግላጋ ሰውነት እነዚህ ውስን ውጫዊ ሰብእናዎች ውብ ወጣት ሴት መሆኗን አስገንዝበውናል፡፡ የፅዮን አካለዊ ገለጻ አቀራረብ ኢ.ርቱእ ወይንም ተውኔታዊ የሚባለው የገጸባህሪ አቀራረብ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ዘዴ የፅዮንን አካላዊ ውበቶች ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር በሚኖራት ግንኙነት ከምትፈፅማቸው ድርጊቶች በመነሳት የምንረዳቸው ናቸው፡፡ “…ንዴቷ ከቁጥጥሯ በላይ ሆነባትና የያዘችውን ደብተር ድንገት ፊቱ ላይ በተነችበት፡፡ ጎላ ጎላ ያሉት አይኖቿ ደፍርሰው፤ ቀጠን ረዘም ያለ ሰውነቷ በንዴት እየተንቀጠቀጠ ተስፈንጥራ ልታንቀው ስትል…” (የዝና፣ 2002፣ 26)

ልክ እንደ ውጫዊው አካሏ የፅዮን ውስጣዊ ማንነት የተገለፀው በጥቂቱና በድርጊቶች ታጅቦ ነው፡፡ ለማወቅ ጥያቄዎችን የምትጠይቅ፣ ገራገር የሚሉ የባህሪ ማብራሪያዎች በተለያዩ ገጾች ከመቅረባቸው ውጭ እንዲህ ናት የሚል ተጨማሪ ሀሳብ አናገኝም፡፡ ይሁን እንጂ ለብቻዋም ሆነ ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር ባላት ግንኙነት በምትፈፅማቸው ድርጊቶች አማካኝነት አንባቢ የፅዮን ባህሪ እንዲህ ነው ለማለት እንዲችል ሁኔታዎች ተመቻችተውለታል፡፡

በትምህርት ቤት ውስጥ ከጓደኞቿ ጋር በነበራት የጭውውት ቆይታ ላይ የማትፈልገው ሀሳብ ስለተነሳ በድንገት የጨዋታውን አቅራቢ ጥቃት ፈፅማበታለች፡፡ (የዝና፣ 2002፣ 26) በዚህ ምሳሌ መነሻነት ደራሲዋ ፅዮን ግልፍተኛ፣ ቁጡና ስሜታዊ ነች ብላ ሳትነግረን ድርጊቷን አይተን እነዚህ ባህሪያት አሉባት ለማለት እንችላለን፡፡ በሌላ ወቅትም ሥራ አስይዝሻለሁ በሚል ማታለያ ሊደፍሯት የነበሩትን የአቶ አሻግራቸውን አይኖች ቧጭራ ስታመልጥ (የዝና፣ 2002፣ 135) እንዲሁም በስካር መንፈስ ሴትነቷን ለማወቅ ያታገላትን

አሠሪዋ ከሊልን ከላይዋ ላይ አሽቀንጥራ በመጣል አደጋ ስታደርስበት የሚያሳዩትን ቅጽበታዊ ድርጊቶቿን በመገንዘብ ቁጡነቷን እንረዳለን፡፡ (የዝና፣ 2002፣ 218)

በአጠቃላይ እነዚህ የገጸባህሪዋ ውስጣዊና ውጫዊ የሰብእና አስረጂ ድርጊቶች በሙሉ በታሪኩ ውስጥ ከቀረቡት ልዩ ልዩ ገጸባህሪያት አጠቃላይ ድርጊቶች ጋር ተስማምተውና ተጣጥመው ስለቀረቡ ደራሲዋ የተሻለ የገጸባህሪ አቀራረብ ተከትላለች፡፡

### 3.2.2.3. የገቦ ፍሬ

የዚህ ልቦለድ ታሪክ ዋና ገጸባህሪ ነፃነት በዝርዝር የተገለፀ አካላዊ ማነንነት በመፅሀፉ ውስጥ የላትም፡፡ በሙሉ በልቦለዱ ውስጥ አካላዊውንም ሆነ ውስጣዊ ሰብእናዋን በአብዛኛው የምናገኘው ከድርጊቶቿ ነው፡፡ ይህም የተሻለና ኢ-ርቱእ ወይም ተውኔታዊ የሚባለው የገጸባህሪ አቀራረብ አይነት መሆኑን በምእራፍ ሁለት ከነበረው ንድፈ ሀሳባዊ መረጃችን ተገንዝበናል፡፡ አንድ እግር ተረከዟ ላይ ጉዳት ያለባት፣ ወፍራም፣ ፀጉሯ እረዥምና ብዙ፣ ጥርት ያለ ፊትና የሚያምር ቅርፅ ያላት፣ አጠር ያለ ቁመት፣ ስትለብስ የሚያምርባት እንደ ሆነች በታሪኩ ውስጥ ቀርቧል፡፡ ይህም በትንሹ በሷ ልክ የምናውቃቸውን ወጣት ቆንጆ ሴቶች በምናባችን ለመሳል የሚያንደረድር እንጂ በበቂ ሁኔታ የነፃነትን ሙሉ አካላዊ ማንነት የሚከስትልን አይደለም ብዬ አስባለሁ፡

ባህሪዋንም ስንመለከት እስከ ዘጠኝ ዓመቷ ድረስ ደስተኛ፣ በራስ መተማመኗ ከተወለደችበት አካባቢ መሰሎቿ እጅግ ላቅ ያለ፣ ቀድሚ ልናገር ባይ ሆነ ነበር የተሳለችው፡፡ በአንዲት ቀን የትምህርት ቤት የእረፍት ሰዓት ላይ የአንድ እግር ጉዳቷን መነሻ አድርገው ጓደኞቿ በተለይም ቸኮለች የተባለችው ገጸባህሪ ከተከታዮቿ ጋር በስድብ መውጫ መግቢያ ካሳጧት በኋላ ከላይ የተዘረዘሩት የልጅነት አስደሳች ባህሪዎቿ በሙሉ በተቃራኒ የባህሪ መገለጫዎች ተተክተዋል፡፡ ይህ የባህሪ ለውጥም በቂ ምክንያት የተዘጋጀለትና አሳማኝ ነበር፡፡ ከድርጊቶቿ በመነሳት ድንጉጥ፣ ፈሪ፣ ተጠራጣሪ፣ በቁጣና በጥላቻ የተሞላች፣ አንዳንዴም አፍቃሪና ለምታፈቅራቸው ሰዎችም ስትል አደጋዎችን የምትጋፈጥ አስገራሚ ወጣት ሆና ትከሰታለች፡፡

እነዚህን ባህሪዎቿን በታሪኩ ውስጥ የምናገኛቸው በደራሲዋ "እንዲህ ናት" ተብለን ሳይሆን ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር ባላት የእርስ በርስ ግንኙነት ከምታከናውናቸው ድርጊቶች በመነሳት ነው፡፡ አዲስ አበባ ገብታ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀጠረቻት ሴት ‹ልጆቼ በልተው

ሳይጨርሱ እንዴት አንቺ ትበያለሽ?› በሚል መነሻ "…ምን አይነት ባለጌ ወልዶ፣ ባለጌ ያሳደገሽ ነሽ አንቺ? ምን አይነት ቤት ነው የኖርሽው ለመሆኑ?" (እንዬ፣ 2003፣ 105) በማለት ስትሳደብ የምትበላበትን ሰሀን አሽቀንጥራ በድንገት የተነሳችው ነፃነት ከሷ የማንጠብቀውን ምላሽ ስትሰጣት እናነባለን፡፡

"… ከማን ቤት ይመስልሻል የኖርኩ? ልንገርሽ ከአባቴ ቤት ነበር፡፡ አባቴ ደግሞ በእንዳንች አይነቱ ማንነቱን በማያውቅ ሰው የሚሰደብ አይደለም፡፡ ይገርምሻል! አባቴ እንኳን እሱ አህዮቹም ከዚህ የወፍ ጎጆሽ በጣም በተሻለ ትልቅ ቤት ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡ አንቺም ቤት አለኝ ብለሽ ትሳደቢያለሽ…" (እንዬ፣ 2003፣ 106)

አብላንተ የተባለው ገጸባህሪ ያለበት ቤተሰብ ውስጥ ወጣቱን ቤተሰቦቹ ጭምር ስለሚፈሩትና እሱም ቁጥብ ስለሆነ በቆያታዋ ስለ እሱ ከመስማቷ ወጭ ፈጥና አላወቀችውም ነበረ፡፡ በአካል በተገናኙበት ቀን የብቻ ክፍሉን እንድታጸዳለት አዟት ይወጣል፡፡ እንደ ታዘዘችው ክፍሉን አጽድታ ከጨረሰች በኋላ ልቦለድ መጽሐፍ ከተቀመጠበት አንስታ እዛው ክፍል ውስጥ ማንበብ ትጀምራለች፡፡ በንባቧ ተመስጣ ባለችበት ሁኔታ አብላንተ ተመልሶ ወደ ክፍሉ በመግባት ተገርሞ ይመለከታት ነበር፡፡ ይህንን በተረዳችበት ቅፅበት ግን የወሰደቻቸው ደመነፍሳዊ እንቅስቃሴዎች ከላይ ያጠቃለልናቸው ባህሪያት ባለቤት እንደ ሆነች የሚያስረዱ ናቸው፡፡

"… ሽንቴን እንኳን መቆጣጠር አቃተኝ፡፡ በቁሜ ፈሰሰብኝ፡፡ ከጀርባዬ የነበረው ግድግዳ እረዳኝ እንጂ ሚዛኔን ስቼ ልዘረር እችል እንደ ነበር ይሰማኛል፡፡ በእህትና በወንድሞቹ ብቻ ሳይሆን በእናቱና አባቱ ጭምር የሚፈራ ሰው ለእኔ የሚራራበት ልብ ይኖረዋል ብዬ አልገመትኩም፡፡ … የይቅርታ ቃል ማውጣት ፈልጌ … አፌን ለመክፈት በታገልኩ ቁጥር እንባዬ ያለ ገደብ መውረድ ጀመረ፡፡ …" (እንዬ፣ 2003፣ 152)

በነፃነት ህይወት ውስጥ ተፅእኖ ፈጣሪዎቹ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ከአካባቢዋ ርቃ በመሄድ በማትፈልገው ህይወት ውስጥ የግድ መዘፈቋ ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች አንባቢ ከአንዱ ገፅ ወደ ሌላው ገፅ እየተጓዘ ልቦለዱን በሚከተልበት ወቅት ያስከተሉባትን አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳቶች እንዲያስተውል ያደርጉታል፡፡ እነዚህን የእለት ከእለት እንቅስቃሴዎችና የህይወት ውጣ ውረዶች በጥልቀት በመገንዘብ የገጸባህሪዋ ውስጣዊ ማንነት ይህን ይመስላል ለማለት እንችላለን፡፡፡

ባህሪዋንም ስንመለከት እስከ ዘጠኝ ዓመቷ ድረስ ደስተኛ፣ በራስ መተማመኗ ከተወለደችበት አካባቢ መሰሎቿ እጅግ ላቅ ያለ፣ ቀድሜ ልናገር ባይ ሆነ ነበር የተሳለችው፡፡ በአንዲት ቀን የትምህርት ቤት የእረፍት ሰዓት ላይ የአንድ እግር ጉዳቷን መነሻ አድርገው ጓደኞቿ በተለይም ቸኮለች የተባለችው ገጸባህሪ ከተከታዮቿ ጋር በስድብ መውጫ መግቢያ ካሳጧት በኋላ ከላይ የተዘረዘሩት የልጅነት አስደሳች ባህሪዎቿ በሙሉ በተቃራኒ የባህሪ መገለጫዎች ተተክተዋል፡፡ ይህ የባህሪ ለውጥም በቂ ምክንያት የተዘጋጀለትና አሳማኝ ነበር፡፡ ከድርጊቶቿ በመነሳት ድንጉጥ፣ ፈሪ፣ ተጠራጣሪ፣ በቁጣና በጥላቻ የተሞላች፣ አንዳንዴም አፍቃሪና ለምታፈቅራቸው ሰዎችም ስትል አደጋዎችን የምትጋፈጥ አስገራሚ ወጣት ሆና ትከሰታለች፡፡

እነዚህን ባህሪዎቿን በታሪኩ ውስጥ የምናገኛቸው በደራሲዋ "እንዲህ ናት" ተብለን ሳይሆን ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር ባላት የእርስ በርስ ግንኙነት ከምታከናውናቸው ድርጊቶች በመነሳት ነው፡፡ አዲስ አበባ ገብታ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀጠረቻት ሴት ‹ልጆቼ በልተው ሳይጨርሱ እንዴት አንቺ ትበያለሽ?› በሚል መነሻ "...ምን አይነት ባለጌ ወልዶ፣ ባለጌ ያሳደገሽ ነሽ አንቺ? ምን አይነት ቤት ነው የኖርሽው ለመሆኑ?" (እንዬ፣ 2003፣ 105) በማለት ስትሳደብ የምትበላበትን ሰሀን አሽቀንጥራ በድንገት የተነሳችው ነፃነት ከሷ የማንጠብቀውን ምላሽ ስትሰጣት እናነባለን፡፡

> "... ከማን ቤት ይመስልሻል የኖርኩ? ልንገርሽ ከአባቴ ቤት ነበር፡፡ አባቴ ደግሞ በእንዳንች አይነቱ ማንነቱን በማያውቅ ሰው የሚሰደብ አይደለም፡፡ ይገርምሻል! አባቴ እንኳን እሱ አህዮቹም ከዚህ የወፍ ጎጆሽ በጣም በተሻለ ትልቅ ቤት ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡ አንቺም ቤት አለኝ ብለሽ ትሳደቢያለሽ..." (እንዬ፣ 2003፣ 106)

አብላንት የተባለው ገጸባህሪ ያለበት ቤተሰብ ውስጥ ወጣቱን ቤተሰቦቹ ጭምር ስለሚፈሩትና እሱም ቁጥብ ስለሆነ በቆያታዋ ስለ እሱ ከመስማቷ ውጭ ፊጥና አላወቀችውም ነበረ፡፡ በአካል በተገናኙበት ቀን የብቻ ክፍሉን እንድታጸዳለት አዟት ይወጣል፡፡ እንደ ታዘዘችው ክፍሉን አጽድታ ከጨረሰች በኋላ ልቦለድ መጽሐፍ ከተቀመጠበት አንስታ እዛው ክፍል ውስጥ ማንበብ ትጀምራለች፡፡ በንባቧ ተመስጣ ባለችበት ሁኔታ አብላንት ተመልሶ ወደ ክፍሉ በመግባት ተገርሞ ይመለከታት ነበር፡፡

ይህንን በተረዳችበት ቅፅበት ግን የወሰደቻቸው ደመነፍሳዊ እንቅስቃሴዎች ከላይ ያጠቃለልናቸው ባህሪያት ባለቤት እንደ ሆነች የሚያስረዱ ናቸው፡፡

> "… ሽንቴን እንኳን መቆጣጠር አቃተኝ፡፡ በቁሜ ፈሰሰብኝ፡፡ ከጀርባዬ የነበረው ግድግዳ እረዳኝ እንጂ ሚዛኔን ስቼ ልዘረር እችል እንደ ነበር ይሰማኛል፡፡ በእህትና በወንድሞቼ ብቻ ሳይሆን በእናቱና አባቱ ጭምር የሚፈራ ሰው ለእኔ የሚራራበት ልብ ይኖረዋል ብዬ አልገመትኩም፡፡ … የይቅርታ ቃል ማውጣት ፈልጌ … አፌን ለመክፈት በታገልኩ ቁጥር እንባዬ ያለ ገደብ መውረድ ጀመረ፡፡ …" (እንዬ፣ 2003፣ 152)

በነፃነት ህይወት ውስጥ ተፅእኖ ፈጣሪዎቹ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ከአካባቢዋ ርቃ በመሄድ በማትፈልገው ህይወት ውስጥ የግድ መዘፈቋ ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች አንባቢ ከአንዱ ገፅ ወደ ሌላው ገፅ እየተጓዘ ልቦለዱን በሚከተልበት ወቅት ያስከተሉባትን አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳቶች እንዲያስተውል ያደርጉታል፡፡ እነዚህን የእለት ከእለት እንቅስቃሴዎችና የህይወት ውጣ ውረዶች በጥልቀት በመገንዘብ የገጸባህሪዋ ውስጣዊ ማንነት ይህን ይመስላል ለማለት እንችላለን፡፡

# ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "አገልጋይ ገጸባህሪያት ከ1990 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በታተሙ የተመረጡ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ" በሚል ርእስ የተከናወነ ነው፡፡ በተጠቀሱት ሃያ ዓመታት ውስጥ ከታተሙ የሴት ደራሲያን ረጅም ልቦለድ መፃህፍት ውስጥ የጥናቴ ዋና ጉዳይ በሆኑት "አገልጋይ ገጸባህሪያት" ዙሪያ ሽፋን ሰጥተዋል ብዬ ያመንኩባቸውን ሶስት ልቦለድ መጻህፍትን በመምረጥ ጥናቴን አካሂጃለሁ፡፡

ጥናቴን ያከናወንኩባቸው ረዥም ልቦለዶች ሶስት ናቸው፡፡ ፀሐይ መልአኩ በ1996 ዓ.ም ያሳተመችው "ቢስ ራሔል"፣ በ2002 ዓ.ም የታታመው የየዝና ወርቁ "የደራሲዋ ፋይል" እና በ2003 ዓ.ም የታተመው የእንዬ ሺበሺ "የገቦ ፍሬ" ጥናቱ ያተኮረባቸው ልቦለድ መጻህፍት ናቸው፡፡

ይህ ጥናት በተመረጡት ሶስት ረዥም ልቦለድ መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ አገልጋይ ገጸባህሪያትን ወደ እዚህ ሙያ የገፋፏቸውን ምክንያቶች ያጠናሁበት ነው፡፡ በተጨማሪም አገልጋይ ገጸባህሪያትን በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ስንመረምራቸው አይነታቸው ከየትኛው እንደሚመደብና አቀራረባቸው ምን እንደሚመስል መርምሬያለሁ፡፡

የሶስቱ ልቦለዶች ገጸባህሪያት ማለትም የ"ቢስ ራሔል" ራሔል ዳርጌ፣ "የደራሲዋ ፋይል" ፅዮን ታምሩ እና "የገቦ ፍሬ"ዋ ነፃነት ክብሩ ውስብስብነት የሚታይባቸውና በህይወት ውጣ ውረድ መከራቸውን ያዩ ገጸባህሪያት ናቸው፡፡ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫናዎቻቸውን ለማራገፍ በሚጥሩበት ጊዜ የሚደቀኑባቸውን ሌሎች ፈተናዎች እየተወጡ ወደ ስኬታቸው ለመቅረብ የቻሉ ገጸባህሪያት መሆናቸውን ከታሪኮቻቸው ተገንዝበናል፡፡

ለነዚህ ሶስት ገጸባህሪያት ምንም ነገር በቀላሉ የለም፡፡ ለሚበሉት ቁራሽ እንጀራ እንኳን ሲቸገሩ እንደ ነበር ከየልቦለዶቹ ተረድተናል፡፡ የሚፈልጓትን እያንዳንዷን ነገር ለማግኘት የሚገጥማቸው ልፋትና ጥረት አስጨናቂና አንዳንዴም አሰቃቂ ሆኖ የቀረበበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ አጠቃላይ ገጸባህሪያቱ ከተሳሉበት ጊዜና ቦታ አንፃር "ለምን ሆነ?" ብለን የምንተቸው አይደለም፡፡ እንደውም የዋና ገጸባህሪያትን ውስብስብ ድርሻ አሳይተውናል፡፡

አገልጋይ ገጸባህሪያትን ወደ እዚህ ተፈልጎ የማይገባበት ሥራ እንዲገቡ ያስገደዷቸው ልዩ ልዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም እኔ ከተጠኑት ገጸባህሪያት አንፃር ለትንታኔ የመረጥኳቸው አራቱን ነው፡፡ የተሻለ ህይወት ፍለጋ፣ አለመማር፣ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ጫና፣ የትውልድ ቦታን መልቀቅ /መሰደድ/ የሚሉትን ነጥቦች ነው፡፡ እነዚህን ምክንያቶች ከተጠኑት ገጸባህሪያት አንፃር ስናያቸው ሶስቱም በሁሉም አስገዳጅ ሁኔታዎች ውስጥ ላያልፉ እንደሚችሉ ተመልክተናል፡፡

ሁሉም ገጸባህሪያት አለመማራቸው የሰው ቤት ሠራተኛ ያደረጋቸውን ያክል ሶስቱም ግን አካባቢያቸውን ለቀው አልተሰደዱም፡፡ ካሉበት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግር ሽሽት የተሻለ ህይወትን ፍለጋ ራሔልና ፅዮን ደላላ ቤት ሥራ ሲያፈላልጉ የ11 ዓመቷ ታዳጊ ነፃነት ግን ከቤተሰቦቿና ከትውልድ ቀየዋ ላለመልቀቅ ደም ዕንባ ስታነባ አስተውለናል፡፡ ሶስቱም ገጸባህሪያት ቤተሰብና ማህበረሰብ በተለየ መልክ ያያቸው የነበሩና በዚህም ለችግር የተጋለጡ ገጸባህሪያት ናቸው፡፡ ቤተሰብም ሆነ ማህበረሰብ ገፍቶ ገፍቶ ለአካላዊና ለስነልቦናዊ ጉዳት ካደረሳቸው በኋላ ዞሮ ተጠቂዎቹን የሚወቅስበትን መንገድ አስተውለናል፡፡

ቤተሰቦች ሳይፈልጉ በተፈጠሩና ተገቢ አስተዳደግ ባላገኙ ልጆቻቸው ህይወት ተጠያቂ መሆን ሲገባቸው ችግር ፈጣሪዎችም፣ አሳዳጆችም ሆነው የቀረቡበት ሁኔታ አለ፡፡ በተለይም ከ"የገቦ ፍሬ"ዋ ነፃነት ክብሩ ህይወት አንፃር ስንመለከተው ማህበረሰባዊ ልምዶችን ከወለድናቸውም ልጆች በላይ ዋጋ የምንሰጣቸው መሆኑን በአግባቡ ያየሁበት ነው፡፡ የዚህች ገጸባህሪ ስቃይና በተለየ አይን የመታየት ሁኔታ በቤተሰቧና በተወለደችበት ማህበረሰብ ተለምዶ ውስጥ የቀረ ብቻ አልነበረም፡፡ ስቃይና መገለልን ሽሽት የትውልድ መንደሯን ብትቀይርም ባይተዋርነቷ፣ አካላዊ ጉዳቷና አለሁልሽ ባይ ማጣቷ በተሰደደችበት ቦታም የቀጣሪዎቿን ጫና እንድትቀበል አድርጓታል፡፡

ከሌሎቹ ገጸባህሪያት በተለየ በዚህች ገጸባህሪ ህይወት ውስጥ የጭራቅነት ሚና የተላበሱ በርካታ አሰሪዎችን ለማየት ችለናል፡፡ "ልጆቼ በልተው ሳይጨርሱ ያቀረብኩልሽን እንዴት ትበያለሽ" ያለቻትን ቀጣሪዋን አማረን ሳንጨርስ በድቅድቅ ጨለማ ከቤቷ አባራት ለጉዳት የዳረገቻትን ሌላ ሴት እናገኛለን፡፡ የቀጠረቻት ሴት ሚስቱ ልጅ መውለድ ከማትችል ባለትዳር ወንድ ጋር በገንዘብ ተደራድራ እንዲደፍራት ያመቻቸችበትን አጋጣሚም

አንብበናል፡፡ ሌላም ሌላም አጋጣሚ የጉዳቷን ጥልቀትና የአሠሪዎቿን ጭካኔ ያስተዋልንበት ነበር፡፡

የራሔል እና የፅዮንንም ታሪክ ስናይ በተወሰነ ደረጃ ከነፃነት የሚሻልበትን ጥቂት ነጥብ እናነሳ እንደሆን እንጂ የጉዳታቸው ጥልቀት ተመሳሳይ ነው፡፡ ቤተሰብና ማህበረሰብ ካደረሰባቸው ጥልቅ ጉዳት አንፃር በወጣቶቹ ገጸባህሪያት አጠቃላይ ሁኔታ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ ብለን የምናስባቸውን አብረውን የሚኖሩ መሰሎቻቸውን እንድናስብ የምንገደድባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ በስቃያቸው አዝነን አብረናቸው ከተጓዝንም በኋላ በብዙ ጥረት ያሳኩትን ግባቸውን ስናይ እፎይ እንላለን፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሰው ቤት አገልጋይነታቸው አሠሪዎቻቸውም ሆኑ ማህበረሰቡ ስለነሱ ያለውን አመለካከት ከሚፈጥርባቸው ጫና በመነሳት ለመረዳት ችለናል ብዬ አስባለሁ፡፡ በሌላ በኩል እነርሱ እራሳቸው በሰው ቤት አገልጋይነታቸው የሚሰማቸው ምንድነው? ብለን ስንጠይቅ የምንገነዘበው ነገር ይኖራል፡፡ ራሔል ዕለታዊ የቤተሰቦቿ ፍላጎት ባለመሟላቱ ከብዙ ሙከራ በኋላ አማራጭ አድርጋ ስለገባችበት የወዳጆቿን ማንቋሸሽ ከምንም ሳትቆጥር በትጋት ሥራዋን ታከናውናለች፡፡ አንድ ቀን ከዚህ ሥራ እመልጣለሁ የሚል ብሩህ ተስፋም ነበራት፡፡ በመሆኑም ከሥራው ብዛት የተነሳ ከሚገጥማት አካላዊ ድካም ውጪ በአሠሪዎቿ በደል ደርሶባት መንፈሷ በበታችነት ስሜት ሲቆስል አናይም፡፡ ይልቁንም ባይሳካላቸውም ሥራዋን ለማንቋሸሽና የበታችነት ስሜት እንዲሰማት ይጥሩ የነበሩት ጎረቤቶቿና ወዳጆቿ እነ አሰገደች ነበሩ፡፡

የደራሲዋ ፋይል ገጸባህሪ ፅዮንን ስናይ በድርሰት ሥራዋ ላይ ያቀረብኩትን ሀሳቤን ተቃወመኝ ብላ አይዞሽ ባይ ፍቅረኛዋን ጥላ በደላላ አማካኝነት የተቀጠረችበት ሰው ቤት ባሰበችው ልክ የእፎይታ ኑሮ ሊሆንላት አልቻለም፡፡ ከአሠሪዎቿ ግላዊ ባህሪና ተገቢ ካልሆነው ቤተሰባዊ ግንኙነታቸው የተረፋት ፍርሀት፣ የበታችነት ስሜትና ስለ ነገ እርግጠኛ አለመሆንን ነበር፡፡ ብር ብላ ላለመውጣትም የያዛት “ወደሚያውቁኝ ሰዎች የምቀላቀልበት ጊዜ አልደረሰም” የሚለው እምነቷ ብቻ ነው፡፡

በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀጠረችባቸው ቤተሰብ አባላት እርስ በርስ ሰላም ማጣታቸው ለእሷም ከፍተኛ ጫና ነበረው፡፡ አንዳንዴ የእልህ መወጫ ያደርጓት ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት የተለያዩ ሥራዎችን ከማዘዛቸውም በላይ “የኔ ይቅደም” በሚል ቀጭን

ትዕዛዝ ግራ ያጋቧት ነበር፡፡ ሁሉም የሰው ቤት ተመሳሳይ ነው ብላ ስላሰበች አስፈቅዳም ሆነ በራሷ ግፊት ለመውጣት አልተጣደፈችም፡፡ በደሷን ችላ ለመኖር ብትጣጣርም ሴትነቷን ለመድፈር የሞከሩት የቤቱ አባወራ ድርጊት "እርም የሰው ቤት" በሚል የመጨረሻ ውሳኔ እንድትወስን አድርጓት ነበር፡፡

የገቦ ፍሬዋን ነፃነትን ስናይ በሰው ቤት አገልጋይነቷ የሚሰማት ከፍተኛ የሆነ የበታችነት ስሜት አለ፡፡ መፈጠሯን እስክትጠላ ድረስ በርካታ ስቃዮችን አሳልፋለች፡፡ ገና በዘጠኝ ዓመቷ የጀመረው የሰው ቤት ሠራተኝነት ታሪኳ ያላሳያት ግፍ፣ ያላሳያት ሰቆቃ የለም፡፡ ገና በትውልድ መንደሯ እያለች ዝም ብላ ትፈራው የነበረው አዲስ አበባ የተቀበላትም እንደፈራችው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከሷ በስተቀር ሰዎች ሁሉ ትክክል፣ ሰዎች ሁሉ ተወዳጅ፣ ሰዎች ሁሉ ተፈላጊ ወዘተ. ናቸው ብላ ስለምታስብ ለራሷ ያላት ግምት በጣም የወረደ ነው፡፡ በምትቀያይራቸው የተለያዩ ሰዎች ቤት ውስጥ የሚደርስባት ግፍ ተገቢ የሆነ ያህል አምና ተቀብላዋለች፡፡ ምን ግፍ ቢውሉባት የማታ ትምህርቷን እስካልከለከሏት ድረስ ልውጣ አትልም፡፡ አባቷ ሳትፈልግ ከቤተሰባቸው ነጥለው እንዳባረሯት እያስታወሰች የሚደርስባትን በደል ሁሉ የሚገባት አድርጋ ወስዳዋለች፡፡ "የወለደኝ አባቴ ያልፈለገኝ በኔ ጉዳት ማን ይጠየቃል?" የሚል አስተሳሰብ በማዳበሯ የሚደርስባትን አካላዊም ይሁን ስነልቦናዊ ጉዳት በዝምታ መቀበልን አዳብራለች፡፡

ከላይ ከተብራሩት ምክንያቶች በተለየ ሁኔታም ተተኳሪ ገጸባህሪያትን አይነትና አቀራረብ ምን እንደሚመስል በጥናቱ ተብራሯል፡፡ በሶስቱ ልቦለዶች ውስጥ ማለትም በ"ቢስ ራሔል"፣ በ"ደራሲዋ ፋይል" እና በ"የገቦ ፍሬ" ውስጥ የሚገኙት አገልጋይ ገፀባህሪያት የልቦለዶቹ ዋና ገጸባህሪያት ሆነው ቀርበዋል፡፡

አካላዊና ህሊናዊ መልካቸውን ስንመለከትም የብዙዎቹ በግልፅና ልንረዳው በምንችለው ልክ በድርጊቶቻቸው እየታጀበ ቀርቦልናል፡፡ በስነጽሁፍ ትምህርት የገጸባህሪያትን ሰብእና በድርጊቶቻቸው እያጀቡ ማቅረብ የተሻለው አቀራረብ በመሆኑ ከዚህ አንፃር እንስት ደራሲዎቻችን ተሳክቶላቸዋል ለማለት እችላለሁ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


1. ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው፡፡ (1973፣ ሐምሌ)፡፡ "የባሪያ ስም በ አማራው ባህል"፡፡ የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ Vol — x , No. 2

2. ስማቸው ዓለሙ፡፡ (1976)፡፡ "የአገልጋይ ገጸባህሪያት ጥናት ከ1966-1975 ዓ.ም በወጡ የአማርኛ ልቦለድ መፃህፍት ውስጥ" ያልታተመ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

3. ቴዎድሮስ አለበል፡፡ (2006)፡፡ "ልጅነት - በማሕሌትና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ፡፡" ያልታተመ የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

4. ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (2001)፡፡ በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

5. አለም እሸቱ፡፡ (1997)፡፡ "መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ፡፡" አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

6. እንዬ ሺበሺ፡፡ (2003)፡፡ የገቦ ፍሬ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርስቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

7. ዘሪሁን አስፋው፡፡ (2012)፡፡ የስነጽሑፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ጃጆው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ ኃላ.የተ.የግ.ማ.

8. ______________ ፡፡ (2013)፡፡ ከበአሉ ግርማ እስከ...አዳም ረታ (ስነ ጽሁፋዊ ተሐዝቦት)፡፡ አዲስ አበባ፣ ጃጆው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ ኃላ.የተ.የግ.ማ.

9. ______________፡፡ (2013)፡፡ የፎክሎርና የሥነ ጽሑፍ መመረቂያ ጥናቶች ጭምቃሳብ፡፡ አዲስ አበባ፣ ጃጆው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ ኃላ.የተ.የግ.ማ.

10. የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፡፡ (1978)፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

11. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡(1993)፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ አርስቲቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

12. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፡፡ (2011):: አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ስለ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ:: ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር 89 አዲስ አበባ::

13. የዝና ወርቁ፡፡ (2002)፡፡ የደራሲዋ ፋይል፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

14. ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ (1970)፡፡ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት በካህናትና በሀገረሰብ ቋንቋ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

15. ፀሐይ መልአኩ፡፡ (1996)፡፡ ቢስ ራሔል፡፡ አዲስ አበባ፣ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፡፡

16. Bethlehem Tekola, Mersha Kinfe, Fikirte Girma, Charlotte Hanlon. (2020). “Perceptions and experiences of stigma among parents of children with developmental disorders in Ethiopia” PMID: 32446155 PMCID: PMC7322556 DOI: 10.1016/j.socscimed.2020.113034, Free PMC article.

17. Cambridge — business - english dictionary https://www.google.com/url

18. David Palumbo-Liu. (2012). “The Deliverance of Others /Reading Literature in a Global Age/”. Durham and London፡ Duke University Press

19. Domestic Workers Convention, 2011 (No. 189) Convention concerning decent work for domestic workers (Entry into force: 05 Sep 2013) Adoption: Geneva, 100th ILC session (16 Jun 2011) - Status: Up-to-date instrument (Technical Convention). Convention may be denounced: 05 Sep 2023 - 05 Sep 2024//C189

20. Dr. D.Y. Patil. (2021). "Top five reasons for understanding the importance of learning and self-development." Dr. D. Y. Patil Institute of Hotel Management & Catering Technology. Approved by AICTE New Delhi and DTE Maharashtra (DTE Code: 6542) July, 09 2021 https://hmct dypvp.edu.in > blogs > Five Reasons Why Learning is So Important in Life!!!

21. Elaine Martin. (2011). "Intertextuality: An Introduction". The Comparatist, The University of North Carolina Press: Volume 35, May 2011 pp. 148-151, Article 10.1353/com..0001

22. Enguday Meskele Ashine. (2019). "Domestic Workers and the Right to Primary Education in Ethiopia: Evaluating the Adequacy of the Legal Framework." Journal of Law, Policy and Globalization www.iiste.org ISSN 2224-3240 (Paper) ISSN 2224-3259 (Online) DOI: 1 0.7176/JLPG Vol.86, 2019 Publication date: June 30th 2019.

23. Giuliani, Maria Vittoria. (2003). "Theory of Attachment and Place Attachment". in Psychological Theories for Environmental Issues. Burlington, VT: edited by Mirilias Bonnes, Terrence Lee, and Marino Bonaiuto. Ashgate, 137—170.

24. Hone Mandefro. (2012, MARCH 1). "Ethiopian women in the Middle East: it's contract slavery." Addis standard. P. 4 Addisstandard.com

25. Jillmarie Murphy. (2018). "Attachment, Place, and Otherness in Nineteenth-Century American Literature New Materialist Representations". Third Avenue, New York: First published by Routledge711, NY 10017.

26. Jin H. (2017). "Otherness, Evolution of Otherness in Gothic Literature". Project Proposal, Section L|0, Comments September 19th.

27. Jonathan Locke Hart. (2015). "The Poetics of Otherness War, ' Trauma, and Literature". Fifth Avenue, New York, NY 10010. copyright © First published in 2015 by PALGRAVE MACMILLAN® in the United States–a division of St. Martin's Press LLC, 175.

28. Kay, Jerald. (2001). "Attachment and Its Disorders in Clinical Child Psychology". Oxford: edited by William M. Klykylo and Jerald Kay. Wiley and Sons,: 274—288.

29. Mailafiya Aruwa Filaba. (2008). "Saratanya (House Servant) in Ethiopia and 'Ya'yan Magajiya (Errand Children) in Nigeria." African Research Review Vol. 2 (1) Jan.,2008

30. Marina de Regt and Felegebirhan Belesti. (2017). "Young, Female and Looking for Change: Migrant Girls' Narratives in Addis Ababa" Migrating out of Poverty Conference, March 28-29, 2017, SOAS, London.

31. MEHRET BEREHE https://africanfeminism.com/the-struggle-begins-at-home-domestic-worker-rights-in-ethiopia/ VIA: PHOTO BY LOUIS REYNOLDS TAGS: DOMESTIC WORKER'S RIGHTS, DOMESTICE WORKERS, ETHIOPIA, ETHIOPIAN DOMESTIC WORKERS, LABOUR RIGHTS, WOMEN'S RIGHTS AND LABOUR LAWS

32. Orson Scott Card. (1988). "Characters and Viewpoint" Published by Writer's Digest Books, an imprint of F&W Publications, Inc., 1507 Dana Avenue, Cincinnati, Ohio 45207. (800) 289-0963.

33. Parkin-Gounelas, Ruth. (2012). "Literature and Psychoanalysis: Inter-textual Reading". New York: Palgrave,

34. Perrine Laurence. (2016). "Literature Structure, Sound & Sense" New York: Haracourt Brace, Javanovich, Inc.

35. Read Cross-border care. (2018). “How to protect migrants in domestic work” (posted by Apolitical, July 2018). For resources on child labour and domestic work, visit the International Domestic Workers Federation’s website.

36. The Private Employment Agencies Convention, 1997 (No.181), and The Employment Relationship Recommendation, 1981 (No. 156), http://www.ilo.org/dyn/normlex/en/f? p=NORMLEXPUB:12100:0 NO:12100:P12100_ INSTRUMENT_ ID:2551460: NO 2/7

37. The unspoken servitude of women domestic workers 17 September 2018 /https://www.ituc-csi.org/IMG/pdf/unwomen_iutc_factsheets.pdf/

38. Urmila Bhoola. (2017). “Modern slavery: Regulation of labour markets key to eradicate forced labour” at the Human Rights Council 36th Session 12 September 2017 Press Releases Special Procedures from http://www.ohchr.org/EN/Issues/Slavery/SRSlavery/Pages/SRSlaveryIndex.aspx

39. Yohannes Mersha Belete. (2014). “Challenges and opportunities of female domestic workers in accessing education: A qualitative study from Bahir Dar city administration, Amhara region, Ethiopia.” International Jornal of sociology and antropology. Vol. 6(6), pp 192-199 june. 2014 DoI፡10.5897/IJSA2014.0525 Article Number:D2D62B045634

40. Zerihun Asfaw. (2012). “Bis Rahel” Ethiopian Journal of Languages and Literature Vol. XII No. 2 June 2012/133

41. How to Develop a Fictional Character? ... https://www.masterclass.com› articles › Sep 8, 2021

42. What is the character of a novel? … https://literaryterms.net> character

# አባሪ

በጥናት ሥራዬ ትኩረት ባደረኩባቸው ሁለት አሰርት ዓመታት ውስጥ የታተሙ የሴት ደራሲያን የፈጠራ ሥራዎችን ርዕስ አባሪ ለማድረግ ሞክሬያለሁ፡፡ እዚህ ላይ በራሴ ጥረት ያገኘኋቸውና የረዱኝ ደራሲያን የሰጡኝን አሰባሰብኩ እንጂ በሃያ ዓመታት ውስጥ የታተሙት የሴት ደራሲያን ሥራዎች እነዚህ ብቻ ስለመሆናቸው ማንም ርግጠኛ መሆን አልቻለም፡፡

| ተ.ቁ | ደራሲው | አርእስት | የታተሙበት ዓ.ም. | ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የምወድሽ በቀለ | የባከነ ጊዜ | 1990 | ረጅም ልቦለድ |
| 2 | ሰዓዳ መሐመድ | እሾህማ ወርቅ | 1992 | ረጅም ልቦለድ |
| 3 | የምወድሽ በቀለ | ያልፈራ ፍሬ እና ሌሎች ግጥሞች | 1992 | የግጥም ስብስብ |
| 4 | ሙሉወርቅ አስራት | ንቡት | 1993 | ረጅም ልቦለድ |
| 5 | ሙሉ ሰሎሞን ብዙነህ | ጊዜ | 1994 | የግጥም ስብስብ |
| 6 | አማረች ተሰማ | ነፍስ የዘራች ህይወት | 1994 | ረጅም ልቦለድ |
| 7 | ጥሩወርቅ ካሳ | ተስፋ የሰነቀ ጉዞ | 1995 | ረጅም ልቦለድ |
| 8 | ሙሉ ሰሎሞን ብዙነህ | ስንክፍሬ | 1996 | የግጥም ስብስብ |
| 9 | ሶስና አሸናፊ ረጋሳ | ከራስ ሽሽት | 1996 | ወጎችና ደብዳቤዎች |
| 10 | የምወድሽ በቀለ | እብዷ በለጠች | 1996 | ረጅም ልቦለድ |
| 11 | ፀሐይ መልአኩ | ቢስ ራሔል | 1996 | ረጅም ልቦለድ |
| 12 | ሜሮን አባተ | ምንታምር ፈተና | 1997 | የግጥም ስብስብ |
| 13 | የሰውደግ ጌታቸው | የበደል ውርስ ይቅር | 1997 | የስነቃል ፋይዳ |
| 14 | ትእግስት ተፈራ<br>እንዬ ሺበሺ<br>ማክዳ ኃይሌ<br>አፀደ ውድነህ<br>አወጣሽ ግደይ | ሩብ ጉዳይ | 1998 | የግጥሞች እና የአጫጭር ልቦለዶች መድብል |
| 15 | መቅደስ በቀለ /ማክዳ/ | የፍቅር መስዋዕት | 1999 | ረጅም ልቦለድ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 16 | የሺወርቅ ወልዴ | አትሮኖስ | 1999 | የግጥም ስብስብ |
| 17 | ፀጋ ዮሀንስ | ጂዳ ነኝ | 2000 | ረጅም ልቦለድ |
| 18 | ጤና ጌታሁን | የእርግቦች ሹክሹክታ | 2000 | የግጥም ስብስብ |
| 19 | እመቤት ስጦታው<br>እንዬ ሺበሺ<br>አበበች ድሪባ<br>የምወድሽ በቀለ<br>ሰላማዊት<br>ሶስና አሸናፊ<br>ሮማን ታደሰ<br>ሰዓዳ መሐመድ<br>መስከረም በቀለ | ያልተናበቡ ልቦች | 2000 | አጫጭር ታሪኮችና ግጥሞች |
| 20 | ሰርካለም ረታ | ቀለበት | 2001 | ረጅም ልቦለድ |
| 21 | ዘቢብ መልኬ | ስብጥር | 2001 | አጫጭር ታሪኮች እና ግጥሞች |
| 22 | እታለም እሸቴ | ምንዳ | 2001 | ረጅም ልቦለድ |
| 23 | ፅጌረዳ ኃይሉ | መቶ ደስታ ፍለጋ | 2001 | አጭር ልቦለዶችና ስኬቾች |
| 24 | ማርታ ቀፀላ | የትም ብዞር | 2002 | የግጥም መድብል |
| 25 | ራሄል ብርሃኑ ፍቅርተ | ድንግል | 2002 | የግጥም መድብል |
| 26 | ሠርካለም ረታ | ሳዱላዋ | 2002 | አጫጭር ልቦለዶች እና ግጥሞች |
| 27 | አበበች ድሪባ | የዘመን ስሞታ | 2002 | ሥነ-ግጥም |
| 28 | ብርቱካን አሳምረው በቀለ | አፍሪካዊ ፈረስ | 2002 | ግጥሞች፣ ልቦለድና አፈ ታሪክ |
| 29 | ፀሐይ መልአኩ | እመ ምኔት | 2002 | ረጅም ልቦለድ |
| 30 | ፀሐይ መልአኩ | የስሜት ትኩሳት ቁ.1 | 2002 | ረጅም ልቦለድ |
| 31 | ፀሐይ መልአኩ | የስሜት ትኩሳት ቁ.1 | 2002 | ረጅም ልቦለድ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 32 | የዝና ወርቁ | የደራሲዋ ፋይል | 2002 | ረጅም ልቦለድ |
| 33 | የምወድሽ በቀለ | ፍቅር የተጠሙ ነፍሶች | 2002 | አጫጭር ልብ-ወለዶች እና ሥነ-ግጥሞች |
| 34 | ቆንጅት ብርሃን | ምርኮኛ | 2002 | ረጅም ልቦለድ |
| 35 | መአዛ መንግስቴ | ከአንበሳ እይታ በታች | 2002 | ረጅም ልቦለድ |
| 36 | ሠርካለም አልታዬ (ሪታ) | ያልተመረቀው | 2003 | አጫጭር ልብ-ወለዶች እና ሥነ-ግጥሞች |
| 37 | ስንዱ አበበ | ራምቤ | 2003 | አጫጭር ልብ-ወለዶች እና ሥነ-ግጥሞች |
| 38 | አበባ ግርማይ | ውስብስብ | 2003 | ረጅም ልቦለድ |
| 39 | እንዬ ሺበሺ | የገቦ ፍሬ | 2003 | ረጅም ልቦለድ |
| 40 | ሰናይት ፈቃዴ | ማራ | 2003 | ረጅም ልቦለድ |
| 41 | የምወድሽ በቀለ | ዋጊኖስ | 2003 | የግጥም መድብል |
| 42 | ተናኜ ከበደ | እኔነት | 2003 | የግጥም መድብል |
| 43 | ውድአላት ገዳሙ | ስደተኛ ግጥሞች | 2003 | የግጥም መድብል |
| 44 | ሀሊና ተፈራ<br>አበበች ድሪባ<br>ተጋርዳ ሃይሉ<br>ሶስና አሸናፊ<br>ብርቱካን አላምረው<br>ምስራቅ ተረፈ<br>የምወድሽ በቀለ<br>አበባ ሽታዬ<br>እየሩሳሌም ነጋ<br>ሩታ አርዓያ<br>ትእግስት ምትኩ<br>ዘርፍነሽ አግዘው | እኛ ቁ.2 | 2003 | የግጥም መድብል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በለጡ በጋሻው<br>ታየች ወልደማርያም | | | |
| 45 | ሜሮን መለሰ | ከደመና በታች /በቀጠለ ህይወት ውስጥ/ | 2004 | ረጅም ልቦለድ |
| 46 | በሁሉም አለበል | የተዋጡ ድምፆች | 2004 | አጫጭር ልቦለዶች |
| 47 | ትዕግስት ዓለምነህ | የዝምታ ጩኸት | 2004 | የግጥም ስብስብ |
| 48 | አበባ ግርማይ ወ/ስላሴ | መውሰቦ | 2004 | ረጅም ልቦለድ |
| 49 | የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበር የአማራ ክልል ቅርንጫፍ አባላት | እኛ ቁ.4 | 2004 | የግጥም መድብል |
| 50 | ፀጋ ዮሐንስ | የሚሼል ኮከቦች | 2004 | ረጅም ልቦለድ |
| 51 | ፀሐይ መልአኩ | የንስሐ ሸንጎ | 2004 | ረጅም ልቦለድ |
| 52 | ፀሐይ ይስማው | ሚስጥር | 2004 | ረጅም ልቦለድ |
| 53 | እታለም እሸቴ | ህልመኛዋእናት | 2004 | ረጅም ልቦለድ |
| 54 | ከበቀለች ቶላ | ስለ ዕፅዋት ልሕፃናትና ለታዳጊዎች | 2004 | ኢ- ልቦለድ |
| 55 | ከበቀለች ቶላ | ለምለም እንጀራ ከብዝሃ ሰብሎች | 2004 | ኢ- ልቦለድ |
| 56 | የምወድሽ በቀለ | ናዋዡ ምሁር /አስራ ዘጠኝ ሀሙሶች | 2004 | እውነተኛ ታሪክ |
| 57 | የዝና ወርቁ | መፍቻው | 2004 | አጫጭር ልቦለዶች |
| 58 | ወ/ሮ ይድነቃቸው አሰፋ | ያልተነገረለት የሀገር ባለውለታ (በቀለ ዓለሙ ጋንች) | 2004 | የህይወት ታሪክ |
| 59 | የዝና ወርቁ<br>እንዬ ሺበሺ<br>የምወድሽ በቀለ | አዙሪት | 2004 | አጫጭር ትረካዎች |
| 60 | ከአስቴር ሰይፈ | የህይወት ስንቅ | 2005 | ኢ- ልቦለድ |
| 61 | እየሩሳሌም ነጋ | የድብልቅልቅ ሰፈር ሰዎችና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች | 2005 | አጫጭር ልቦለዶች |
| 62 | ሩታ አርዓያ | የፍቅር አምላክ | 2005 | ረጅም ልቦለድ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 63 | ፀሐይ መልአኩ | የጴጥሮስ ዋዜማ | 2005 | ታሪካዊ ልቦለድ |
| 64 | የልፍኝ ወርቁ ጀምበሬ | ትውስታ | 2005 | ረጅም ልቦለድ |
| 65 | እቴ ገረመው | የጭን መነባንብ | 2006 | ረጅም ልቦለድ |
| 66 | ታየች ወ/ማርያም | ገርባባ | 2006 | የግጥም ስብስብ |
| 67 | ትንቢት ምናለ | ቃልና መንገድ | 2006 | የግጥም መድብል |
| 68 | ሐረገወይን ወልዴ | አማርኛ ናፈቀኝ | 2006 | የግጥም መድብል |
| 69 | ብርቱካን አላምረው በቀለ | ስሞት አትቅበሩኝ ቁ.2 | 2006 | እውነተኛ ታሪክ |
| 70 | የጠፋው ቤተሰብና ሌሎች | የሺ.ወርቅ ወልዴ | 2006 | አጫጭር ልቦዶች |
| 71 | ራሔል አሸናፊ | እንካችሁ አደራ | 2007 | ረጅም ልቦለድ |
| 72 | አለም ደስታ | ህንደኬ /ጽኑዎቹ የኢትዮጵያ ሴቶች/ | 2007 | ታሪክ |
| 73 | ኤልሳቤጥ ጌታቸው | ምርኮ | 2007 | ረጅም ልቦለድ |
| 74 | ዝናሽ ኤሊያስ (ዲና) | መስዋዕት | 2007 | በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልቦለድ |
| 75 | የሺእመቤት ካሳ | አመሻሽ | 2007 | ረጅም ልቦለድ |
| 76 | የደስደስ ተስፋ | እንጀራ ከመከራ | 2007 | ረጅም ልቦለድ |
| 77 | ሊና ካሳሁን | ፍቅር እና አደራ እና ሌሎችም | 2007 | አጫጭር ልቦለዶች |
| 78 | ቤተልሄም ኒቆዲሞስ | እንባና አሞሌ | 2008 | የወጎችና ግጥሞች ስብስብ |
| 79 | ገብርኤላ ገርማንዲ | Queen of Flowers and Pearls | 2008 | ረጅም ልቦለድ |
| 80 | አበራሽ በቀለ | የማለዳ ወጥመድ | 2008 | እውነተኛ ታሪክ |
| 81 | እመቤት ደቻሳ | ያልተገባው | 2008 | በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልቦለድ |
| 82 | እታለም እሸቴ | ተፈናቃይ ፍቅር | 2008 | ረጅም ልቦለድ |
| 83 | በሁሉም አለበል | ውስብስብ ውሎዎች | 2008 | አጫጭር ልቦለዶች |
| 84 | ባዩሽ ከበደ(ዶ/ር) | አስገራሚው የኢትዮጵያ ጤፍ | 2009 | ኢ-ልቦለድ |
| 85 | ትእግስት ፀዳለ ጎሩይ | ቅብጥብጧ | 2009 | ረጅም ልቦለድ /ትርጉም |
| 86 | አስራት ጥላሁን | ግጥም ለትውልድ | 2009 | የግጥም መድብል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 87 | ፀሐይ ይትባረክ | የፀሀይ ጉዞ | 2009 | ግለ ታሪክ |
| 88 | ሰዓዳ መሐመድ | ደባሎቹና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች | 2010 | አጫጭር ልቦለዶች |
| 89 | እመቤት ጀማል | አብሮነት | 2010 | ስነልቦና |